# ራእይ፡ ምዕራፍ አራት ክፍል 2

ዛሬ ጠዋትም መድረስ በመቻሌ በጣም ደስ ብሎኛል። በረዶውን እንዴት አደርገዋለሁ ብዬ እያሰብኩ ነበር... አሁን፡ በኮሎራዶ ብንሆን ኖሮ፡ ይህ በረዶ ለሰላሳ እና ሞቹ፡ እንዲሁም ከዜሮ በታች አርባ ያህል ይሆን ነበር፡ እናንተም እንዲህ እየበተናችሁት፡ እና ውስጡ ላይ እየተንከባለላችሁ፡ **እፎይ**፡ ትሉ ነበር። ክረምቱ በሙሉ እንደዚያ ይቀጥላል። አሁን ግን፡ እዚህ ጋር፡ እንደመሆኑ መጠን... በዞኑ አጋማሽ፡ መኃል በመሆኑ፡ እጅግ እርጥበታማ እና ጭቃ እና መጥፎ ይሆናል፡ እና—እንደው ምናልባት ጸደይ ጠብቄ—ለመመለስ፡ ወደ አሪዞና፡ በበረርኩ ብዬ እስክመኝ ድረስ የደረስኩ ይመስለኛል።

2 ሁላችንም ጉንፋን የሚይዘን በዚህ መንገድ ነው፡ ጀርሞች እና ነገሮች አሁን መሬት ላይ ተኝተዋል በረዶ ይሆናል ከዛ በኋላ ይቀልጣል፡ ከዛ በኋላ በረዶ ይሆናል ከዛ በኋላም ይቀልጣል። እና ያ ነገር ወደላይ ሲተን ወደ ውስጥ እንተነፍሰዋለን፡ ያን ጊዜ የጉሮሮ ህመም፡ ራስ ምታት፡ ህመሞች እና ውጋቶች ያሰይዙናል። እና፡ ማይ፡ ማይ፡ እንዴት ያለ ድንቅ ጊዜ፡ እንዴት ያለች ድንቅ ምድር ትሆን።

ከወንዙ ማዶ ያለች ምድር፡  
ስሟን ሲጠሯት የምታምር፡  
በእምነት አዋጅ ደርሰን ዳርቻዋ፡  
አንድ በአንድ እንጠጋለን ወደ ደጇ፡  
ዘለአለም ለመኖር በውስጧ፡  
ሲደወሉ ሰምተን ወርቃሞች ደወሎቿ።

3 ይህ ማለት ለመኖር የምንሄድበት ሰፍራ ነው፡ አይደል? የምንጠብቃት ቀን ያቺ ናት።

4 እንግዲህ፡ ትናንትና ማታ ከወንድሞቼ በሰማኋቸው ስብከቶች እና ነገሮች ሁሉ በእውነት ተባርኬባቸዋለሁ። ፓት ታይለር የት አለ፡ ዛሬ ጠዋት መጥቷል? ውይ፡ ፓት፡ አንተ የተፈጥሮን ድርብ የምታክል የህይወት ግዙፍ ሰው ተቀምጠህ አልታየኸኝም። እና—እና እ—ተቀምጠህ አላየሁህም። ፓትን... ፓት ሲናገር ስሰማው ይህ የመጀመሪያዬ ነው፥ በእርግጠኝነት ተባርኬበታለሁ፡ ሁላችንም እንደተባረክን እርግጠኛ ነኝ።

5 እና ከዚያ በመቀጠል እሳት የሆነውን የሰብከት ምስክርነት የሰጠው ታናሽ ወንድም ያም በእውነት እንደ መትረየስ ተኩስ ነበር። ሌላም ከኦሃዮ የመጣ፡ ወንድም፡ ተዋውቄዋለሁ። ዛሬ ጠዋት እዚህ አለ? እዚህ አካባቢ ነው? ወንድም ኔቪል ስለሱ ሲናገር እጅግ ፈጣን መትረየስ ነው ብሎታል።

6 ከዚያ በመቀጠል ወንድም ጄ. ቲ. ፓርኔል። እ—እና ወደ ወንድም ቢለር የደረሱ አይመስለኝም። ወንድም ፓርኔል፡ እዚህ አለ? ወንድም ፓርኔል፡ ወንድም ቢለር? እርግጠኛ አይደለሁም፡ ወንድም ቢለርን ያየሁ መሰሎኝ ነበር።

7 እነዚህ መብራቶች፡ ይሄኛው... አዲሱን ተበርናክል ሲሠሩ፡ ነገሩን በተለየ ምልኩ፡ በመጠኑ እንደሚጠግኑት ተሰፋ አደርጋለሁ። ይሄኛው የመጀመሪያችን፡ እንደ ሙከራ ነው። ስለዚህ አዲስ የምናመጣ ከሆነ፡ እንግዲያውስ፡ ከዚህኛው በመጠኑ የተለየ እንዲሆን እንፈልጋለን፡ ማየት ይከለክላችኋል፡ ለተበርነክል ሲሆን፡ ለታዳሚዎቹ **እንደዚህ** ተንጠልጥሎ ቢሠራ ደስ ይለኛል። ሁልጊዜ ታዳሚዎቻችሁን በቀጥታ ፊት ለፊት ታያላችሁ። በተለይ በመለየት ጸጋ አገልግሎት ውስጥ፡ በትክክል ዙርያውን መቃኘት ትችላላችሁ። እያችሁ፡ ከፊት ከኋላ፡ ከየጥጉ እንዲህ ታውቀዋቸዋላችሁ። እና ደግሞ፡ ምንም እንኳ አነስተኛ መተላለፊያ ባልኮኒ ቢኖርም እንኳ፡ የተሻለ ነው።

8 ቢሊ እዚህ ከሆንክ፡ ወንድም ሊትልፊልድ፡ ትላንት ማታ ደወለልኝ እና የዚያን ያስመረቅኳት ተበርነክል፡ የአርኪቴክቱን ዝርዝሮች እየላከ ነው... ወንድም ዉድ፡ እንደሚመስለኝ፡ አርክቴክቱን ለመሳል፡ አምስት መቶ ዶላር አስከፍሏል። እርሱም—ያንን ነገር ከቁሳቁሱ ሁሉ ጋር እና ከዋጋው ጋር እየላከ ነው እና እያንዳንዱ ሁለት-በ-አራት እንዲህ-በ-እንዲህ ውስጥ ይገባል። እና እየላከልን ነውና፡ መምጣት ይፈልጋል፥ እርሱም ወደ አንጨት ባለሞያዎች እና የመሳሰሉትን ሄጄ የእኔን አይነት አቆራረጥ—እንዲቆርጡልኝ ከቻሉ እያለሁ አለ። በጣም የሚያምር ተበርነክል፡ በጣም ትልቅ አይደለም፡ ግን የሚያምር ቅርጽ አለው።

9 ስለዚህ እኔም ነገርኩት፡ እንዲህ አልኩት፡ "ለቢሊ እንደላክለት ወዲያውኑ ለባለአደራዎች እና ለዲያቆናት እ—እሰጣቸዋለሁ ከዚያም—ሕንፃቸውን ለመጀመር ምን ያህል አግባብነት እንዳላቸው እንዲመለከቱ እናደርጋቸዋለን።"

10 "ያንን ስታደርጉ፡ እኔም እመጣለሁ፡ ያን ጊዜ ቱታዬን ለብሼ አብሬአችሁ እቆያለሁ፡" ብሎኛል። ወንድም ሊትልፊልድ ሞገስ ያለው፡ ቸር፡ በጣም ጥሩ ሰው ነው።

11 አሁን፡ አዲሱን ዓመት ለመጀመር፡ ሁላችሁም ትክክለኛ ስሜት እየተሰማችሁ ነው? አሜን! በአዲሱ ዓመት በትክክል ተጓዙ። ጌታን በማገልገል፡ በትክክል ልንጀምረው ይገባል። ዛሬ ጠዋት ስትነሱ ስላለፈው አመት እና ስለ ሁሉ አመሰግናችሁ፡ "ያለፈውን ሁሉ ደምስሰልን፡" ብላችሁ የጠየቃችሁ ስንቶች ናችሁ? ስለዚህ፡ ሰንነቃ አልጋችን ጎን ሆነን እንለዋለን፡ ከዚያም የትንሿ ቤተሰብ መሰውያ ወደ ሆነችው ጠረጴዛ እንመጣለን፡ ሁሉም ይሰበሰብና ይጸለያል።

12 እናም ሁልጊዜ ከመተኛታችን በፊት የመጸለይን ልማድ ለማድረግ እንለማመድ። ከመጀመሪያ፡ ከተቀየርኩበት ጊዜ ጀምሮ፡ አደርገዋለሁ። ማለዳ እነሣለሁ፡ እና ለመራመድ ጨለማ እና ጭጋጋማ ይሆንብኛል፡ መሄጃዬ ይ—ይጠፋብኛል። እጄን ያዘኝ ካልኩት ግን ቀኑን ሙሉ ይመራኛል።

13 እና ትዝ ይለኛል፡ ገና ወጣት ሰው በነበርኩ ጊዜ፡ መኖርያችን ከመንገዱ ማዶ ነበረ፡ ቢሊ ፖል የሦስት ዓመት፡ ወይም የአራት ዓመት ልጅ ነበር፡ የምንኖረው ከመንገዱ ማዶ ነበር። እና አንድ ምሽት ውሃ መጠጣት ፈለገ፡ እና ጭልፋ የተንጠለጠለበት ባልዲ፡ ወጥ ቤት ውስጥ ነበር። አልኩትም... አቤት፡ በጣም ደክሞኛ ነበር፡ ቀኑን ሙሉ በትጋት ሰርቼ፡ እኩለ ሌሊት ድረስ ሰብኬ ነበር። እና—እሱ "አባዬ፡ ውኃ—መጠጣት እፈልጋለሁ፡" አለኝ።

14 እኔም፡ “ቢሊ፡ ወደ ኩሽናው ሂድና፡ ጠረጴዛው ላይ አለልህ።” አልኩት…

15 ተነሣና፡ አይኑን አሻሸቶ፡ አሻግሮ ተመለከተ፡ እና “አባዬ፡ መሄድ እፈራለሁ፡” አለኝ። አያችሁ?

16 “አይ፡ ምንም… ችግር የለም፡” አልኩት። “ሮጠህ ሂድና፡ ጠጣ፡ የኔ ማር፡ እኔ አባትህ ድክም ብሎኛል፡” አልኩት። እስከ መስኮቱ ድረስ፡ ትንሽ ርቀት ነው።

እና—እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ እኔ ግን ፈርቻለሁ።” አያችሁ?

17 እና፡ ከህጻኑ ጋር ተነሣሁ። ጠጋ አልኩትና እጄን ያዘ፡ መያዙም በጀ፡ ሚዳ ወለሉን በሰም የወለወለችበት የኒሎኔም ጨርቅ እስኪረግጥ ድረስ፡ አራት እና አምስት እርምጃ አልተራመድንም፡ ያም ምን አይነት እንደሆነ ታውቁታላችሁ። እና እንዲህ ተንሸራተተ፡ እጁን ይዤዋለሁ፡ እሱም ጠበቅ አርጎ እጄን ያዘኝ። ለአፍታ ባለሁበት ቆም አልኩኝ፡ እና “እግዚአብሄር ሆይ፡ እውነት ነው፡” ብዬ አሰብኩኝ። አያችሁ? “መቼ እንደምንሸራተት አላውቅምና፡ አንተ እጄን ሳትይዘኝ አንድ እርምጃ ማድረግ አልፈልግም።” አያችሁ? “እና ትልቁ እና ኃይለኛው እጅህ፡ እጄን እንደያዘኝ እስከተሰማኝ ድረስ፡ በችግሬ ጊዜ እንደምትይዘኝ አውቃለሁ… ” አያችሁ?

18 ስለዚህ እ—እጄን በእሱ ውስጥ ማቆየት፡ እንደ ልማድ ለማድረግ እሞክራለሁ። አንዳንድ ጊዜም ለራሴ እይታ እንኳን አሰቂኝ የሚመስሉ ነገሮችን አደርጋለሁ፡ በሰው አእምሮ ውስጥ በጣም ያልተለመዱ የሚመስሉ ነገሮች ናቸው፥ ዝም ካልነው ግን፡ ነገሮች ልክ እንዲከናወኑ መሆን ያለበት ብቸኛው ነገር ይህ መሆኑን ተረድቻለሁ።

19 ታውቃላችሁ፡ አሁን እዚህ ትክክል የማይመስሉ ነገሮች ሁሉ፡ እግዚአብሔር ወደነሱ ሲመራችሁ፡ አያችሁ፡ እንዴት እንደሚመራ ራሱ ስለሚያውቅ፡ በሆነ መልኩ ትክክል ይሆናሉ። ስለዚህ፡ እርሱ በቂ ጸጋችን መሆኑን፡ እና የምንፈልገው ወይም የምንሻው ሁሉ በእርሱ ዘንድ እንዳለ ተመልክተን፡ ከእርሱ በቀር ሌላውን ሁሉ ወደ ጎን ትተን የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ እንያዝ።

20 ከዚህ በፊት የምንዘምረው ዝማሬ ነበረ፡ ሲዘመር ከሰማሁት ቆይቷል። እንግዲህ፡ መዘመር አልችልም… በመካከላችን እንግዶች ያሉ አይመስለኝም። ስለዚህ… ታውቃላችሁ፡ ትንንሽ ዝማሬዎች ሰሞክር፡ ሰለምወድ ነው። ምናልባት ጂንም፡ ይህን ካሴት በህዝብ ዘንድ እንዲወጣ ከፈቀድክ! ይህች ትንሿ ዝማሬ ድሮ እንዘምራት ነበርን፦

ጊዜ በፈጣን ለውጥ የተሞላ፡
የለም በምድር ላይ የማይነቀል የጸና፡
ተሰፋህን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ገንባ፡
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!

እስኪ ይህን ዝማሬ ሰምታችሁ የምታውቁ? ኦህ፡ በጣም እወደዋለሁ፡ እናንተስ? እስኪ አዝማቹን እንሞክረው፦

የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!
ተሰፋህን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ገንባ፡
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!

አዝማቹን እንሞክረው፦

ጉዟችን ሲጠናቀቅ፣
ለእግዚአብሔርም ታምነን፣
ውብ እና ድንቅ የክብር ቤታችሁ፣
በተማረከች ነፍሳችሁ ታያላችሁ!

የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!
ተስፋህን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ገንባ፣
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!

21 ፈቃደኞች ከሆናችሁ፣ አሁን ለጸሎት አንድ ደቂቃ ብቻ እንቁም፣ አንድ እጃችንን ወደ እግዚአብሔር እያነሳን እንደገና እንዘምራለን፦

የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!
ተስፋህን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ገንባ፣
የማይለወጥ የእግዚአብሔርን እጅ ያዝና!

አትመኻ ከንቱ የዓለም ሀብት፣
ቶሎ የሚበሰብሰውን በፍጥነት፣
ተስፋህን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ገንባ፣
መቼም በማያልፍ በማይጠፋ!

22 የሰማይ አባት ሆይ፣ እንደቆምን፣ ጌታ ሆይ፣ እነዚያን የድሮ ዝማሬዎችን መዘመር እንወዳለን፣ ወደ ልባችን ውስጠኛ ክፍል ወርደው ለአንተ ለሕያው አምላክ፣ ያለንን የፍቅራችን መግለጫ ፈልፍለው ያወጡታልና። እጆቻችንም ወደ ላይ ስናነሣ፣ ጌታ ሆይ፣ ዛሬ ጠዋት፣ “ጌታ ሆይ፣ እጃችንን ያዝ” የሚል መታሰቢያ ነው። ስለ ቢሊ ፖል፣ እጄን እንዴት እንደያዘ እየተናገርኩ ነበር፣ እኔ እርሱን ይዤው ባልሆን ኖሮ ይወድቅ ነበርና። እናም፣ አምላክ ሆይ፣ አንተ እጃችንን ባትይዝ ስንት ጊዜ በወደቅን ነበር! ስለ እሱ ስናስብ፣ እንደ ህጻን ልጅ፣ ያለ እናት… እንዴት ይቻላል… ህይወትስ እንዴት ይሆናል፣ ያለፈባቸው ጎዳናዎች በሙሉ፣ ድሮ በሞተ ነበር፣ ነገር ግን እኔ ዘርግቼ የማልደርስባቸው ነገሮች፣ ተዘርግታ የምትይዝ እና የምትደርስ ታላቅ እጅህ ነበረች። አሁንም፣ እጅግ እናመሰግንሃለን።

23 ጌታ ሆይ፣ ነፍሳችን ከዚህ አካል ስትለይ፣ አሁንም የምንዘረጋበት፣ እና የምንይዘው እጅ እንዳለ፣ ከወንዙ ማዶም እንደሚያደርሰን በማወቃችን በጣም ደስ ብሎናል። ስለ እነዚህ ነገሮች፣ ስለዚህ ማሕተም፣ የነፍስ መልህቅ ስለሆነው፣ ስለተባረከው ማሕተም፣ በዚህ ጉዞ ላይ ወይም የህይወትን ዋና ባህር ላይ ስንጓዝ እንድንረጋጋ ስለሚያደርጉን ነገሮች እናመሰግንሃለን።

24 አባት ሆይ፣ ገጣሚው እንደተናገረው፣ እንዲሁ እንጸልያለን፣ “የተረበሸ፣ እና የህይወት መርከብ የጠፋበት ወንድም፣ ጽናታችንን (ትጥቃችንን)፣ አይቶ፣ ልቡ እንዲጸና፣ ወይም ዳግም ወኔው ተነስቶ እንደገና ይነሣ”፥ ብንሰናከል ወይም ብንወድቅ፣ ሁሉን-የሚችለው አምላክ፣ ታላቅ እጁ እንደሚረዳን ይህን እወቁ። ፀጋው በቂ ነውና።

25 አሁንም፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ አዲሱን ዓመት፡ በማለዳ ዝማሬና፡ በደስታ መዝሙር እንድንጀምር እንጸልያለን፡ እግዚአብሔር በህይወት ጉዞ እና በሞት ወንዝ ላይ ወደ ተሰፋይቱ ምድር እንደሚመራን አውቀናልና። ዛሬ ጠዋት ዓይኖቻችን ከዮርዳኖስ ከባባድ ጅረቶች ባሻገር፡ ወደ አበቦች ሳር ወደ ሜዳ—የለመለመ መስክ ወዳለበት ሜዳ ያያሉ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ነፍሳችን ራእዩን እንዲይዘው እና እንዳይለቀው፡ እንጸልያለን። አንድ ቀን እንደ ቀድሞው፡ እንደ ኤልያስ፡ ወደዚያች ጅረት ስንወርድ፡ የእግዚአብሔር መኀናጸፊያ የሞት ጅረቶችን ይመታልና ያን ጊዜ ያለ ፍርሃት እንሄዳለን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

26 ወደ ቃልህ ስንቀርብ እርዳን። ጌታ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስህ ይህንን ቃል እንዲቀባ እጸልያለሁ። አስተማሪ ሳንሆን፡ ይህን ለማስተማር በእርግጠኛነት ብቁዎች አይደለንም። ይህን ማወቅ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ መምህር በሆነው በታላቁ ጌታ እንደሆነ እናውቃለን እርሱ መጥቶ በልባችን ውስጥ ማ—ማደርያውን ይቆጣጠር፡ አእምሮአችንን በተሻለው—መንገድ ኃያል ያድርገው (ሀሳቦቻችንም እንዲሁ) እርሱ... ቅዱሳት መጻሕፍትን ይተረጉምልናልና። በዚህ ላይ በጥብቅ እንደገፋለን።

27 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይሄን ሰናሰበው፡ አቤት፡ እንደዚያ ያለ ሕያው እና ድንቅ አባት፡ እርሱም ወደ... ሟች ወደ ሆኑት ፍጡራን ወደ እኛ ወርዶ የረዳን፡ የዘለአለም ህይወት ልደት ራሱ ነው፡ ቃሉን ሰምተን እንድንኖርም በአፋችን በልባችን በጆሮአችንም አምጥቶ ይሰጠናል፡ ይህም አባት ሆይ፡ ከሱ መምጣት ጋር ምንም ሕብረት ከሌለው ከእርግማን ይቤዠን ዘንድ፡ ያም የፈጸመው የሰው ዘር ነውና እኛም የእነዚያ—የመጀመሪያዎቹ ባለትዳሮች የዘር ሐረግ ነን። “እኛም በኃጢአት ተወልደን፡ በዓመፅ ተፈጠርን።” ጻድቅ እና ሕያው አምላክ ግን ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለን ያውቃል። ነገር ግን የማምለጫ መንገድ አዘጋጅቶ የመመለሻ እድል ሰጥቶናል። ወደ አባት ቤት በመምጣታችን ምንኛ ደስ ብሎናል!

28 አሁንም ቤተክርስቲያናችንን፡ እንዲሁም—ፓስተራችንን፡ ትሁት የሆነው አገልጋይህን ወንድም ኔቪልን፡ እንድትባርክ፡ እንጸልያለን፣ ዲያቆናትን እና ባለአደራዎቻችንን፡ ካሳለፉት ይልቅ ታላቅ አመት እንድታደርግላቸው እንጸልያለን። ይሁንላቸው፡ ጌታ ሆይ። እረጅም እድሜ ስጣቸው። አገልጋዮች ናቸውና፡ ጌታ ሆይ፡ አበርታቸው። በአገልግሎት ዘርፋቸው ዘወትር ብርቱዎች ይሁኑ። ምእመናንን እ—አባላትን፡ ባርካቸው፡ ወደዚህ ቤት የሚመጡትን የተወደዱ ልጆችህ ሁሉ። እግዚአብሔር ሆይ፡ የዚህን ቤት ደጃፍ የሚያልፉትን የእያንዳንዳቸውን ነፍስ ለአንተ ማረክናቸው። ጌታ ሆይ፡ ለአንተ ማረክናቸው። በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ፡ ቃልህን ሞቺ እና እውነተኛ አድርገው የሚያመጡ አገልጋዮች እንድንሆን እርዳን፡ ይህም ጌታ ሆይ፡ አንተን ለመምሰል እንዲናፍቁ ነው። ይሁን። የሚመጡትን ድውያንና ህመምተኞችን ፈውስ። በአለም ዙሪያ ሁሉ፡ በሁሉም የእግዚአብሔር ቤቶች ይህ ይሁን።

29 በመጨረሻም፡ ጌታ ሆይ፡ አንተ ሁሉንም ስትጨርስ፡ ወደ ደጆችህ ገብተን፡ በእግዚአብሔር የእንግዳ መቀበያ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጠን፡ ቁጥር ለሌለው ዓመታት አብረን እየበላን መኖር ይሁንልን። እስከዚያው ድረስ፡ ጤና እና ጥንካሬ፡ ሐሴት፡ ደስታ፡ ኃይል እና ብርታት፡ እና የሚመራ የመንፈስ ቅዱስ በረከት ይሁንልን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን። አረፍ አረፍ በሉ።

30 ዛሬ ጠዋት ያንን ጥሩ ሙዚቃ ተባርኬበታለሁ። እና... በሰዓቴ፡ ገና መግባቴ፡ ከአንድ መልካም ወዳጄ ጋር እያወራሁ ነበር፡ ወንድም ሰካግስ፡ እና—ወንድም ጂን ከኋላ፡ እና ሌላ ወንድማችን ከበሩ አጠገብ፡ የተወሰነውን ተካፍያለሁ፡ ይሁን እንጂ በመቅጃው ላይ እጅግ የሚያምር ነበር።

31 እንዴት ናችሁ ራእይ ላይ እየተባረካችሁ ነው? ጥሩ ነው? ከኋላ እንዳለችው፡ ትንሿ ልጄ፡ እንደ ሳራ፡ ለእኔም “ሪቮሉሽን” እንደሆነ ይሰማኛል፡ ብቻ—በተደጋጋሚ ሪቮሉሽን እየሆነ ይገኛል። ታውቃላችሁ፡ እስከ መጋቢት ወይም እስከ ሚያዝያ ድረስ ቢደርስልን እመኛለሁ፡ አንድ ትልቅ ቦርድ ከኋላ ላይ ለማስቀመጥ እና በቀን ብርሃን እየመጣን አጠቃላይ ቻርቱን እና ሰዕሎቹን እንሰልበታለን፡ እና እንደ መሰኮት ወደ ላይ እና ወደ ታች የምናንሸራትተው ቢሆን፡ ታውቃላችሁ፡ ሁልጊዜ አንድ ታላቅ ተበርናክል የሆነ ቦታ ላይ እንዲኖረን እንደምመኘው እና ይህ ቻርቱን ሰቤ አውርጄ፡ እስከ መድረኩ ድረስ ማምጣች የምችለው ቢሆን፡ ጌታም የሰጠኝ መገለጦችና ትርጓሜዎችን በሙሉ፡ ጠቋሚ ነገር ይዤ እነዚህን ዘመናት በሙሉ ማሳየት ብችል እመኛለሁ። ከዚያ አንደኛው ላይ ስንጨርስ፡ ወደላይ ሰቅለን፡ ሌላኛውን **እንዲህ** ወደ ታች መጎተት እና በዚያ ላይ መጀመር፡ እና ሙሉውን ማስተማር። አቤት፡ እንደው እንደ ትንሿ ሰማይ ይሆን ነበር፡ አይደል? ክረምቱን በሙሉ፡ ከጌታ ጋር እንዲህ ቁጭ ማለት ነበር።

32 ተለይታችሁ ከእርሱ ጋር መሆን እንዴት ድንቅ ነው! ታውቃላችሁ፡ አንድ ዝማሬ እንዘምር ነበር፡ “ከጌታዬ ከክርስቶስ ጋር ብቻዬን መሆን የምወድበት ጊዜ አለ፡ ችግሬን ሁሉ በራሴ ልነግረው እችላለሁ።” እያችሁ፡ መድረሻው መንገድ ያ ነው። ሮይ ዴቪስ፡ አንዲት ዝማሬ ይዘምር ነበር፡ **ገለል በልና ከኢየሱስ ጋር ጸልይ፡** የሚል ዝማሬ ይዘምሩ ነበር። አቅጣጫዎች ሁሉ... የምትመለከቷቸው ነገሮች ሁሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ውስጥ ይመራሉ፡ አይደል?

33 አሁን፡ ባለፉት የሰምንት ቀናት ሰብሰባዎች፡ የቤተክርስቲያን ዘመን በተመለከተ ተነጋግረናል... ከዚያ በኋላ ትናንት ማታ ራዕይ 4ኛው ምዕራፍ 2ኛው ቁጥር ላይ የደረሰን ይመስለኛል። እና ይሄን ለመማር—ሁላችሁም ትናንት ማታ እዚህ ነበራችሁ ብዬ እገምታለሁ። ስለዚህ... ምናልባት ዛሬ ጠዋት አንድ ወይም ሁለት ቁጥሮችን ከሸፈንኩ፡ ወ... ወይም ጌታ እስከፈቀደው ድረስ፡ እኔ አላውቅም። እስከ 6ኛው እና 7ኛው ድረስ ተዘጋጅቼበታለሁ፡ ትናንትና ከተማርናቸው ወደ ተለያዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ወደ ኋላ ልመለስ እና እነዚህን ነገሮች ጎትቼ ማውጣት የምችልበትን፡ ትንሽ አውድ ጽፌአለሁ።

34 አሁንም፡ እንዳየነው፡ ትናንት ማታ ያቆምንበት፡ 2ኛው ቁጥር፡ ይመስለኛል፡ የ 3ኛው ቁጥር መጀመሪያ፡ ይመስለኛል። ያቆምነው “የመለከት ድምፅ” በሚለው ክፍል ነበር። “ድምጹ በሚሰማበት፡” በሚል አይደል የነበረው? አሁን እንመለሰበት ዘንድ ሁሉንም ላንብበው፡-

> **ከዚህ ነገር በኋላም አየሁ፡ እነሆም፡ በሰማይ፡ የተከፈተ ደጅ፥** እንደ **መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ፥ ወደዚህ ውጣና፡ ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያሰፈልገውን... ነገር; አሳይሃለሁ አለ።**

**ወዲያው፡ በመንፈስ ነበርሁ፥ እነሆም፡ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል፡ በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ።**

በዙፋኑ **የነበረውም... ተቀምጦ የነበረው በመልኩ... የኢያሰጲድንና... የሰርዲኖን ዕንቍ ይመስል ነበር፥ በመልኩም መረግድን** የመሰለ **ቀስተ ደመና፡ በዙፋኑ** ዙሪያ **ነበረ።**

35 አሁን፡ ይህ ትምህርት፡ ቆንጆ፡ በጣም ደስ የሚል ነው! እና ዛሬ ጠዋት፡ ገና ወደዚህ ከመውረዴ በፊት፡ ወደ 6ኛው ቁጥር ገባሁና፡ እንዲህ አሰብኩ፡ "ኦህ፡ ማይ፡ ይህን ማለፍ አልችልም፡ ምክንያቱም በዚህ በ6ኛው ቁጥር ውስጥ ወደ **እንስሶቹ** ስንደርስ፡ ህዝቡ ሁሉ በደንብ ሊሰማው የምፈልገው ነገር አለኝ። የእነዚህ እንስሶች የተለያዩ ትርጓሜዎች፡ ወደ ዋናው መለስ ብለው ሲመለከቱ፡ አንዱ አንድ የተለየ እንስሳ ነው፡ የቀሩትም አራቱ ራሳቸውን የቻሉ ሌላ እንስሶች ናቸው። አንደኛው የእንስሳ፡ በግሪክኛ፡ እንደ "ዱር እንስሳ" ነው። ይህ ሌላው በኪንግ ጀምስ ውስጥ በትክክል አልተተረጎመም፡ ምክንያቱም **እንስሶች** አይልም፡ "ህያዋን ፍጡራን" ይላቸዋል። እና እነዛ ፍጡራን፡ ምን ነበሩ፡ ሰው ወይም መልአክ አልነበረም። ስለዚህ "ሕያዋን ፍጡራን" ናቸው፡ ባለ አራት ፊቶች እና አራት... ኦህ፡ ማይ፡ ይህ በወንጌል ውስጥ ስንመለከተው፡ ወደ ኋላ መልሰን እንደ አቀማመጡ በትክክል መደርደር እንችላለን። እና፡ **አራት**፡ ምድራዊ ቁጥር እንደሆነ አስታውሱ። አያችሁ? ብቻ የሚያምር ትምህርት ነው፡ እና ወደዚያ እንደማንደርስ በጣም እ—እርግጠኛ ነኝ፡ ምናልባትም ልንደርስ እንችል ይሆናል። ግን በጣም ድንቅ ነው!

36 ከዚያም፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ቅርብ ከሆንን፡ ምናልባት በሚቀጥለው እሁድ እንደገና ያንን ልንሞክር እንችላለን፡ ብቻ፡ ከመሄዳችን በፊት፡ 4ኛው ምዕራፍ ለማጠናቀቅ እንሞክራለን። የመጀመሪያው ጅማሬ የት እንደሚሆን በትክክል አናውቅም።

37 አሁን፡ ያንን ከዚያ ነገር **በኋላ**፡ "ከእነዚህ ነገሮች በኋላ" ሆኖ እናገኘዋለን። **በኋላ** አባባሉ "የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ካለፉ በኋላ" ማለቱ ነው።

38 ከዚያም ዮሐንስ ወደ ላይ እንዲወጣ ተጠራ፡ "ወደዚህ ውጣ፡" ማለት "ወደዚህ ና።" በቤተ ክርስቲያን ዘመን—በዓለም ሊሆን ያለውን ነገር ሁሉ አሳየው። ከዚያም የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ካለፉ በኋላ፡ ዮሐንስ የእያንዳንዱ እውነተኛ አማኞች ምሳሌ ሆኖ እናገኘዋለን ይህም በክርስቶስ ወደ አርያም ይጠራል። ልክ ነው? ይጠራል፡ "ወደዚህ ውጣ" ይባላል።

39 እና እሱን ያነጋገረው ድምጽ የመለከት ድምፅ እንደሆነ እውቀናል፡ ግልጽ፡ ጥርት ያለ ነበረ፡ ድምጹም በምድርም እርሱን የተናገረው ያው ድምፅ ነበር። አያችሁ፡ በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል እስካለ ድረስ፡ ለ... ወይም **ከዚያ** ውስጥ ይናገራት ነበር። ኦህ፡ "ከመቅረዞቹ መካከል መናገሩ፡" በጣም ደስ ይለኛል። አያችሁ፡ በመቅረዙ ውስጥ ነበር፡ ከዚያም መካከል ሆኖ ለቤተክርስቲያን ይናገራታል። የቤተ ክርስቲያን ዘመን ካለፈ በኋላ፡ ምድርን ትቶ ወደ ሰማያት ዐረገ እናም የተቤዣቸውም ከእርሱ ጋር ጠራ። አቤት፡ ደስ አይልም? እ—እ... ኦህ፡ በቃ ልቤን ያዘልላል።

40 አስታውሱ፡ እነዚህ ነገሮች ሰናመጣ፡ በተለይ እንደነ እህት ዓና የመሳሰላችሁ አዳዲስ ክርስትያኖች፡ ማለቴ፡ እንደነ ዓይና፡ እና ባለቤቷ፡ ወይም፡ እነ ሮድኒ

እና—ሚስቱ፡ እነ ቻርሊ እና ሌሎችም፡ እና ገና ወደ ጌታ አሁን የመጣችሁ ወጣቶች፡ በዚህ መንገድ ጊዜ ያላስቆጠራችሁ ሁላችሁ፡ እርሱን ቀምሳችሁ መልካም እና ቸር መሆኑን ያያችሁ ሁላችሁ፡ እነዚህ ነገሮች እንድትረዱ እፈልጋችኋለሁ። እንግዲህ፡ ይህን አስተውሉ፡ የምንናገረው እነዚህ ነገሮች፡ ልናደርገው የምንሞክረው እምነታችሁን ለማረጋገጥ ነው። ይህም እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ሲናገር መፈጸም አለበት ነው። በቀላሉ አይወድቅም! ምንም… አንድ ሚሊዮን ማይል ያህል የራቀ… በጭራሽ የማይፈጸም ቢመስልም እንኳ፡ እግዚአብሔር ግን አዙሮ ያንቀሳቅሰዋል እንዲፈጸም ያደርገዋል። ይህንንም የሚያደርገው እናንተን ለመፈተን ነው።

41 ለአብርሃም የተናገረውን ተመልከቱ። “ልጅህን ወደዚህ ኮረብታው ውሰደው ግደለው፡” ለሃያ-አምስት ዓመታት ከጠበቀው በኋላ። “ወደ ላይ ወስደህ ግደለው፡” አለው። እንዴት ይሆናል… ? “እኔ የአሕዛብ አባት አደርግሃለሁ።”

42 አብርሃምም፡ የመቶ ዓመት ሰው፡ ሚስቱም፡ ዘጠና፥ አንድ ልጃቸውን… አብርሃም በዚያን ጊዜ መቶ አሥራ አምስት አመት ያህል ነበር። ስለዚህም እንዲህ አለ፡ “የሚሆነው እንዴት ነው፡ እንዴት—እንዴት ሊሆን ይችላል? እኔ፡ እንደ ሽምግልናዬ፡ እርጅቼ፡ ለሃያ-አምስት አመታት ከጠበቅኩ… በሰባ-አምስት አመቴ ላይ ቃል ኪዳን ገባህልኝ፡ እነሆ አሁን መቶ ሆኖኛል። ሳራም ስድሳ-አምስት ነበረች፡ አሁን ዘጠና ሆኗታል። እንዴት? ይህንን ልጅ ከወለድን በኋላ… የዛሬ ሃያ-አምስት ዓመት የሰባ-አምስት ዓመት ሰው ሳለሁ፡ ያኔ ነግረኸኝ ነበር፡ ይህን ሁሉ አመታት ከሳራ ጋር ከኖርን በኋላ እኔ መኻን ሆኜ ነበር እሷም መውለድ አትችልም ነበር፡ ያኔ ‘ይህን ልጅ ትወልዳለህ’ ብለኸኛል። ታዲያ እንዴት ነው? ደግሞም፡ እኔንም እሷንም መውለድ እንድንችል አድርገህ፡ መጣህና ይህን ልጅ ሰጥተኸናል። እኛም እስከ አስራ አምስት አመቱ ድረስ አሳድገነዋል፡ አንተም በዚህ ልጅ በኩል ‘አሕዛብ ሁሉ እና በዓለም ያሉትን ህዝቦች በሙሉ’ እባርካለሁ ብለሃል፡ እኔንም የአሕዛብ አባት አድርግሃለሁ አልከኝ፡ አባት አደረግከኝ። ከዚያም ጌታ ሆይ፡ ወደፊት ባሉ ዘመናት፡ በዚህ ሕፃን በኩል ከሰማይ በታች ላሉ አሕዛብ ሁሉ አባት ታደርገኝ ዘንድ ተናግረሃል። እናም በዚህ ልጅ በኩል ቤዛ ይመጣል፡ በዚያ ቤዛ በኩል መላውን የሰው ዘር ትቤዣለህ። ጌታ ሆይ፡ እንዴት ታደርገዋለህ? ” የአብርሃም ሃሳብ ያ አልነበረም፡ የአብርሃም ጥያቄ ያ አልነበረም። መታዘዝ! “እንዴት ታደርገዋለህ? ” አላለም፡

43 “ይህ ጉዳዬ አይደለም። አንተ ተናግረሃልና፡ አንተ ቃልህን ለእኔ እንዲህ ከጠበቅህ፡ ቃልህ እውነት እንደሆነ እኔ እውቃለሁ እና የሰባ-አምስት አመት ሰው ሆኜ ይህን ለእኔ ካሳየህ፥ አንተ በጠራኸኝ ጊዜ እንዲህ ባልከኝ ጊዜ፡ “ተለይተህ ወደማታውቀው ምድር ውጣ’ አልከኝ፡ እኔም ለሃያ-አምስት አመታት በዚህች ምድር ቆየሁ። ሰወጣ፡ ሽማግሌ ነበርኩ፡ ከልጅነቷ ጀምራ ከእኔ ጋር ከኖረች ሚስት ጋር ኖርኩኝ፡ እሷም በግማሽ እህቴ ነበረች። ከዚያም በዚህ ሁሉ ዘመን-… ኖርኩኝ። አንተም ቃል የገባህልኝ ልጅ ሰጠኸኝ፡ ከሙታን መካከል እንደመቀበል ተቀበልኩት። አሁንም ‘ግደለው’ ካልከኝ፡ ከሙታን መካከል ልታስነሣው እንደምትችል አምናለሁ።” ኦህ፡ ማይ! ይህ ነበር፡ ይኸው ነው። እሱም ታዘዘ።

44 እግዚአብሔርንም በሙላት እንደ ታዘዘ፡ የይስሐቅን ጠጉር ከፊቱ ሰብስብ አደረገ፡ የገዛ ልጁን፡ የወለደውን ልጅ፡ ለመግደል... ሰንጢውን አወጣ። እግዚአብሔር የሚያሳየ፡ በጥላ እያሳየን ነበር። ያንን ያደረገው ለምንድነው? ያን ማድረግ አይገባውም ነበር። ነገር ግን እኔና እናንተ፡ በእነዚህ አሰፈሪ እና ጨለማ በሆኑ ቀናት ይህን ማየት እንድንችል የሰዎችን ልብ በክፋት በተሞላበት በዚህ ዘመን፡ እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ እናውቅ ዘንድ ነው። ምንም ያህል በቂ ያልሆነ ቢመስልም፡ ምንም ያህል የማይቻል ቢሆንም፡ እግዚአብሔር አሁንም አምላክ ሆኖ ይኖራል የገባውንም ቃል ሁሉ ይጠብቃል።

45 በፈውስ አገልግሎት እዚህ ሰንቆም ልነግራችሁ የምሞክረው ይህንኑ ነው። እናንተ እዚህ ቆማችሁ፡ "ታምሜአለሁ፡" ትላላችሁ። ይኸውላችሁ... መታመማችሁ፡ ጥርጥር የለውም። እግዚአብሔር ግን ቃሉን ይጠብቃል! እንግዲያውስ እርሱ ይወርዳል። አሁን፡ እያችሁ፡ እንደሚፈውሳችሁ—እነሆ እዚህ ጋር ማስተሰረያ አደረገ። እሱ ያደረገው ይህንኑ ነው። አሁን፡ እንድታደርጉት የሚጠይቃችሁ ብቸኛው ነገር እንድታምኑ ብቻ ነው፡ ልክ እንደ አብራሃም አጥብቃችሁ ያዙት።

46 "እንዴ፡ ዶክተሩ እንደነገረኝ—አንድ ቀን ብቻ ትኖሪያለሽ ብሎኛል።"

47 አገደኝም። ምንም ይሁን፡ የሰውዬው እውቀት ያ ብቻ ነው፡ ትልቁ እውቀቱ ያ ነው። አብርሃም ይህን ሕፃን በዚህ ካጋደመው በኋላ ሊቀበለው እንዴት ይችላል፡ የእግዚአብሔር ቃል "ሄደህ ብላቴናውን ግደለው" ብሎት ሳለ እንዴት ይሆናል? እንዴት እንዴት ያደርገዋል? ጥያቄው ያ አልነበረም። እግዚአብሔር አድርግ ብሎታል አለቀ ደቀቀ። "ዶክተሩ መዳን እንደማልችል ተናግሮኛ ሳለ እኔ እንዴት እድናለሁ? " ይህ... ለእኔ አይመለከትም... ጥያቄዬ አይደለም፥ ይህ የእግዚአብሔር ቃልን ይጠይቃል። እና እንደምትፈወሱ በተገለጠላችሁ ቅጽበት፡ በቃ ያን ጊዜ—እንደምትፈወሱ ብቻ አሰቡ። ከዚያ ሊያግዳችሁ የሚችል አንዳች ነገር አይኖርም። በትክክል። እያችሁ?

48 ስለዚህ አብርሃም ሙሉ በሙሉ በታዘዘ ጊዜ... እንዴት ሊያደርገው ነበረ? የመጨረሻዋ ቅጽበት ላይ፡ የመጨረሻ አምስት ደቂቃዎች፡ የመጨረሻ ሶስት ደቂቃዎች፡ የመጨረሻ ሁለት ደቂቃዎች፡ የመጨረሻ አንድ ደቂቃ፡ የመጨረሻ ሰላሳ ሴኮንዶች፡ የመጨረሻ ሴኮንድ ደረሰች፡ የብላቴናውን ህይወት ለመውሰድ እጁን ባነሣ ጊዜ፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ "አሁን ይበቃሃል። አቁም፡ አየህ። በእውነት እንደምታምነኝ አይቻለሁ። አሁን፡ ይህን ያደረግሁት፡ አብርሃም ሆይ፡ በመጨዎቹ ዘመናት የብራንሃም ተበርናክል፡ ምን እንደሚሆን፡ ለማሳየት፡ እኔን ማመን ይችሉ ዘንድ ነው። በጭራሽ ሊጠራጠሩኝ አይገባም። እመነኝ!"

49 ያን ጊዜ፡ መሰዋዕቱም... እነሆ በአጠገቡ ነበረ፡ ጭራሽ በከንቱ አላደረገም። አይ፡ በጭራሽ በከንቱ አልነበረም፡ ምክንያቱ በጉ የጮኸው—ያን ጊዜ ነበርና፡ በምድረ በዳ አንድ አውራ በግ በቀንዶቹ ታስሮ ነበር። እኛም ይህ ነገር በተደጋጋሚ አይተነዋል። አውራው በግ ወደዚያ እንዴት መጣ? እነዚያ ሁሉ የዱር እንስሳት ባሉበት፡ እንዴት ሊሆን ቻለ? አንበሶች፡ ቀበሮዎች፡ ተኩላዎች፡ ሁሉም አይነት የዱር አራዊት ባሉበት፡ ከሰልጣኔ አንድ መቶ

ማይል በራቀ፡ ውሃና ሣር በሌለበት ተራራ አናት ላይ፡ ምን እያደረገ ነበር? እግዚአብሔር ፈጥሮ፡ በዚያ አስቀመጠው።

50 እኛ በምንኖርበት ዘመንም እርሱን ለማየት! አሁን፡ ዛሬ ጠዋት ይህን ለመናገር—ማለት የሚገባኝን ነገር ለማለት፡ የተለያዩ የግል ጉዳዮችን እዳስሳለሁ። ስለዚህ ገና ከመጀመሪ በፊት፡ ነገሩን በዚህ መልኩ ዳራ መስጠት ያስፈለገኝ ለዚህ ነው። እነዚህ ግላዊ የሚመስሉ ነገሮች፡ ግላዊ አለመሆናቸውን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ። የመጡበት ምክንያት እምነታችሁ በክርስቶስ ባለው እምነት ጸንቶ እንዲያርፍ ለእናንተ ምሳሌ እንዲሆኑ በማሰብ ብቻ ነው፡ በተሰፋው ቃል ላይ ትጸኑ ዘንድ ነው። ምክንያቱ አሁን እንደሚያሳየን፡ እግዚአብሔር በሚያስፈልገው መንገድ ሁሉ የገዛ ተሰፋ ቃሉ ይጠብቃልና።

51 እናንተም አብራሃም **ያሕዌ-ይርኤ፡** ብሎ የጠራውን ተመልከቱት፡ በዕብራይስጥ ትርጉሙ "እግዚአብሔር ለራሱ መሥዋዕት ያዘጋጃል" ማለት ነው። እግዚአብሔር ይህን ማድረግ ይችላል። በራሱ መንገድ ያደርጋል። ለምሳሌ... ኖህን አለው...

52 እናንተም "አይ፡ አብራሃምን ብቻ ነው፡" ትላላችሁ። አይደለም። በሁሉም ዘመናት ላይ ተናግሯል፡ አሁንም እየተናገረ ይገኛል።

53 ያኔ ድሮ ኖህን እንዲህ ተናገረው፡ ማለት፡ አሁን ወደዚህ ማለዳ እንደገባን፡ "እነሆ፡ ይዘንባል" አለው። ግን'ኮ ምንም አልነበረም... በሰማይ ላይ ደመና አልነበረም። ትልቁ የውሃ ጅረት እግዚአብሔር ምድርን የሚያጠጣበት፡ አንድ ቦታ ላይ ትንሽ ምንጭ ነበረ። ያኔ የነበረው ትልቁ የውኃ ምንጭ ያ ነበር።

54 እና፡ ሰዎች ይናገራሉ፡ "ኧረ እንደው እንዴትስ ቢሆን ውኃ ከሰማይ እንዴት ይወርዳል? እስቲ በዚያ በጠራራ ፀሐይ ውስጥ የት እንዳለ አሳየኝ፡ አንዳችም የሌለው ካልሆነ በቀር።"

55 "እግዚአብሔር 'ይዘንባልና፡ መርከብን ስራ፡' ካለ፡ ስለሚዘንብ፡ መርከብ የመስራት ኃላፊነት የእኔ ነው። እርሱ ያሕዌ-ይርኤ ነውና፡ ከዚያ ከላይ ማዘጋጀት ይችላል።"

56 እርሱ ያደረገው ብቸኛው ነገር ይህ ነው፡ ሊመጣ ያለውን የሚያውቀውን ይመጣ ዘንድ፡ ሞኙ፡ እና ቂሉ ሰው፡ በትክክል በሳይንስ እንዲሰራ አደረገው። እግዚአብሔር ዓለምን ፈጽሞ አላጠፋም፡ ሰው ግን ዓለምን አጠፋ። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለመጠበቅ ይሞክራል እንጂ፡ እግዚአብሔር ምንም አያጠፋም። ሰው በኤደን ገነት በዛፉ ላይ እንዳደረገው፡ እና በሌላ ነገር ሁሉ፡ በገዛ እውቀቱ እራሱን ያጠፋል። እናም አንዳንድ ወግ አጥባቂዎች፡ በሆነ ሰፍራ የያዙት፡ የአቶሚክ ሃይል ነበራቸው።

57 ያኔ ለሰራቸው ይጠቀሙበት—ነበር፡ ምክንያቱ እኛ ዛሬ ያልደረስንባቸው ነገሮች ያኔ መጠቀም ይችሉ ነበርና። እኛ ገና ያን ያህል ሰልጣኔ አልደረስንበትም። ምናልባት፡ ያኔ ያደረጉት ነገር ለማድረግ፡ ገና ሶስት አራት አመታት፡ ይቀሩን ይሆናል። እነርሱ ፒራሚዶችን እና ስፊኒክስን እና የመሳሰሉትን ሠርተዋል። ያንን ማድረግ በፍፁም አልቻልንም። ምናልባት የአቶሚክ ሃይል ሰናገኝ ካልሆነ በቀር፡ ያንን አይነት መሰራት አልቻልንም፡ የምንሰራበት ምንም መንገድ የለም። የነዳጅ ኃይል፡ እና የኤሌክትሪክ ኃይል፡ እነዚያን ድንጋዮች፡ ከመሬት የማንሣት አቅም የላቸውም። አንዳንዶቹም፡ ወደ

ላይ የአንድ ጎዳና ያህል ከፍታ ያላቸው፡ ቢልየን ቶኖች የሚመዝኑ ነበሩ። እንዴት ወደዚያ አደረሷቸው? አያችሁ፡ እውቀት ነበራቸው።

58 እና ያኔ በዚያ ዘመን፡ የሆነ አካል አቶሚክ ቦምብ ተኩሷል ያንን ነገር ወርውረዋል፡ ወደ ሌሎች ምሽግ አሰወንጭፏል፡ ምክንያቱ፡ "በኖኅ ዘመን እንደነበረ፡" እንደዚያ ዓይነት ሥልጣኔ፡ እነዚያን ዓይነት፡ ብልህ ሰዎች እንደነበሩ፥ "በኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ እንዲሁ ይሆናል፡ የሰው ልጅ በሚመጣ ጊዜ እንዲሁ ይሆናል።" ድሮ የነበረውን ይደገማል! አያችሁ?

59 በቅርብ ጊዜ እዚህ በሜክሲኮ አካባቢ፡ ከጥፋት ውኃ በፊት የተሰራ—ዘመናዊ የውኃ መስመር በቁፋሮ አግኝተዋል። አይታችሁታል? ጋዜጣ ላይ ወጥቷል፡ ከመሬት ወደ ታች እጅግ የጠለቀ፡ አሁን በዚህ ዘመን እንዳለው ዘመናዊ የውኃ ሰራዎች ዓይነት ነው፥ አቶሚካዊ የሆነ ነገር ሸፍኖታል። ያኔ በፍንዳታ እንዲሁ ጠፍታለች። አያችሁ?

60 አሁን፡ "በኖኅ ዘመን እንደነበረው፡" በእውቀት የላቁ ሰዎች፡ በአቶሚክ ኃይል እና በሌሎች ነገሮች የላቀ እውቀት ያላቸው ሰዎች ነበሩ፡ ፒራሚዶችን እና ስፊንክስን እና የመሳሰሉትን መገንባት ይችላሉ። "በዚያ ቀን እንደነበረው፡ እንዲሁ ይሆናል።" በዚህ ዘመን ግን ሰራው ቶሎ ይቋረጣል፡ በንጥቀት የሚወሰዱ ሰዎች ስለሚኖሩ። እንደ ሄኖክ፡ የሚወሰዱ ሰዎች አሉ። እኛም ዛሬ ጠዋት በዚያ ክፍል ውስጥ ያለነው፡ ኖህ በጎርፍ ከፍ እንደተደረገ የሚወሰዱ ህዝብ ነን።

61 ግን አስታውሱ፡ አስቀድሞ... ይህን አትርሱ! አንድ የዝናብ ጠብታ ከመውደቁ በፊት፡ በሰማይ ላይ አንዳች ነገር ሳይኖር፡ ኖኅ መርከቡን ገና—ሣይሰራ በፊት፡ ሄኖክ ወደ ቤት ተወሰደ። ሄኖክ ሳይሞት ተነጠቀ፡ አንድ ቀን መራመድ ጀመረ፡ እና—የመሬት ስህበት ሊይዘው አልቻለም። እና ራሱንም አንደኛው እግሩ ከፍ፡ እና ሌላኛው እግሩም ከፍ፡ ሌላኛውም ከፍ ማለት መጀመሩን ተገነዘበ፡ እና ይህ ሲሆን መጀመሪያ፡ "ቻው፡ ዓለም፡" ማለት ጀመረ። ወደ ክብር ተጓዘ አረገ።

62 ኖኅም ዘወር ብሎ ሲመለከት ሄኖክን ማየት አልቻለም፡ ዘወር ብሎ ተመለከተ ሄኖክ ወዴት እንደሄደም አላወቀም፡ ከዚያም "መርከቡን ለመሥራት ጊዜው አሁን ነው፡" አለ። አያችሁ? ቅሪቶችን ይዞ የሚወጣ መርከብ መስራት ጀመረ።

63 እዚህ የሚካሄደው ነገርም ተመሳሳይ ነገር ነው። ቤተክርስቲያን ወደ መንግሥተ ሰማያት ተወሰደች፡ አሁንም ዮሐንስ ደግሞ ትናንትና ማታ እንደተማርነው፡ ከሙታን የተነሡትን ጥላ ነው። ወደ ምድር መለስ ብሎ እንዲመለከት የጠራው ይኸው ድምፅ፡ ወደ ላይ እንዲወጣ የጠራው ያው ድምፅ መሆኑን ተረድቷል።

64 ኦህ፡ ክርስቲያን ሁሉ! ቻርሊ ሆይ፡ በኬንታኪ ውስጥ አንድ ቀን "ወደ ኋላህ ዙር፡" በማለት የጠራህ፡ ያው ድምጽ፡ "ወደ ላይ ውጣ!" በማለት የሚጠራህ ያው ድምጽ ነው፡ ወንድም ኢቫንስ ሆይ፡ በዚህ ደስ አይልህምን? "ወደ ኋላህ ዙር፡" ያለህ፡ ያው ድምጽ "ወደ ላይ ውጣ!" የሚል እርሱ ነው፡ ኦህ፡ ማይ! ይኸው፡ እንዴት ያለ ጥሪ ነው! እንዴት ያለ እውነታ ነው! ግልጽ፡ እንደ መለከት የነጠረ፡ "ወደ ኋላህ ዙርና፡ አገልግለኝ! እኔ ወዳለሁበት ውጣ።"

65 ሙሴ በዚያም የሞቱትን ጥላ ሲሆን፡ የሞቱ ቅዱሳንን ጥላ ሆኖ፡ ሲነሣ አይተነዋል። ኤልያስ፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከተነጠቁት ቡድኑ ጋር በዚያ ቆመ። ሁሉም በጌታ በኢየሱስ ፊት ነበሩ! ዮሐንስ ይህን ገለጠው... ኢየሱስም እሱ አይሞትም—በማለት ነገራቸው፡ ምጽአቱን እስኪያይ ድረስ በሕይወት ቢኖር ምን አገባቸው። ደቀ መዛሙርቱም ነገር ተናገሩ።

66 ኦህ፡ አሁን እንደው ለጥቂት ደቂቃዎች፡ በደንብ፡ በደንብ ጠለቅ ብዬ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ብገባ ደስ ይለኛል። ሁሉም ያውቃል... እና ሁሉም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የግል ሕይወቱ ይ—ይኖራል። ለመናገር እንኳን የማትደፍሯቸው ነገሮች ላይ የሚያስገባችሁ መንፈሳዊ ነገር፡ የግል ጉዳይ ነው።

67 ይህንን በራሴ ትንሿ፡ እና ተራዋ አገልግሎቴ ላይ አስተውያለሁ፡ ብዙ ጊዜ አንድ ነገር እናገራለሁ ለምን እንዳልኩት እንኳ አላውቅም፡ እና ትክክል አይመስልም (ነገር ግን ደግሞ፡ የሆነ ሰው ይናገራል።)፡ ከዚያ በኋላ ዝም ብዬ እጠብቀዋለሁ እና በተገቢ መልኩ በፍጹም ይሆናል። እግዚአብሔር ያደርገዋል! አንድ ነገር ለማለት ስፈልግ፡ እንዲህ እላለሁ፡ "እሺ፡ አሁን፡ አንድ ደቂቃ ቆይ። **እከሌ-እና-እከሌ**፡ የተባለው **ሰው**፡ እዚህ ላይ እንዲህ ይሆናል እላለሁ፡ አሁን ያ—እንደተባለው ይሆናል።" እንግዲህ፡ ስለ እውነት፡ ለምን እንደዚያ እንደተናገርኩ እኔ አ—አላውቅም። ከሁሉ በላይ ግን፡ እንደተባለ ሲፈጸም ታያላችሁ። እግዚአብሔር ያደርገዋል!

68 እንግዲህ፡ እነዚያ ደቀ መዛሙርት፡ "ኦህ፡ ኢየሱስ 'ይህ ሰው አይሞትም' ብሏል" ብለው ተናገሩ። ኢየሱስ ግን እንደዚያ አላለም።

ኢየሱስ ያለው፡ "እኔ እስክመጣ ድረስ ቢኖር አንተ ምን አግዶሃል? "

69 ደቀ መዛሙርቱ በዚያ ላይ ወሬ እንዳወሩ ባየ ጊዜ፡ ኢየሱስ ዮሐንስን ወሰደው እና ነገርን ሁሉ እንደ ቅድመ እይታ ለማሳየት አመጣው፡ የጌታን መምጣት ቅድመ እይታ በደንብ አይቷል። ዮሐንስ ቤተክርስቲያንን አይቷል፡ የቤተክርስቲያንን ዘመን መጨረሻ አየ፡ የአይሁድን ፍጻሜ አይቷል፡ የዳግም ምጽአቱን አይቷል፡ ሥርዓትን ሁሉ አየ።

70 እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደነበረበት ተመልከቱ፥ ለሃያ-አራት ሰዓታት ያህል በፈላ ዘይት ውስጥ ጣለው፡ አ—አፈር-ከመሆን፡ በመለኮታዊ መንፈስ የተቀባ መለኮታዊ መሆኑን ለማሳየት... (ውጫዊው፡ አፈር-መሆን፡ ወይም ምንም ብላችሁ ጥሩት፡ የሰው አካሉ)፡ በፈላ ዘይት ውስጥ ለሃያ-አራት ሰአት ቢቆይም ጫፉንም እንኳ እስከማይነካው ድረስ እንዳልተጎዳ መለኮታዊ አድናቆት አሳየ። በፈላ ዘይት ቀቅለው ያን መንፈስ ቅዱስን ከሰው ለማስወጣት መኮሩ፡ አልቻሉም። ከዚያም ወደ ፍጥሞ ደሴት አወረዱት፡ መጽሐፉንም ጻፈና፡ ከዚያ ወጥቶ ብዙ ዓመታት ሰበከ። እህም። እህም።

71 እርግጥ ነው፡ መቼም፡ መጥፎ ስም መስጠቱ የማይቀር ነበረ፡ "ጠንቋይ፡ መተተኛ ይባል ነበርና።" ዮሐንስ ጠንቋይ መባሉን ስንቶች ታውቃላችሁ? በትክክል! ኢየሱስም፡ ተብሏል። አያችሁ? ተመልከቱ፡ ዓለም ስለ እነዚህ ነገሮች ምንም የሚያውቀው ነገር የለም፡ "እእምሮ አንባቢ ይሉታል።" አያችሁ? እንዲህ አሉት "ቅባቱ እንዳይጎዳው አድርጎ ጠንቁሎበታል፡ እንዲህ ያለ ከባድ ጠንቋይ ነበር ይሉታል፡" ችግራቸው በካቶሊካዊ አሳባቸው ስላልተስማማ ብቻ ነው። ያ ብቻ ነው።

72 ይህ ትሑት፡ የእግዚአብሔር ባርያ… ጠብቆ ያቆያት አነስተኛ ተልዕኮ ነበረችው። እነዚያን ታላላቅ ነገሮች መታገስ አልቻለም፡ እግዚአብሔርም ግን ጠበቀው አቆየው። ለእነ ማርቲን እና—ኢራኔዎስ፡ በዘመናት ሁሉ ለነበሩ ሁሉ ጭምር፥ እንዲሁ አደረገላቸው።

73 አሁንም ተመሳሳይ ነገር እያደረገ፡ ዛሬም ቀጥሎበታል። አሁን፡ እግዚአብሔር ታላቅ መናወጥ፡ እና ታላቅ ተአምራትን እንደሚሆን፡ ቃል መግባቱን፡ ፈጽማችሁ አትርሱ። አሁን፡ እየጻፋችሁ ባለው ማስታወሻችሁ ላይ ይህንን ፃፉ (ተመልከቱ። እያችሁ? )፡ ሰው "ታላቅ እና ኃይለኛ" የሚለው ነገር፡ በእግዚአብሔር ፊት "ሰንፍና" ነው! ሰው "ሰንፍና" የሚለውም፡ እግዚአብሔር "ታላቅ" ይለዋል! ይሄን አትርሱ፡ እያችሁ፡ እንዳትረሱት። ይህ በሚቀጥሉት አመታት ውስጥ አንዳች ነገር ለመረዳት ያግዛችኋል፡ ምክንያቱም ሁልጊዜ የበለጠ ነገር እየፈለግን እንቀጥላለንና። እንዲሁ ደግሞ ታላላቅ ነገሮች እየተቀበልን እንገኛለን፡ የዓለም ሰዎች ግን ገና አላወቁትም። በኖኅ ዘመንም አላወቁትም፡ በዘመነ ዮሐንስም አላወቁትም፡ በኢየሱስ ዘመን፡ በሐዋርያቱ ዘመን፡ በኢራኔዎስ ዘመን፡ በማናቸውም ዘመን፡ ፈጽመው አላወቁትም።

74 አርካዊት ጆአን እንኳን፡ የተቀደሰች፡ ምስኪን ሴት ነበረች። ምንም የሌላት ልጃገረድ በነበረች ጊዜ፡ እግዚአብሔር በራእይ ይናገራት ነበር፡ መላእክትም ይናገሯት ነበር። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግን ምን እንዳለቻት ታውቃላችሁ? "ጠንቋይ ነች አለች።" እና በእንጨት ላይ አሰረው በእሳት አቃጠሏት፡ ይህን ያደረጉት የካቶሊክ ቀሳውስት ናቸው፥ ገደሏት፡ "ጠንቋይ ናት" በማለት ሞት ፈረዱባት፡ አርካዊቷ ጆአን ጠንቋይ ተብላ ሞተች። ከሁለት መቶ ዓመታት ገደማ በኋላ፡ ጠንቋይ አለመሆኗን አወቁ፡ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ነ—ነበረችና።

75 በቅዱሳን ሁሉ ላይ እንዲሁ አደረጉ። ኢየሱስም፡ "ከእናንተ አባቶቻችሁ ያላሳደዱት ማን ነው? ከነቢያት መካከል እምቢ ያላሉት የትኛው ነው? " "እናንተ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮች፡" አላቸው። እንዲህ አላቸው፡ "እናንተ—እናንተ እየተነሣችሁ—የነቢያትን መቃብር የምታስጌጡ፡ ወደ መቃብር ያወረዳችኋቸው እናንተ ራሳችሁ ናችሁ።" እህም! አቤት! አቤት! እያችሁ? ቡጢ ልምታችሁ አላለም። እህም! እንዲሁ ብቻ ተናገራቸው።

76 "እናንተ የእፉኝት ልጆች፡" አለ ዮሐንስም፡ "ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አስጠነቀቃችሁ? አብራሃም አባት አለን አትበሉ።" "የትልቁ ድርጅት፡ አባል ነን።"

"ክርስቲያን ነህ? "

77 "እንዴ፡ ሜቶዲስት ነኝ። ፕረስባይቴሪያን ነኝ። እኔ ጴንጤቆስጤ ነኝ።" ይህ ሁሉ በዚያ በጭራሽ የለም። ጸሐይ በረዶ ላይ ከሚያደርገው የ—የ—የ—የ—የዘለለ ልዩ ትርጉም የለውም። እያችሁ? ምንም ትርጉም የለውም። ክርስቲያን ከሆናችሁ፡ ዳግመኛ-የተወለደ የእግዚአብሔር ባርያ ናችሁ።

78 አሁን፡ አሁን፡ ዮሐንስ በመጣ ጊዜ፡ ትናንት ማታ አይተነዋል። አሁን፡ አስታውሱ፡ ወደዚህ ስትመጡ… ስለዚህ ነገር ስለ አውዱ፡ እንዲህ እ—እላችኋለሁ። አሁንም ዓለም፡ ዓለማዊቷ ቤተክርስቲያን፡ በፊት ከገጠማት የላቀ መናወጥ እየገጠማት እንደሆነ፡ አትርሱ።

79 አሁን፡ አስታውሱ፡ በ—በዮሐንስ ዘመን፡ በኢየሱስ ዘመን፡ በዘመናቸው፡ ታላላቅ በዓላትና ታላላቅ ተናጋሪዎች፡ ታላላቅ ምሁራን መኖራቸው አያጠራጥርም፡ እና በአስር ሺህ ጊዜ በሺዎች የሚቆጠሩ የሰዎችን ልብ ያሸፍቱ ነበር። ቀያፋ ሰብሰባ ሲጠራ ምን—ዓይነት አቅም ነበረው? መላ ኢየሩሳሌም፡ እና መላ እስራኤል፡ ከጥግ እስከ ጥግ ድረስ መጥራት ይችል ነበር። ሁሉም በአንድነት እንዲህ ይሉለታል፡ "ኦህ፡"

"እንደው፡ ቀያፋ **አንድ-አንድ** ነገሮች ቢናገር፡ ደስ ይላል።"

"ኦህ፡ ራባይ፡ ሬቨረንድ፡ ዶክተር፡ ቢሾፕ ሆይ፡ መጻሕፍትን ታምናለህን? ቅዱሳት መጻሕፍትን ታምናለህን? "

"ያል ጥርጥር፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን አምናለሁ፡ እኔ'ኮ ታዋቂ ምሁር ነኝ!"

80 "መልካም። አሁን፡ እዚህ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ በሚመጣ ዘመን ላይ እንዲህ ይሆናል ይላል፡ 'ተራሮች ሁሉ እንደ አውራ በጎች ይዘላሉ፡ ቅጠሎቹ ሁሉ ያጨበጭባሉ፡ ኮረብቶች ዝቅ ይላሉ፡ ሸለቆዎችም ከፍ ከፍ ይደረጋሉ። ይህም ሁሉ ድምጹን በምድረበዳ በሚያሰማ ሰው የሚፈጸም ይሆናል።' ይህን ታምናለህ፡ ራባይ፡ ሬቨረንድ፡ ዶክተር፡ ፓስተር? "

"በትክክል፡ አምናለሁ!"

"እንዴት ይሆናል? "

81 "እነሆ፡ እግዚአብሔር አንድ ቀን ኃያል ሰው ወደ ምድር ይልካል። እነሆ፡ እርሱም ታላቅ ይሆናል። እርሱ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ይሆናል፡ ወይም የመሲሕ መምጣት ያበስራል። እና ሲመጣ፡ ከሰማይ ወደ ቤተ መቅደስ እንደሚወርድ በአእምሮዬ ምንም ጥርጥር የለኝም። ወደዚህ ወደ ቤተ መቅደሱ ይወርዳል፡ ከዚያም እንዲህ ይላል፡ 'አሁን፡ ሮማውያን በሙሉ እንይዛቸዋለን እንገድላቸዋለን። በቃ። ሮማውያንን በሙሉ እናሸንፋቸዋለን።' ያን ጊዜም— እንዲህ ይላል፡ 'መሲሕ ሆይ፡ ና ውረድ!' መሲሕም ያን ጊዜ ይወርዳል፡ እኛም ማጭዶቻችንን ወደ ሌላ ነገር እናስተካክለዋለን... ማለት ሰይፎቻችንን ማረሻ እናደርጋለን፡ ከዚያ በኋላ ጦርነት አይሆንም።" እና፡ ወይ-ጉድ፡ የራሳቸው ትርጉም ይህ ነው።

82 በመጣ ጊዜ ግን ምን ተፈጠረ? ምን ሆነ? እነርሱ አይተናል የሚሉት፡ ሰማያዊ ትዕይንት አልነበረም፥ አላዩትም እንጂ፡ አንድ ነገር ግን ሆኗል። አላዩትም። አያችሁ። ተራሮች ሁሉ እንደ ጠቦቶች መቼ ዘለሉ? ኮረብቶች መቼ ዝቅ አሉ ሸለቆዎቹስ መች ከፍ ከፍ አሉ? ገና ሀሁን በትክክል ያልቆጠረ ፊተ-ዘናና የሆነ ሰው ከምድረ በዳ እየተራመደ መጣ። ታሪክ እንደሚለው፡ በዘጠኝ ዓመቱ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ እስከ ሠላሳ ዓመቱ ድረስ እንደገና አልተገለጠም። ምግቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበረ። አንበጣ ማለት፡ ረጃጅሞቹ አንበጦች ናቸው።

83 ሁሌም ይመገቧቸዋል። እንግዲህ፡ እዚህ ጋር ይሸጣሉ... መጥፎ ነገር እንዳይመስላችሁ፡ ከፈለጋችሁ ከዚያ ከሱፐርማርኬት መግዛት ትችላላችሁ፡ ባምብልቢስ፡ ንቦች፡ አንበጣዎች፡ ራትልስኔክስ፡ የፈለጋችሁት ሁሉ፡ ታገኛላችሁ።

84 ስለዚህ ምግቡ አንበጣ እና የበረሃ ማር ነበረ። ምን የሚሉት አመጋገብ ነው! እሱ ግን በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቆ ነበር። ትናንት ማታ የሆነ ሰው እንዳለ፡ ወንድም ፓርኔል ወይም ሌላ ሰው እንደተናገረ፥ አንገትጌው አዙሮ አልለበሰም። ፍሮክ-ቴይል ኮት፡ እና ሌላው ነገሮች አልለበሰም። አንድ ትልቅ ያረጀ የበግ ቆዳ ሰውነቱ ላይ ጠቅልሎ፡ ከምድረ በዳ ወጣ። እንዳልኩትም፡ ምናልባት... እኛ በየቀኑ ገላችንን እንታጠባለን፡ እና ምናልባት በዚያ በምድረ በዳ፡ በየሦስት ወይም በአራት ወሩ አንድም ጊዜም አይታጠብም ይሆናል። እንጃ። ሲያዩት የሚሰብ አልነበረም። ፑልቢትም አልነበረውም። ወደ ትልልቅ ከተሞች በመሄድ ታላላቅ ኮንፈረንሶችን አላዘጋጀም። ጭቃ እስከ ጉልበቱ ድረስ ተመርጎ፡ በዮርዳኖች ዳርቻ ቆመ፡ እና እንዲህ አለ፡ “እናንተ የእፉኚት ልጆች፡ ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሹ ማን አስጠነቀቃችሁ? ” እህም። ኮረብቶች ዝቅ ያሉት፡ አያችሁ፡ ሸለቆዎችም ከፍ ያሉት ያኔ ነበር። ወይ-ጉድ። አዎን፡ ወዳጄ።

85 እና፡ ከሁሉ በፊት ሲጠባበቁት የነበረው ነገር፡ መሲሕ ከመላእክትና ከነገሮች ጋር ይወርዳል ብለው እየጠበቁ፡ እሱ እንዲመጣበት አሰበው በሠሩት ቤተ መቅደስ ጣሪያዎች ላይ ይወጣሉ (ዛሬ በመላ አገሪቱ ላይ እና በሌላ ስፍራ እንደገነባናቸው ታላላቅ ቤቶች አይነት)። አያችሁ? እና መቼ መጣ? ሙክራቦች ሁሉ አለፋቸው፡ ድርጅቶች ሁሉ አልፎ፡ ወደ አንድ በረት መጣ። ወደዚያ አስገደዱት።

86 ዛሬም ያው ነው። ወደ ነገሮች ያስገድዱታል፡ እንዲያደርግ ያስገድዱታል፡ በቤተ እምነቶች መካከል ለመሆን ያስገድዱታል፡ ምክንያቱም መልእክቱ ከሐይማኖት ተቋም ጋር አይስማማም። የሐይማኖት ተቋማት አስወጥተውታልና፡ ዛሬ በአገልጋዮቹ የሚሰበከው መልእክት፡ ለሁሉም ቤተ እምነቶች ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ይመሰክራል። በገዛ ቤተ ክርስቲያኑ፡ ለመግባት እየፈለገ (አያችሁ? )፡ ከውጭ ቆሞ፡ ያንኳኳል። ዛሬም ያው ነው። አያችሁ፡ እዚያ ላይ ነው።

87 ስለዚህ፡ አስታውሱ፡ ለሰው ትልቅ የሚመስለው፡ በእግዚአብሔር ፊት ትንሽ ነው። አሁንም፡ እናንተም ብዙ አበቦች የሌላችሁ ምክንያቱ ይህ ነው። አሁንም እግዚአብሔር እንደገና ሲመጣ፡ ኢየሱስ እንደገና ሲመጣ፡ ትደነግጣላችሁ፡ ጎዳናው ላይ ካለች ልብስ አጣቢ በቀር። ወይ-ጉድ። ከዝምተኛው ሰውዬ በቀር፡ ሌሎቻችሁ ትደነግጣላችሁ፡ ምሥጢሩን በእግዚአብሔር ፊት ለራሱ እየጠበቀ ከሚኖር፡ ትሑት ሰው በቀር። ትደነግጣላችሁ። በርግጥ-...

88 በቅርብ ጊዜ አንድ ሰብከት ሰብኬ ነበር፡ በፍርድ ወቅት... **በፍርድ ወቅት የሚፈጸሙ አስደንጋጭ ነገሮች።** መጠጥ ሻጩ ወደዚያ መግባቱ አስቀድሞ ያውቃልና፡ አይደነግጥም። በትክክል። ውሸታሙን፡ አመንዝራውን ሁሉ፡ ወደዚያ መግባቱ፡ አይደነግጥም። ድንጋጤ፡ እና ብስጭት የሚሆነው ግን፡ እንገባለን ብለው አሰበው ለነበሩ፥ ጉድ-ነው፡ አዎን፡ በኋላ ግን ለተጣሉ ላይ ነው። እንዲህ ሲሉ የነበሩ፡ “እንዴ፡ ተው እንጂ፡ እናቴ'ኮ የቤተክርስቲያን ሰው ነች፡ አባቴ'ኮ የቤተክርስቲያን ሰው ነው፡ ወንዱ አያቴ እና ሴት አያቴ። ዘመኔ ሁሉ የእነዚያ አባል ሆኜ ኖርኩ ባዮች።”

89 እናንተ አመጸኞች፡ ከእኔ ራቁ፡ እኔ አላውቃችሁም።“

90 ያን ጊዜ የነበረው፡ ምስኪኑ፡ በማንም የማይታወቅ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለሱ አንዳች የማናውቅ፡ ሽማግሌው ስምዖንን ተመልከቱት። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ አለ፡ “በመንፈስ ቅዱስም ተገለጠለት፡” (እያችሁ፡ ይኸውላችሁ።) “ጌታ የሆነው ክርስቶስ—እስኪያይ ድረስ እንደማይሞት ተረዳ።”

91 እንግዲያውስ መጥምቁ ዮሐንስ ማን እንደ ነበረ ተመልከቱ፡ በጫካ ውስጥ የሚኖር፡ እንግዳ-አይነት ሰው ነበረ። ለእርሱም ተገለጠለት። እርሱም መልእክቱን እየሰበከ ወጣ። እስቲ ተመልከቱ!

ምስኪኗ ሃና ማን ነበረች?

92 ምስኪኗ ድንግል፡ ማርያም፡ በ—በናዝሬት ከተማ የምትኖር (ማለት እንደ ጀፈርሰንቪል) ኃጢአትና ሁሉም ነገር በበዛበት ከተማ፡ አንድ ቀን የሚመጣ መሲሕ እንዳለ ሰላወቀች ግን ራሷን በንጽሕና ጠብቃ አቆየች። አያችሁ?

93 አናጺ፡ የነበረው ዮሴፍ፡ ሚስቱ የሞተችበት ሰው—ይህች ምስኪን ሴት እጮኛው አርጓት ነበር። መንፈስ ቅዱስ ወደዚያ የመጣውም በዚያ መንገድ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ዓለም ይመጣና ስሙን-ያጠለሻል “ጴንጤቆስጤ፡ ወንበር-ሰባሪ፡” በማለት ይሳደባል። አያችሁ፡ ስሙን-ያጠለሻሉ። “እንዴ፡ ያ፡ እሷ’ኮ... ያ’ኮ ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ልጅ ነው።” አያችሁ፡ እንደዚያ ብለው ሰላመኑ፡ እውነት መሰለ። እግዚአብሔር ግን ያንን ያደረገው ጥበበኞችን እና አስተዋዮችን ያሳውር ዘንድ፡ እና መማር ለሚፈልጉ ለህጻናት ይገልጥላቸው ዘንድ ነው።

94 ከአፍታ በኋላ ለማደርገው ነገር በቂ ዳራ እንዳስቀመጥኩ ተስፋ አደርጋለሁ። አሳያችኋለሁ። ይህን ዘይት ታያላችሁን? አሁን፡ እኔ የነገርኳችሁ፡ ዳራው፡ እግዚአብሔር እንጂ፡ ሰው አለመሆኑን ለማየት፡ **ወደዚህ** እጠቁማለሁ። በጣም ጥሩ።

95 አሁን ድምጹ፡ “ወደዚህ ውጣ፡” የሚል ነበር። እና በከፈተው ጊዜ እነሆ የመለከት ድምጽ ሰማ፡ ያን ጊዜ ዮሐንስ በመንፈስ ነበረ—በመንፈስ ነበረ፡ በመንፈስ በሆነ ቅጽበት ነገሮችን ማየት ጀመረ። በመንፈስ ስትሆኑ ነገሮችን ማየት ትጀምራላችሁ። በመጀመሪያ በመንፈስ መሆን አለባችሁ። ልክ ነው?

96 ለምሳሌ፡ “ቤዝ ቦል እወዳለሁ፡” ብላችሁ፡ ወደ ኳስ ጨዋታ ብትሄዱና። አሃ-ህም። እና የቦክስ መቀመጫ ባለበት፡ ፊተኛው-ረድፍ ላይ ተቀምጠህ ያንኪስ ወይም ቡልዶግስ፡ ማንም ይሁን ማን፡ ጨዋታ ላይ ያለውን ለማየት ተገኝተሃል። እና ሁሉም ግሩም ጨዋታ እያደረጉ ነው።

97 እና አንተ የምትደግፈው ቡድን ሊሸነፍ ሆነ፡ ድንገት ግን ዘመናዊው ቤቤ ሩት ኳሱን **እንዲህ** ወርውሮ፡ “እዚያ ማዶ ይታይሃል? ” ሶስቱም ቤዙ ጋር ናቸው። “ዋሚይ!” ብሎ ከእይታ ውጪ ያበራታል፥ ከዚያ ኮፍያውን ያወልቃል እራሱን ያቀዘቅዛል፥ በመጀመሪያው ቤዝ ላይ ይራመዳል፡ ዙሪያውን ይቃኛል፡ ወንዶቹ ሁሉ፡ ወደ ሁለተኛው ቤዝ በመሄድ ከሁለተኛው ቤዝማን ጋር እጃቸውን ይጨባበጣሉ፡ ተራምዶ፡ በፍጥነት በመራመድ ሆም ይደርሳል፡ ጎንበስ ይላል... ከዚያስ፡ ማይ! ማይ! ጩኸቱ፡ መዝለሉ፡ ጫጫታው፡ ድምጹ፡ “ሆታው!” ድርጊታቸው፡ እንዴት ነው...

98 በእውነት ይህ ሁሉ ሲያደርጉ አይቼ አውቃለሁ... የድሮ የገለባ ኮፍያ ታስታውሳላችሁ? አንድ ቀን ወደ ቤዝቦል ጨዋታ ሄድኩና ሰውዬው ሆም ራን ውጤት ሲያስመዘግብ አየሁ። እና የገለባ ባርኔጣ ያጠለቀ ከፊቴ የነበረ ይህ ሰው፡ እጅግ ደስ አለው፥ ኮፍያውን ሳብ አርጎ አወረደና፡ ከዚያ ከላይ በተገለጠው በኩል ኮሌታ ነገር **እንዲህ** ጣል አደረገበት። ታዲያስ፡ በቃ ልዩ ጊዜ እያሳለፈ ነበር! በ—በራሱ ዓለም ነበር የሚያደርገውን እንኳ አያውቅም ነበር። ተራገጠ ሆይ ሆይ አለ ጮኸ እንዲሁም ዘለለ። እንግዲህ፡ አሁን፡ ምን አሰቤ እንደነበረ አውቃችኋል፡ እርግጥ ነው... እርሱ-... እሱ እንደሆነ... ቤዝቦልን ይወዳል። ይህ ማለት ልክ እንደ ሲጋራ ሱሰኛ ወይም እንደ ዊስኪ ሱሰኛ፡ የቤዝቦል ሱሰኛ ነበረ ማለት።

99 እኔ ግን የኢየሱስ ሱሰኛ ነኝ። አዎ። በቃ ደስ ይለኛል። የኢየሱስ ሱሰኛ ከ... ከሆንክ፡ አየህ፡ በሆነ ነገር ሱሰኛ መሆን ነው።

100 እንግዲህስ ያ ሰው "ኦህ፡ እርግጥ ነው፡ እኔ የቤዝቦል ሱሰኛ ነኝ፡" ሲል አሰቡት። እና የሚደግፈው ወገን ሊሸነፍ ተቃርቦ የነበረ፡ ጨዋታውን እንዲህ ሲያሸንፉ አይቶ፡ ዙርያውን እንዲህ ያይና፡ "ይመስለኛል፡ ይህ ልክ ነው።" ኸሃ-ሃህ። "ቤዝቦል እወዳለሁ፡" ይላል'ዴ።

"ኦህ፡ እንግዳ ነገር ነው!"

101 እናንተም እንዲህ ባላችሁ ነበር፡ "ታዲያስ፡ አልተመቸህም፡ አይደል? ይሆን ችግር እማ አለብህ!" የቤዝቦል ወዳጅ የሆነ ማንኛውም ሰው፡ "ይህ ሰው ምን ነካው? ችግር አለበት መሰለኝ። ተመልከቱት ቁጭ እንዳለ ነው" ባለው ነበር። እንዴ! ትክክል ነው...

102 እስኪ አሁን ሁለት ለሁለት አንድ ላይ አድርጉልኝ፡ እሺ። አቤት፡ የኢየሱስ ሱሰኛ ስትሆኑ፡ መንፈስ ቅዱስ በእነዚያ ቃሎች ሲሰምጥ ስታዩት፡ የሆነ ነገራችሁ ይጮኻል! አቤት፡ ከቁጥጥር ውጪ ትሆናላችሁ!

103 ይህ እዚ ጠጋ ብሎ የተቀመጠ ሰው፡ ይቅር እንዲለኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ እዚህ ጋር የተቀመጠው፡ ባለ ጥቁር-ጸጉር ረጅም እና ግዙፍ ሰው፡ አንድ ቀን ማታ እዚህ አዳራሽ ውስጥ ቆሞ ሳለ፡ አንድ ሰው የሆነ ነገር አይነት ነገር ተናገረው... ማለት፡ ታውቃላችሁ፡ የሆነ ባረከው። ያኔ ይህ ምስኪን ሰው ከባድ ጊዜ እያሳለፈ ነበር፡ ሚስቱ ትታው—ሄደች እና ጌታ ኢየሱስን በመውደዱ ሕግ ፊት ከሰሰችው። እውነት ነው። እና የሆነ ሰው ስለ ኢየሱስ ተናገረ፡ ታውቃላችሁ፡ እሱም ከሱሰኞቹ መካከል አንዱ ነው። እና አውደ ውጊያ ላይ የነበረ ብዙ ቦታ የተወጋ፡ ወዘተረፈ ነው፡ እና ይህ ሰው፥ በጣም አዘነለት። እና ወደቤቱ መጣና... ወደ ሚስቱ ወደ ልጆቹ። ከዚያ በ—በኋላ አገለግልሃለሁ በማለት በጌታ ፊት ቃል ገባ፡ እና በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ መሆን በጀመረ እና ጌታም እርሱን መባረክ በጀመረ ጊዜ፡ ሚስቱ ዞር ብላ፡ ለፍቺ ከሰሰችው ትታውም ሄደች። ብርድ ላይ ጥላው ወጣች። ነገር ግን አሁንም ሱሰኛው ነበረ።

104 እናም አንድ ቀን ማታ ላይ በዚያ ቆሞ ሳለ አንድ ሰው ስለ ኢየሱስ የሆነ ነገር ተናገረ፡ የሆነ ነገር አለ፡ እንዴት ድንቅ እንደሆነ፡ አይነት ነገር ተናገረ፡ እሱም "ኦህ፡ ክብር ይሁን!" አለና፡ ክንዶቹን እንዲህ ወርውሮ በቡጢ ግድግዳውን እንዲህ ቦደሰው። እንደዚያ ማድረጉም አላወቀም። እጁን እንደጨበጠ ግድግዳው ውስጥ ተቀረቀረ። ከዚያ "ወንድም ቢል፡ ዕዳውን እከፍላለሁ፡" አለኝ። ከዚያ

በኋላ ወንድም ዉድ መጥቶ ቆርጦ ለጠፈበት፡ ሌላ ቁራጭ ለጠፈበት። ወንድም ቤን፡ አይዞህ ምንም አልመሰለንም፡ ሱሰኛው በመሆንህ ደሰ—ብሎናል። አየህ?

105 መንፈሰ ቅዱሰ አንድ ነገር ሲያደርግልህ፡ ዝም ብለህ መቀመጥ አትችልም፡ የሆነ ነገር ይፈልቅብሃል። አሜን። አቤት! አዎን፡ አንዳች ነገር ይይዝሃል፡ የክርሰቶሰ ሱሰኛ። ጌታን ሰትወደው በውሰጥህ የሆነ ነገር ለመያዝ፡ ለመጨበጥ፡ ይራባል፡ ይጠማል። ኢየሱሰም፡ "የሚጠሙ፡ ብፁዓን ናቸው። አገኛችሁም አላገኛችሁትም፡ ቢጠሙ ብፁዓን ናቸው።" ሰንቶች እግዚአብሔርን አብዝታችሁ ትፈልጋላችሁ? በጣም ጥሩ። እሺ፡ እግዚአብሔርን አብዝታችሁ በመፈለጋችሁ ብቻ፡ ያን በመሆናችሁ ብቻ ብጹዓን ናችሁ። እሰከ አሁን ባታገኙትም እንኳ፡ ብጹዓን ናችሁ። "የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው።" በመጠማታችሁ እና በመራባችሁ ብቻ ብጹዓን ናችሁ። በመፈለጋችሁ ብቻ፡ ብጹዓን ናችሁ። ምክንያቱም ብዙ የማይፈልጉት ሰዎችም አሉ።

106 የበቀደም ማታ ሰብከቴ ትዝ ይላችኋል? አያችሁ፡ ማሸጊያውን አሰቀርቶ፡ ሰጦታውን እንደሚጥል ቂል። አያችሁ? ማሸጊያውን ሳይሆን፡ ሰጦታውን ውሰዱ። በጣም ጥሩ።

> እንግዲህ፡ **ወዲያው... በመንፈሰ ነበርሁ፥ እነሆም፡ ዙፋን... በሰማይ ቆሞአል፡ በዙፋኑም** ላይ፡ **ተቀማጭ ነበረ።**

107 አሁን፡ አሰተውሉ፡ ከአፍታ በኋላ፡ ወይም፡ ይመሰለኛል፡ ትናንትና አይተነዋል፡ ማለት በዙፋኑም ላይ... በመጀመሪያ በዙፋኑ ላይ ምንም ነገር እንዳልነበረ ተረድተናል፡ አሁን ግን በዙፋኑ ላይ አንድ ሰው አለ ሰለዚህ ኢየሱሰ ከቤተክርሰቲያኑ ጋር ወደ ክብር እንደመጣና በገዛ ዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠ አሳይቷል። "በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፡" ይህ ማለት ከቤተ ክርሰቲያን ዘመን በኋላ ነው። አሁን፡ አሁን፡ ከአፍታ በኋላ ወደዚህ እንገባበታለን።

108 አሁን፡ እናንተ እንዲህ ትሉ ይሆናል፡ "ታዲያ፡ ዙፋኑ ዛሬሰ ወዴት አለ? " አሁን፡ ወንድም ኔቪል፡ ያንን ካለፍኩት፡ ከአፍታ በኋላ "ዛሬሰ ዙፋኑ የት አለ፡" ትለኛለህ። ቶሎ ብዬ መግባት ያለብኝ ይመሰለኛል። "አሁን በዙፋኑ ላይ ካልሆነ ዙፋኑ የት አለ? "

አሁን በዙፋኑ ላይ የለም። የለም፡ ጌታዬ።

109 በጣም ጥሩ፡ አሁን፥

> **ተቀምጦም የነበረው በመልኩ... የኢያሰጲድንና የሰርዲኖን ዕንቍ... ይመሰል ነበር፥** በመልኩም... **መረግድን ይመሰላል፡ ቀሰተ ደመና የመሰለ በዙፋኑ** ዙሪያ **ነበረ።**

110 አሁን፡ ለመጀመር 3ኛውን ቁጥር፡ እንውሰድ። እናም "ኢያሰጲድ፡" ይህ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው መልኩ... በሌላ አነጋገር፡ እሱን ሰትመለከቱት፡ እንደዚህ ባለው ግርማ፡ ውብ ነበር! ኦህ፡ እሱን ማየት እናፍቃለሁ። እናንተሰ?

111 አንድ ቀን... አሰታውሳለሁ እህት ካድል፡ እህት ሃዋርድ ካድል፡ ብዙዎቻችሁ የምታሰታውሷት ይመሰለኛል። ከመንገዱ ማዶ ነበርን፡ አሁን እዚያ ተቀምጣ ያለችው ባለቤቴ ታሰታውሳለች፡ እና ቤት ውሰጥ በርዷት ነበር። እና ተነሳሁ፡

እና ትንሽ ነገር ይዤ ነበር፡ ኧ... ማንኪ የምንለው ሰቶቭ ነበረ በላዩ ላይም... ዳቦአችንን በምድጃው ላይ ባለው ብረት፡ እንጋግረው ነበር። እና እኔ... በጣም ቀዝቃዛ ነበር እናም ነፋሱ እየነፈሰ ነበር፡ ክረምት ነው፡ መሬቱ በበረዶ ተሸፍኗል፡ ንፋሱ በጭሰ ማውጫው ላይ ይነፍሳል፡ እና ህይወቴን ለማትረፍ፡ ምድጃውን ማቀጣጠል ተሰኖኛል። እና እኔ እጅግ ተበሳጨሁ። የሆነ ነገር እጨምርበታለሁ፡ እንደገና ያጠፋብኛል። ቢሊ በርዶታል፡ እሷም በርዷታል፡ እሳት እያቀጣጠልኩ ነበር። እናም በአጋጣሚ ሬዲዮን ከፈትኩት እና (አሁን፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ መሞቅ ጀምረናል)፡ እና እህት ካድል እየዘመረች ነበር፡ "ወደዚያች ምድር በደረስኩ ጊዜ፡ ከሩቅ ከማዶ፡ ኢየሱስን ማየት እንፋቃለሁ። እናንተስ? " ኦህ፡ ማይ!

112 በቃ ወለሉ መሃል ላይ ተቀምጩ እዚያው ተቀመጥኩና ማልቀስ ጀመርኩ። ከዚያ፡ እውነተኛው ጣፋጭ የሞኪንግ ወፍ ድምጿ፡ እንዴት እንደምትዘምረው ታውቃላችሁ። ወደዚያው አድማስ ሰሻገር እሷን መስማት እፈልጋለሁ፡ እንዲህ ስትል፡ "ኢየሱስን ማየት እናፍቃለሁ። እናንተስ? "

113 እኔም "አምላክ ሆይ፡ አዎ፡ አንድ ቀን እሱን ማየት እናፍቃለሁ። አበቦቹ በሙሉ ሲንሳፈፉ፡ ኢየሱስን ማየት እናፍቃለሁ፡" ብዬ አሰብኩ። እንዴት... እርሱን በዙፋኑ ላይ፡ ውበቱን፡ ግርማውን ለማየት! ቢሆንልኝ... ኦህ፡ ቆሜ እሱን ማየት እችል ዘንድ፡ ዮሐንስ በቆመበት ስፍራ መቆም እናፍቃለሁ።

114 ከተወሰነ ጊዜ በፊት እዚህ፡ ታች... በባርያ ንግድ ወቅት። ይህን የምለው ዛሬ ጠዋት እዚህ ሰላሉት ጥቁር ወዳጆቼ ነው። አንድ ጥቁር ሽማግሌ ነበረ፡ እና ሰውዬው... ሁሌ እንደሚሄዱ፡ አንድ ሰፍራ ላይ እየተጓዘ ነበረ።

115 እና በኬንታኪ ውስጥ እንዲህ ልምዳቸው ነበረ፡ ይዘምራሉ። ምናልባት እማማ ኮክስ እና ሌሎች መንገድ ላይ እየዘመሩ ሲሄዱ የነበረ ጊዜ ማስታወስ ይችሉ ይሆናል፡ ታውቃላችሁ፡ እና ከቤት ቤት እየሄዱ ኦርጋን ይጫወታሉ፡ ወጣቶቹ ይዘምራሉ። እዚህ በኡቲካ፡ እና በዙርያ ባሉ ገጠሮች ያደርጉ ነበር። አሁን አሁን ሩብ ዊስኪ ይዘው፡ በየ ሮክ-ኤንድ-ሮል ፓርቲ መዞር ሆኗል።

116 ያኔ፡ ግን፡ ዝማሬዎችን ይዘምራሉ። ከእነዚህ የድሮ መዝሙር-ዝማሬዎች፡ አንድ የዳነ ጥቁር ሽማግሌ፡ ነበር። ጌታም ሰባኪ እንዲሆን ጠራው፡ በማግስቱም በእርሻው ላይ እየዞረ ለባሮቹ እየነገራቸው ነበር። "ጌታ ትናንት ማታ አዳነኝ እና ለወንድሞቼ እንድሰብክ ጠርቶኛል፡" ይላቸው ጀመር።

117 እና በመጨረሻም ወደ እርባታው ባለቤት ወይም ወደ እርሻው ባለቤት ደረሰ። እርሱም ጠራውና፡ "ሳምቦ፡ ና እስኪ፡ እዚህ ግባ፡" አለው። "ወደ ቢሮዬ ግባ፡" አለው።

"እሺ፡ ጌታዬ፡" አለውና፡ ወደ ቢሮው ገባ።

118 አለውም፡ "ይህ በባሮቼ መካከል ሲወራ የምሰማው ነገር ምንድነው፡ እዚያ ካሉ ወገኖች መካከል፡ ከእጄ፡ ከባሮቼ፡ አንተን ጌታ ነጻ አወጣ የሚባለው ወሬ ምድነው? "

119 "አዎን፡ ጌታዬ፡" አለው። "ቦስ፡ እኔ ባርያህ ነኝ፡" አለው። እንዲህ አለው፡ "በገዛ ገንዘብህ የተገዛሁ ነኝ፡ ነገር ግን... " አለውም፡ "ነገር ግን ትናንት

ማታ እግዚአብሔር እኔን ነፃ ያወጣበት መንገድ ይህ ነው፡ ኢየሱስ ከኃጢአትና ከኀፍረት ሕይወት፡ እና ከሞተ ማንነቴ ነፃ አወጣኝ። ነፃ አወጣኝ።"

እሱም እንዲህ አለው፡ "ሳምቦ፡ የምርህን ነው? "

"የምሬን ነኝ፡" አለው።

120 እሱም፡ "በዚህ አካባቢ ባሉ በ—በወገኖችህ መካከል በእርሻው ዙርያ ለመሰበክ እየወጣህ እንደሆነ ሰምቻለሁ።"

121 "አዎን፡ ጌታዬ!" አለ፡ "ይህንን ወንጌል፡ ለሕዝቤ መሰበክ አላማዬ ነው፡" አለው።

"በእውነት የምርህን ነህ ግን፡ ሳምቦ? " አለው፡

"የምር የእውነቴን ነው፡" አለው።

122 እሱም አለው፡ "በል፡ ተነሣና—ወደ ፍርድ ቤት ተከተለኝ፡ እኔም ነጻነትህን አውጅልሃለሁ። ከእኔም ነጻ ነህ፡ ከእንግዲህ ወዲህ ከባርነት ነጻ ነህ። እኔ ገዛሁህ፡ አንተ የእኔ ነህ፡ አሁን ነፃ አውጥቼሃለሁ ይህም ለሕዝብህ ወንጌልን እንድትሰብክ ነው።" ወርዶ የነጻ ወጪዎች ውል፡ ወይም አዋጅ ፈርሞ፡ ነፃ ወጣ። ከዚህ በኋላ እንደ ባሪያ ሊሸጥ አልቻለም። ወንጌልን ለመሰበክ ነፃ ሰው ነበር።

123 ለብዙ ዓመታት በወንድሞቹ መካከል ሰበከ። በአገልግሎቱ ብዙ ነጮች ተለውጠዋል። አንድ ቀን ሽማግሌው የሞቱ ቀን ደረሰች። ለሠላሳ ወይም ለአርባ ዓመታት፡ ወይም ከዚያ በላይ ሰብኳል። በሞተ ጊዜ፡ እነሆ በቤት ውስጥ አስተኝተውት ነበር፡ እና ብዙ ነጮች ወንድሞቹ በቤቱ ከበውት ነበር እና ለሁለት ወይም ለሦስት ሰዓት ያህል የሄደ መሰሏቸው ነበር። ከዚያም በመጨረሻ ነቅቶ በክፍሉ ውስጥ ሲመለከት፡ እንዲህ አሉት...

"ሳምቦ፡ የት ነበርክ? "

እሱም አላቸው፡ "ኦህ፡ ተመልሼ መጣሁ'ዴ? ተመለስኩ'ዴ? "

"ነገሩ ምንድነው፡ ሳምቦ፡" ብለው ጠየቁት?

"ኦህ፡ ወደ ሌላኛው ምድር ተሻገርኩ፡" አላቸው።

"ንገረን እስቲ፡" አሉት።

124 እንዲህ አላቸው፡ "እነሆ፡ ወደ ህልውናው፡ ተወሰድኩ።" "በዚያም በቆምኩ ጊዜ፡" አላቸው፡ እንዲህ አለ፡ "አንድ መልአክ መጣ፡ 'ሰምህ፡ ሳምቦ **እከሌ-እና-እከሌ** ነውን? ' በማለት ጠየቀኝ፡"

"አዎን፡ ጌታዬ፡ ነው፡" አልኩት።

"ግባ፡" አለኝ።

"ወደ ውስጥ ገባሁ፡ እና እዚያ ተቀምጦ ተመለከትኩት።"

125 ከዚያ እንዲህ አሉኝ፡ "ሳምቦ፡ ይበቃሃል፡ እሱን አይተኸዋል፡ አሁንም ወደዚህ ና፡ መጐናጸፊያህን እንሰጥሃለን፡ በገናህን እንሰጥሃለን፡ አክሊልህን እንሰጥህ ዘንድ እንወዳለንና።"

ሳምቦም፡ "ስለ በገና፡ ስለ ዘውድ እና ስለ መጎናጸፊያ አታናግሩኝ፡" አላቸው።

"ግን'ኮ ድል ነስተሃል፡ ሽልማትህን ልንሰጥህ እንፈልጋለን፡" አሉት።

126 አላቸው፡ “ስለ ሽልማት… ስለ እኔ… አትንገሩኝ።” “ብቻ ቆሜ እሱን አንድ ሺ አመት ልየው ተውኝ። ሽልማቴ እሱ ይሁንልኝ።” አላቸው።

127 ሁላችንም የሚሰማን በዚህ መልኩ ይመስለኛል፡ “ብቻ ቆሜ እሱን ልየው ተውኝ።” ኦህ፡ አሁን ካለኝ የተለየ ሰውነት ይኖረኛል፡ የሰውነታችሁ እያንዳንዱ አካል ሁሉ እሱን ማየት ይመኛል።

128 በዚያም ዮሐንስ ቆሞ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየው፡ እርሱም “የኢያሰጲድ እና የሰርዲን ዕንቍ ይመስል ነበር።” አሁን፡ ነገሮች እና ቃላት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትርጉም አላቸው። አሁን፡ “የኢያሰጲድ እና የሰርዲን ዕንቍ።”

129 አሁን፡ ካስተዋላችሁት፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ይነጻጸራል። በቅዱሳት መጻሕፍት የኋላ ክፍሎች ላይ፡ እርሱ አልፋ፡ ኦሜጋ፡ መጀመሪያው እና መጨረሻው ነበር፡ ፊተኛውና ኋለኛው ነበር፡ አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ ነበር። “ሁሉም በሁሉም” በእርሱ ተጠቃሏል። ማቴዎስ 17 እንደሚያሳየው… በታቦር ተራራ ላይ፡ ነገር ሁሉ በእርሱ ዘንድ ተጠቃሎ ነበር።

130 አሁን፡ “ኢያሰጲድ” ማለት—ዕንቍ ነው፡ እና “ሰርዲዮን” ዕንቍ ነው። (አሁን፡ ከእፍታ በኋላ ወደ ቀለሞቻቸው እናልፋለን።) አሁን፡ ቀደምት ነገዶች እያንዳንዳቸው ሲወለዱ፡ አዎ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ የልደት ዕንቍ እንዳለው ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። የኔ፡ የተወለድኩት በሚያዝያ ወር፡ አልማዝ ነው። እና የተለያዩ ወራት የተለያዩ ዕንቆች ይወክላሉ። እንግዲህ፡ ቀደምት ነገዶች እንደዚሁ ነበሩ። አንዱ ነገድ አባት፡ በተወለደ ቁጥር፡ የልደት ዕንቍ-… ነበረው።

131 እስቲ አንድ እፍታ ብቻ ቆም እንበል። የዕብራውያን እናቶች… ወዳጄ ሆይ፡ እምነትህ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተረጋገጠ እንዲሆን፡ መለኮታዊ ቃል ላሳይህ። ሁል ጊዜ፡ ዕብራውያን እናቶች፡ ምጥ ላይ ሲሆኑ፡ ለመውለድ፡ በምጥ ወቅት… ልጆችቹን ለመውለድ ሲያምጡ፡ ልክ ሲወልዱ ስሙን ይናገራሉ (ማለት ከእሷ ለሚወለደው ህጻን) የህጻኑን ስም ትናገራለች፡ በዚህም ምክንያት በጌታ መምጣት ጊዜ በፍልስጤም ምድር ላይ የልጁን ሰፍራ ትመድባለች። ምጡ በእናቲቱ ላይ ያማል! ለምሳሌ፡ **ኤፍሬም** ማለት “ባሕር ዳር” ማለት ነው። አያችሁ? ስለዚህም የኤፍሬም ዕጣ በባሕር ዳርቻዎች ላይ ተሰጠው። እና፡ **ይሁዳ**፡ ከተባለ… ቃሉ ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም፡ ከፍቼ ማየት ግን እችላለሁ። አሁን፡ ተመልከቱ፡ በርግጥ እነዚህ ትንንሽ ነገሮች፡ ለመልቀም፡ ጊዜ አይኖረኝም። ብቻ ወደ ኋላ መለስ ስንል፡ **ይሁዳ፡** የይሁዳ ትርጉም ምንም ይሁን፡ ሰፍራው በእስራኤል ልጆች መካከል መቀመጡን ያመለክታል።

132 በዘፍጥረት 48 እና 49 ላይ ደግሞ፡ ያዕቆብ በበትሩ እንደተደገፈ፡ ሲሞት፡ በዚያ ታዩታላችሁ፡ ዓይነ ሰውር ቢሆንም፡ ለእነዚያ ልጆች በዓለም መጨረሻ በየሰፍራቸው የት እንደሚገኙ ወሰነላቸው። እና ወደ ትውልድ አገራቸው ከተመለሱ ጀምሮ አሁን በተወሰነላቸው ዳርቻ ይገኛሉ። ዮሴፍን አለው፡ “በቅጥር አጠገብ እንደሚያፈራ ፍሬያማ የወይን ነህ።” አያችሁ፡ “በምንጭ አጠገብ፡” በውኃ። ከዚያም አለፈ። እንዲህ አለው፡ “በጌታ በእግዚአብሔር ታምነሃል። ቀስትህን—አበረታህ” (ዩናይትድ ስቴትስን። አያችሁ? ) “በጌታ ዘንድ፡ አንድ ቀን ግን ያን ወይን በቅጥሩ ላይ ይመለሣል።” አሁንም ይችትና፡ ተመልከቷት። የዛሬ ሶስት ሺ አመታት ገደማ እንደተናገረው፡ እንደገና

ተመልሳለች። ስለ ኤፍሬም እግሩን በዘይት እንዳጠለቀ ይነግራል፡ ኤፍሬምም ትላልቅ የድፍድፍ ዘይት ጉድጓዶች ባሉበት ተቀምጧል። በትክክል።

133 የእነዚያ ሰዎች ንግግር፡ በእነዚያ ሟቾች ላይ ምን ነበረ? እግዚአብሔር አካላቸው ወስዶ በውስጣቸው ተመላለሰ!

134 እንዲህ ሆነ የሮማ ኢምፓየር ሲበታትናቸው፡ ሌሎችም ሲበትኗቸው፡ በሂትለር ተጠሉ፡ ብዛታቸው እልፍ ጊዜ እልፍ ነበሩ፡ ደም ስራቸው ውስጥ አረፋ እየወጋ ገደላቸው፡ ገላቸውን ከልጆቻቸው እና ከነገሮቻቸው፡ እና ከአጥንቶቻቸው ጋር በአጥር ላይ ተንጠልጥለው ይታዩ ነበር... አውርደውም ከአጥንታቸው ማዳበሪያ ይሰሩ ነበር። ወደዚያ ይወስዷቸውና መርፌ ይወጓቸዋል፡ ፉርጎ ላይ ይጭኗቸዋል። ከዚያም ወጡ፡ በወጡ ጊዜም፡ ገና ከጅምሩ፡ መዘመር ጀመሩ፡ "መሲህ ይመጣል የወይኑን ጭማቂ እንደገና እንጠጣለን።" እነዚያ አይሁዶች፡ ለመሞት፡ ወደዚያ ሲወሰዱ፡ በጉዞ ላይ ሳሉ፡ ጥቂት የልብ ምት እንደሚቀራቸው ከዚያ በኋላ እንደሚሞቱ ያውቁ ነበር። ወደዚያም፡ እየዘመሩ ይወርዱ ነበር፡ "መሲሑን በቅርብ እናየዋለን።" ኦህ፡ ማይ! ከአጥንቶቻቸው ማዳበሪያ ተሠራ።

135 እዚህ ያላችሁ ብዙዎቻችሁ ወታደሮች ይህን ታውቃላችሁ አይታችሁታል። ሂትለር እና ሌሎች፡ እነርሱን ባቃጠሉበት፡ በዚያ ሰፍራ እኔ ራሴ ቆሜአለሁ። እንዲሁም እነ ስታሊን ሩስያን እና ሌሎቹን ተመልከቷቸው፡ ተመሳሳይ ድርጊት ፈጽመዋል። በትክክል። አይሁዳዊው፡ መጨረሻው ምን ሆነ? ወደ ትውልድ አገሩ እንዲመለስ አስገደዱት። አሁን የቆሙበት ቦታ እሱ ነው።

136 አሁን፡ **ሶስት ደቂቃ ጎደል ለእኩለ ሌሊት**፡ የሚለውን ታላቅ ፊልም አይቼዋለሁ። አይሁዶች በገቡ ጊዜ፡ "በገዛ ምድራችሁ ለመሞት፡ ለምን ተመለሳችሁ፡" በማለት፡ ይጠይቋቸው ነበር?

137 እነርሱም "መሲሑን ለማየት መጥተናል፡" አሉ። አሜን። እህም! በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን።

138 ስለዚህ የሚወለዱት እያንዳንዳቸው ልጆች፡ የልደት ዕንቍ ነበራቸው። አሮን፡ የእነዚያ ልጆች ሁሉ ሊቀካህን የሆነው፡ በላዩ ላይ፡ በልብሱ ላይ የደረት ኪስ ነበረው። ወደዚህ 6ኛ ቁጥር ለመግባት፡ ይህንን ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ ማቆየት እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም የብሉይ ኪዳንን ምልክቶች ሁሉ እዚያው ውስጥ ያመጣቸዋል። እያንዳንዱ... በብሉይ ኪዳን የነበሩት ዕቃዎች እና ሁሉም ነገሮች በመንግሥተ ሰማያት የታዩ ምሳሌዎች ነበሩ፡ የሰው ልጆች ተምሣሌት ነበር።

139 እና የአሮን የደረት ኪስ ይህ ነው፡ እርሱም ሊቀ ካህን ነበረ። አስተውሉ፡ የእያንዳንዱ ነገድ የልደት ዕንቍ በተምሣሌት ተቀምጦ ነበረ። አንደኛው፡ የልደት ዕንቍ፡ ዕንቍውን በዚያ የተቀመጠ ነበር፡ የኤፍሬም ነገድ፡ የምናሴ ነገድ፡ የጋድ ነገድ፡ የብንያም ነገድ፡ ሁሉም በዚህ ተምሳሌት ተቀምጠው ነበር። እና እንደዛ ነው... ከዚያም የልደት ዕንቍዎች፡ ቆንጆ እንቁዎችን፡ ወስደው እንደዚህ ባለው መለጠፊያ ያንጠለጥሉታል። አንድ ነቢይም ትንቢት ቢናገር፡ ትክክል ቢመስልም ባይመስልም፡ ወደ ኡሪም እና ቱሚም ይወስዱታል በዚያም በፊቱ ትንቢቱን ይናገራል፥ ቅዱስ ብርሃን ወደዚያ መጥቶ እነዚያን ድንጋዮች

በአንድነት ማንጸባረቅ ከጀመሩ፡ የተናገረው እግዚአብሔር ነው ይባላል። ይህም ለሁሉም፡ ለነገዶቹ በሙሉ፡ የተሰጠ ነበረ።

140 እሺ፡ አሁን በዚህ ውስጥ፡ አንደኛው ዕንቍ። አንደኛ፡ የመጀመሪያው ልጅ ማን እንደነበረ የሚያውቅ አለ? ስሙ ማን ነበር? ሮቤል። በጣም ጥሩ። የመጨረሻው ማን ነበር? ቢንያም። ልክ ነው። የሮቤል የልደት ዕንቍ "ኢያስጲድ" ሲሆን፡ የቢንያም ዕንቍ "ሰርዲዮን" ነበረ። በምስሉም እንደ ፊተኛው እና እንደ ኋለኛው "ሮቤል እና ቢንያም፡" መታየት ነበረበት፡ የነበረውና፡ ያለው፡ የሚመጣውም፡ በግሪክ ፊደል አልፋ (A)፡ እና በግሪክ ፊደል ኦሜጋ (Z) ነበር። እርሱ ፊተኛው፡ የመጨረሻው፡ ከብንያም እስከ ሮቤል፡ ከሮቤል እስከ ቢንያም ነበር። ኦህ፡ ማይ! እንዲሁ ነበረ፡ "በምስሉም እንደ ሰርዲዮን ድንጋይ እና እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ ይመሰል ነበር።" በዙፋን ላይ ተቀምጦ ነበር!

141 በክብሩ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ልታዩት እንዴት ትፈልጉ ይሆን? እስኪ በፍጥነት፡ ራዕይ 21፡10 እንግለጥና፡ እና እዚህ ጋር እንመልከተው። እሺ፡ 21፡10 እስከ 11።

> **በመንፈስም ወደ ታላቅና ረጅም ተራራ ወሰደኝ፡ ታላቂቱ**ንም **ከተማ አሳየኝ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ የወረደች፡ ቅድስት ኢየሩሳሌም፡**
>
> **የእግዚአብሔር ክብር ተሞልታ፡... የእግዚአብሔር ክብር ተሞልታ፥** ብርሃኗም **እጅግ እንደ ከበረ ዕንቍ፡ እንደ ኢያስጲድ... ይመስላል**... **፡ እንደ ክሪስታልም ግልጽ ነው፥**

142 "ብርሃኗ።" ብርሃን! ብርሃን ማን ነው? "ለከተማይቱም በጉ ብርሃንዋ ነውና፡ ፀሐይ አያስፈልጋትም።"

143 "ኢያስጲድ፡ ሰርዲዮን" ዕንቍ። የእግዚአብሔር ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ቤተክርስቲያኑ ናት። ፊተኛው እርሱ ነበር። ምን ነበር? የዘመን መጀመሪያ እርሱ ነበር፡ የዘመን ፍጻሜም እርሱ ነው። የነገዶች ጅማሬ እርሱ ነበረ፡ የነገዶች ፍጻሜም እርሱ ነው። በዚያ በቤተ ክርስቲያን የነበረው... በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን—የነበረ መንፈስ እርሱ ነበር፡ በሎዶቅያ የነበረ የቤተ ክርስቲያን መንፈስ እሱ ነው። እርሱ ፊተኛውና መጨረሻው፡ ከ A እስከ Z፡ ፊተኛው፡ ኋለኛው፡ የነበረውና የሚመጣው፡ የዳዊት ሥር እና ዘር፡ የንጋት ኮከብ፡ የሸለቆ አበባ፡ የሳሮን ጽጌሬዳ! አቤት፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እርሱን የሚገልጹ ወደ አራት መቶ እና ከዚያ በላይ መጠሪያ መዓርጎች አሉ። እስኪ አስቡት፡ ከዚያስ ምን ሆነ! ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ለእግዚአብሔር ምስጋና በግርግም የተወለደ ትሑቱ ጌታ ኢየሱስ ሆነ።

144 ትሑት የሆነ ነገር ሁሉ፡ ትክክል ስለሆነ ተከተሉት። ትልቅ የሆነ ሆሉ ጥቅጥቅ ሸሚዝ ነውና፡ ከእርሱ ራቁ፥ ኢያችሁ፡ ብዙ ንፋስ ነው፡ ባዶ ነው። በጣም ጥሩ።

145 አሁን፡ "እርሱ የኢያስጲድ እና የሰርዲዮን ዕንቍ ይመሰል ነበር።" ወደ ኋላ እንመለስ። ይዛችኋል... ? ትንሽ ጊዜ አለን፡ አይደል? ገና አርባ ደቂቃ ገደማ ይቀረናል። እናስተውልና፡ ወደ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 1 እንመለስ። በመጽሐፍ ቅዱስ ወደ ብሉይ ኪዳን፡ ወደ ሕዝቅኤል ተመልሰን፡ ሕዝቅኤል እርሱን ባየበት ቦታ፡ እናንብብ። እና እነዚህን ቅዱሳት መጻሕፍት አሁን

አነጻጽረን የት እንዳለን እንመልከት። ሕዝቅኤል ምዕራፍ 1፡ እሺ፡ አሁን ለአፍታ እናንብብ። አሁን የመጀመሪያዎቹን አምስት ጥቅሶች አነባለሁ፡ እናነባለን፡ ምልክት አድርጌበታለሁ፡ ከ26 እስከ 28። አሁን ግን ከነቢዩ ከየሕዝቅኤልን ከምዕራፍ 1 ላይ፡ የመጀመሪያዎቹን ጥቅሶች እናንብብ። በጣም ጥሩ፡-

> **እንዲህም ሆነ በሠላሳኛው ዓመት፡** እና **በአራተኛው ወር፡ ከወሩም በአምስተኛው ቀን፡... ከምርኮኞች መካከል ነበርኩ—በኮቦር ወንዝ ከምርኮኞች መካከል ነበርኩ፡...** (ኮበር፡ ልክ ነው? ሲ-ኤች-ኢ-ቢ-ቢ-አር፡ ኮበር።)... **ሰማያትም ተከፈቱ፡ የእግዚአብሔርንም** ራእይ **እየሁ።**

> እዚህ ውስጥ... (አሁን፡ ተመልከቱ።)... **ንጉሡ ዮአኪን** በተማረከበት ወር**፡ ከወሩም በአምስተኛው** ቀን፡

> **የእግዚአብሔር ቃል ወደ ቡዚ ልጅ፡ ወደ ካህኑ ወደ ሕዝቅኤል፡ በከለዳውያን ምድር... በኮቦር ወንዝ አጠገብ ሳለ ወደ እርሱ በግልጥ መጣ፥ የጌታ እጅም... በእሱ ላይ ነበረች።**

> **እኔም እየሁ፡ እነሆም፡ ከሰሜን በኩል፡ ዐውሎ ነፋስና፡...**

146 ይህን ነቢይ ተመልከቱት፡ ከክርስቶስ መምጣት አምስት መቶ ዘጠና-አምስት ዓመት በፊት፡ ራእዩ ከዮሐንስ ጋር እንዴት እንደሚመሳሰል ተመልከቱት፡-

> **... ከሰሜን በኩል ታላቅ ደመና፡ ዐውሎ ነፋስም፡... ወደ ውስጥ** እየታጠፈ የሚነድ፡**በዙሪያውም ፀዳል ያለው እሳት ነበረ፡ በመካከልም በእሳቱ ውስጥ፡ ህምበር ቀለም ያለው** ነበረ።

> **ከመካከልም የአራት ህያዋን ፍጡራን አምሳያ ወጣ። መልካቸውም እንደዚህ ነበረ፥ ሰውም ይመስሉ... ነበር።**

147 አስተውሉ፡ ከእነዚህ ከአራቱ ፍጥረታት አምሳያ በላይ የነበረው የእግዚአብሄር መንፈስ ቀለም፡ ህምበር ነበር። ህምበር ቢጫማ-አረንጓዴ ነው። አሁን፡ ተመልከቱ፡ "ቢጫማ-አረንጓዴ፡" **ህምበር**፡ ኦህ፡ እሱ ትናንትም ያው ነው... ራሱን ለሕዝቅኤል ገለጠ፥ በሕዝቅኤል ራእይ መካከል፡ ከአራቱ ሕያዋን ፍጥረታት በላይ ሲወጣ ያየው ብርሃን ቢጫማ-አረንጓዴ ነበር። ወደ ዮሐንስ በመጣ ጊዜም፡ **በመረግድ** ውስጥ ታየው እርሱም ደግሞ "ቢጫማ-አረንጓዴ" ነው። አሁን ወደ ገላጩ በቢጫማ-አረንጓዴ መጣ። ወደ እኛም በ ቢጫማ-አረንጓዴ መጣ፡ ያንን ብርሃን! እርሱ ብርሃን ነውና፡ በብርሃን ተመላለሱ።

148 አሁን ወደ 26 ኛው ቁጥር እንሂድ፡ ከዚያም 28ኛ ማንበብ እንችላለን። 26ኛው ቁጥር፡-

> **ከጠፈሩ በላይ፡...**

ኦህ፡ ወደ ቤታችሁ ከተመለሳችሁ በኋላ፡ ይህን ማስታወሻ ይዛችሁ እያንዳንዷ ነገር እንድታነቧት እፈልጋለሁ። ጊዜ ለመቆጠብ፥

> **በራሳቸውም ላይ ካለው ጠፈር በላይ፡** የሰርዲዮን ዕንቊ **የሚመስል ዕንቊ ነበረ፥** በ**ዙፋኑም አምሳያ ላይ... እንደ ሰው መልክ አምሳያ ነበረ።**

149 እያችሁ፡ የሰው ልጅ ያ ነበር፡ ክርስቶስ። አሁን እንዴት እንደነበረ፡ እዚህ እንዴት እንደለበሰ ተመልከቱ፥

**የሚብለጨለጭ የሀምበር** ቀለማት **እየሁ፡** (በዚህ በሰው ልጅ ዙርያ፡ ተመልከቱት) **ከወገቡም እምሳያ በውስጡ—በውስጥ** በዙርያውም፡ **እንደ እሳት መልክ ያለው እምሣያ ይመስላል...**

150 አዳምጡ! በልባችሁ ውስጥ፡ መንፈሳዊ ሁኑ፡ አስተዋይ ሁኑ። በኢየሱስ ስም አምላችኋለሁ፡ ይህን ለራሳችሁ ጠብቁት! ምን ያህል አስደሳች እንደሆነ አስታውሱ!

151 "እኔ-... " እንደገና ከ 27ኛው ቁጥር እንጀምር። ሁላችሁም፡ ሰሙ! አሁን እውነተኛ ግንዛቤ ይኑራችሁ!

**እና እንደ ሀምበር እምሣያ ቀለም እየሁ** (ያም ቢጫማ-አረንጓዴ ነው)፡ በዙሪያው **ያለውን የእሳት መልክ እየሁ... እ፡**...

በሀምበራዊ-አረንጓዴ ዙሪያ እሳት ነበረ። አሁን፥

**... ከወገቡም መልክ ወደ ላይ፡** (ከወገቡም ወደ ላይ።) **ከወገቡም መልክ... ወደ ታች፡ እንደ እሳት የሚመስል እየሁ፡ እና** በዙሪያውም **ጸዳል ነበረው።** (ዙርያው ሁሉ እሳት ነው።)

በ**ዝናብ** ቀን **በደመና ውስጥ እንደ ቀስተ ደመና** ቀለም **እምሳያ፥** እንዲሁ በዙሪያው **ያለ ፀዳል እምሳያ ነበረ። የእግዚአብሔር ክብር** እና **ምሳሌ** እና **መልክ ይህ ነበረ። ባየሁም ጊዜ፡ በግምባሬ ተደፋሁ፡ የሚናገርንም ድምፅ ሰማሁ።**

152 ተከታተሉ! ዝግጁ ናችሁ? አድምጡኝ! እንግዲህ ይህን ያዙት፡ አስታውሱት፡ እሳሰባችኋለሁ። (ጂን፡ ይህን ቴፕ ማቆም ትችላለህ።) አድምጡ! (እይደለም፡ ችግር የለውም፡ እዚህ ጋር ማቆም እይጠበቅብኝም። ቴፑን እስቀጥል ማለቴ ነው፥ ይህን ለቤተ ክርስቲያን ይፈቀድላት።) ይህን አስተውሉ! አሁን፡ ይህ ከጌታ ዘንድ ያለው የብርሃን ቀለም ታውቁት ዘንድ፡ እና ጌታን ተከትሎ የሚመጣው የጌታ ብርሃን፡ እና እንደ ጌትነቱ፡ ሀምበር ነው፡ ቢጫማ-አረንጓዴ ነው። ዛሬ ከእኛ ጋር ያለው የብርሃን ተመሳሳይ ቀለም ነው፡ ሳይንቲስቶች ምስሉን እንደወሰዱት፡ ቢጫማ-አረንጓዴ፡ ሀምበር ነው።

153 ትንሽ ልጅ ሳለሁ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳየው፡ እናንተ እንጋፉ-የሆናችሁ፡ ታስታውሳላችሁ። ትክክለኛው ፎቶ ከመነሳቱ በፊት ደጋግሜ ነግሬአችኋለሁ፡ "ቢጫማ-አረንጓዴ ነበር፡ እሱም ሀምበር ነው።" አሁን፡ የጌታን መንፈስ መሆኑን እንድታውቁት ለማድረግ...

154 በፊቱ ከቆመው ከሕያው ፍጥረት ወገብ ባየው ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "ከወገቡ ወደ ላይ እንደ እሳት፡ ከወገቡ ወደ ታች ያለው ብርሃን፡ በብርሃን ተሸፍኗል። ዙሪያውም በሙሉ እንደ ቀስተ ደመና ያሉ ብዙ ቀለሞች ነበሩ።" ልክ ነው?

155 እግዚአብሔር በእነዚህ ተመሳሳይ ቀለሞች ዘንድ እንደሚኖር፡ እንድታስታውሱት እፈልጋለሁ፡ "ከወገብ ወደ ላይ፡ እሳት፡ ሀምበር ቀለም፡" በፊልም ካሜራ ወይም በቀለም ካሜራ የተነሣ፡ "ከወገብ ወደ ላይ፡ ከወገብ ወደ ታች፡ እና ዙሪያው ሁሉ ሀምበር፡ ከዝናብ በኋላ በሰማይ እንደሚወጣ ቀስተ ደመና ውስጥ እንዳሉ ቀለሞች ዓይነት።" ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡

እስከ ለዘላለምም ያው ነው! መንፈስ ቅዱስ አሁንም በዚህ በመጨረሻው ቀን፡ ከሰልጣኑ ጋር አሁንም በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አለ። ይኸው እዩት። እኔ አይደለሁም፡ እኔ ዝም ብዬ በሰፍራው ቆምኩኝ፡ የተነሣው ምስሉ ነው። ልክ ሕዝቅኤል ባየው መልኩ፡ እንድትመለከቱት እፈልጋለሁ። በተመሳሳይ መልኩ፡ ተመሳሳይ ቀለሞች፡ እንቅስቃሴውም ተመሳሳይ፡ ሲያበራም ተመሳሳይ የሆነ፡ ሕያዋን ፍጥረታት። ይህ ምንድነው? ሕያዋን ፍጥረታት የሕያው ቤተክርስቲያንን ጥላ ነው፡ በክርስቶስ ኃይል እና ትንሳኤ ሕያው የሆነች ቤተክርስቲያን። ተመሳሳይ የሀምበር ቀለሞች ከወገብ ወደ ላይ፡ ከወገብ ወደ ታች ሸፍነውታል።

156 ሳይንስ ሰዕሎቹን እንሰቷልና፡ ግምት ብሎ ነገር የለም! ቀለሞቻቸውን ተመልከቱ፡ እዚያ ውስጥ ያሉትን የእሳት ቀለሞች ብቻ ተመልከቱ። እያችሁ? ቀስተ ደመና። ይህንን ቢጫማ-መረግድ ቀለም እዩት። አሁን፡ **በዚህ** ካሜራ አንሺ የተነሣው፡ ፊት ለፊት የተነሣ ፎቶግራፍ ብቻ ነው። **በዚህ** ባለ ከለር ካሜራ፡ ከለር ያላቸው ሰዕሎች፡ ኮዳክሮም ቀለም ነው። በዚያ ውስጥ ያሉ የመረግድድ ቀለሞችን ተመልከቷቸው። ከኋላ በኩል እናንተ ማየት በምትችሉበት ብርሃን ባለው አቅጣጫ ላሰቀምጠው። አሁንስ ይታያችኋል? "እንደ ቀስተ ደመና፡" እንደ ቀስተ ደመና ወደ ኋላ እና ወደ ፊት የሚመጡትን ፍንጣቂዎች ተመልከቷቸው፡ እያንዳንዱ ባለ ልዩ ልዩ ቀለም ነው። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ወደዚያ እንገባለን፡ እነዚህ ቀለሞቹ ምንድ ናቸው እና ምን ምን ያንፀባርቃሉ?

157 አቤት! ምስኪኑን ልቤ በደስታ የሚያዘልለው ነገር ይህ ነው። አሁን በምንኖርበት በዚህ ዘመን ይህ ማወቃችን፡ ከክርስቶስ በቀር... ሌሎች መቆሚያዎች፡ የምንቆምባቸው ሁሉ የሚውጡ አሸዋዎች ናቸው። ሳስበው፡ "ለምን ያንን መናገር አቃተኝ? ለምንስ አለምን እንዲያየው ማድረግ ተሳነኝ? " ዓለም ይሄን እንዳያይ ስለተደረገ ነው። ዓለም አያየውም፡ በፍጹም አያዩትም! ቤተክርስቲያን ግን አይታው የማታውቀውን የላቀውን መነቃቃት እየተቀበለች ትገኛለች!

158 በእነዚያ ዘመናት ፎቶግራፍ ማንሣት አይችሉም ነበር። አሁን ግን ይችላሉ ምክንያቱ የሜካኒካል መሣሪያ-ዎች አሏቸው። እግዚአብሔርን ለመካድ መካኒካዊ መሣሪያዎችን የፈለሰፉ ሰዎች፡ ወዲያው ተመልሰው አምላክ እንዳለ አረጋግጠዋል። ትክክል፡ "መረግድ፡" ነው። አሁን፡ ይሄን ቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ አነበብኩላችሁ እንጂ፡ ከራሴ ፈጥሬ አለመሆኑን አስተውሉ። አሁንም ሳነበው ተከታተሉኝ፡ እና ተመልከቱ፡ እነሆ ያው ጌታ አምላክ ነው፡ ልዩነት የለውም። 27ኛውን ቁጥር ተመልከቱ፡-

**እንደ እሳት ምሰያ** የሆነ... **የሀምበር ቀለም፡ እየሁ**...

159 ተመልከቱ፡ ልክ እንደሚንቀለቀል ነበልባል። እያችሁ? ከእሳት መካከል እንደሚንበለበል ሀምበር ቀለም። አሁንስ እያችሁት? ሀምበር፡ **ይህ** ከእሳት መካከል የሚንበለበል ሀምበር ቀለም ነው። እዚህ ታች እንዲህ ይላል፡-

**በምሰሉም** እንደ **ቀስተ፡ ከዝናብ** ቀን በኋላ፡ ቀስተ ደመና፡...
**ከዝናብ** ቀናት በኋላ፡ እንደሚወጣ ቀስተ ደመና **ይመስላል፡...**

160 እንዲሁም—ደግሞ "ሕያው ፍጥረት" ነበረ። ዮሐንስ ምሳሌዋ የሆነው፡ መላዋ ቤተ ክርስቲያን፡ ተወሰደች። ነግሬአችኋለሁ። አንድ ሰው በራእይ ውስጥ፡ የለበሰችውን የክርስቶስን አካል ሊወክል ይችላል! አሁንም፡ ተመልከቱ፥

> **እንደ እሳት ምሰያ የሆነ... የህምበር ቀለም፡** በ**ዙርያው... አየሁ፡ በምስሉም... ከወገቡም አምሳያ ወደ ላይ፡ እና ከወገቡም አምሳያ ወደ ታች፡ እንደ እሳት ምሰያ ሆኖ አየሁ፡...**

161 ተከታተሉ፡ የሚረጨውን እሳት **ተመልከቱ**። ከምን? ከቀስተ ደመና፡ ከሰባቱ ቀለማት። አሁንም፡ ተመልከቱት፡ **በዚያ** ውስጥ ሰባት ቀለማት ይገኛሉ፡ ቀስተደመናም ሰባት ቀለማት አሉት።

> **... እንደ እሳት ምሰያ እየሁ፡** በዙሪያ**ውም ፀዳል ነበረ።**
>
> **በዝናብ ቀን** በደመና **ውስጥ** እንደ **ቀስተ ደመና አምሳያ፡ እንዲሁ** በዙሪያው **ያለ ፀዳል አምሳያ ነበረ።** (በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ፡ አያችሁ።) **የጌታ ክብር ምሳሌ መልክ ይህ ነበረ።**

162 ማለት፡ **ጌታ** ሳይሆን፡ የጌታ**ን ክብር**። በገዛ ቤተክርስቲያኑ ላይ በቤተክርስቲያኑ ሁሉ የሞላ የጌታ ክብር አለ! አሜን! አቤት፡ ለማያስተውሉ ሞኝነት ይመስላል፡ ለሚያምኑ ግን እንዴት ታላቅ ነው። ኧሃ-ሃህ።

> **... የጌታ ክብር ምሳሌው** እና **መልክ ይህ ነበረ። ባየሁም ጊዜ፡** በ**ግምባሬ ተደፋሁ፡ የሚናገርንም ድምፅ** ሰማሁ...

163 እዚህ ላይ ወደፊት በመቀጠል ይህ ራእይ ምን ማለት እንደሆነ ይናገራል፡ ወደዚያ ለመግባት ዛሬ ጠዋት ጊዜ አይኖረንም።

164 አሁን፡ ጌታ በታላቅ ምህረቱ እነዚህን ነገሮች እንዴት እንደሚሰጠን አስተውሉ።

165 አሁን ሌላውን ደግሞ እንመልከት። ሕዝቅኤልም ዮሐንስም ሁለቱ በብርሃን እና በቀለማት ምሥጢር አይተውታል፡ እና "ህምበር ቀለም" በማለት ጠርተውታል። ዮሐንስ በኋላ... እናንተ ለምትጽፉ... ጥቅሶቹን ለምትጽፉት፡ አንደኛ ዮሐንስ 1፡5 እስከ 7 ደረሰ። ዮሐንስ፡ በኋላ (መጽሐፉን ሲጽፍ ሦስት ዓመት ገደማ በፍጥሞ ደሴት ላይ ነበር)፡ በዘጠናዎቹ ውስጥ ያለ ሽማግሌ ሆኖ ሲመለስ፡ በአንደኛ ዮሐንስ 1፡5 እና 7 ላይ፡ "እግዚአብሔር ብርሃን ነው፡" አለ። ዮሐንስ የግል ልምምድ ያገኘ ነበር፡ እርሱን አይቶ ብርሃን መሆኑን አውቋል፡ ብርሃን፡ ዘለአለማዊ ብርሃን። የኮስሚክ ብርሃን አይደለም፡ የኩራዝ ብርሃን አይደለም፡ የመብራት ኃይል፡ የፀሐይ ብርሃን ሳይሆን፡ የዘላለም ብርሃን! አቤት፡ ሰወደው። "እግዚአብሔር ብርሃን ነው።"

166 አስተውሉ፡ አሁን ወደ ኋላ መለስ ብለን የት እንደደረስን እናያለን። ገና 3ኛው ቁጥር ላይ ነን፡ አይደል? እንረዳው ይሆንን? ተስፋ አደርጋለሁ። በጣም ጥሩ፡-

> **... እርሱም... በመልኩ የኢያስጲድንና** የሰርዲኖን **ዕንቍ ይመስል ነበር፥** በ**መልኩም መረግድን የመሰለ... ቀስተ ደመና፡ በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ።** (ቢጫማ-አረንጓዴ።)

167 አሁን፡ "ቀስተ ደመና፡" ቀስተ ደመና እንደነበረ አስተውሉ። ወደ ዘፍጥረት 9 እንመለስ፡ እና ከዘፍጥረት 9፡13 ላይ እንረዳው። እዚህ ወደ ኋላ ላይ "ቀስተ

ደመና፡" ለመጀመሪያ ጊዜ ቀስተ ደመና ሲታይ እናያለን። ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 9 ላይ፡ ከ 13ኛው ቁጥር ጀምሮ፡ ዘፍጥረት 9፡13 እንጀምራለን። ሁላችሁም ይህን ትወዱታላችሁ? ኦህ፡ እኔም እወደዋለሁ! ኧረ አልወደውም፡ አፈቅረዋለሁ እንጂ! ተመልከቱ፦

**ቀስቴን** በደመና **ውስጥ አኖራለሁ፡ እርሱም እንደ ምልክት ይሆናል** (ተመልከቱ!)፡ **በእኔና በምድር** መካከል **የቃል ኪዳን ምልክት ትሆናለች**።

168 ምንድን? "በእኔ እና በኖህ መካከል"? አይደለም። "በእኔና በምድር መካከል።"

**እንዲህም ይሆናል፡ በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ፡ ቀስቲቱ በደመናው ትታያለች፥**

**በእኔና በ—በእናንተ** መካከል **ያለውን፡ ቃል ኪዳኔን አስባለሁ**...

169 አሁን በመካከላቸው ወደገባው ቃል ኪዳን ተመለስ፡ ወደ ቀስተ ደመናው ቃል ኪዳን... አያችሁ፡ ለኖህ ያ ቃል ኪዳን፡ ህይወቱ የዳነበት ኪዳን ነበረ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከራሱ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ቀስተ ደመና ነበር፡ እርሱም... አሁን፡ በደቂቃ ውስጥ የኖህ ቃል ኪዳን ምን እንደነበረ፡ አሳያችኋለሁ። ይህ ግን እግዚአብሔር ከራሱ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ነበር፡ አሜን፡ ቀስተ ደመና ነው።

170 እንግዲህ፡ ያኔ **ቃል ኪዳን** ማለት "ምልክት" እንደሆነ አውቀናል፡ ምልክት ነው። እግዚአብሔር "ምልክት" እንደሆነ እዚህ ጋር ተናግሯል፡ አይደል´ዴ? አያችሁ?

**ምን... አኖራለሁ... ቀስቴን** በደመና **ውስጥ አኖራለሁ፡** (ይህም በውሃ የጠፋው ዓለም፡ ከጠፋ በኋላ ነው፡ ከ—ከኖኅ በቀር፡ ሰጋ ለባሽ ሁሉ፡ ጠፋ።) **እና በእኔና በምድር መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል።**

171 "በእኔ እና በዓለም" አይደለም። **ዓለም** "ኮስሞስ" ነውና። አያችሁ? ይሄኛው ግን "በእኔ እና በምድር መካከል" ነው። እግዚአብሔርም፡ "ያቺን ምድርን እኔ አደረግኳት። እገለብጣት ዘንድ እና አደቅቃትም ዘንድ፡ እኔ ክፉ አደረግኩባት። እና—እና ምናልባት፡ ይ—ይ—ይ—ይ—ይህ ማድረግ አልነበረብኝም ይሆናል።" "እ—እ እጅግም አዝኛለሁ፡ በጣም አስቃቂ ነገር ነው፡" ይላል።

172 አሁንስ በቁጣው ሲመጣ ምን የሚሆን ይመስላችኋል? ኃጢአተኛ ወዳጄ ሆይ፡ ተስተካከል።

ኦህ፡ ያ ትዕይንት ሲፈጸም ለማየት ጠብቁ ትጉ፥
እንደገና እየመጣ ነው።

ታምናላችሁ?

እንደገና እየመጣ ነው።

እኔ ያንን ደስ ብሎኛል፡ እናንተስ?

ኦህ፡ ከጠላቶቹ እንደ አንዱ ትሆናላችሁን?

እኔ እንደዚያ መሆን አልፈልግም። ትፈልጋላችሁ? አይ፡ ወዳጄ። እንደገና ጠላት-... ወይም፡ ለእርሱ ጠላት መሆን፡ ከእርሱ ጋር መሆን መልካም ነው። ጠላት መሆን ግን!

ነውር አልባ ሁን ከውስጥህ፡ ነቅተህ ጠብቀው ለማየት
በአይንህ፡
ዳግም ይመጣልና ጌታህ። (እህም!)

173 አሁን፡ ቃል ኪዳን፡ የምን ምልክት? የምን ምልክት? ተቀባይነት ያገኘ መስዋዕት ምልክት። አሁን ዘፍጥረት 8፡20 እና 22ን ክፈቱ። አሁን፡ ዘፍጥረት 8፡20 እና 22፣ በጣም ጥሩ፡ በዚያው ገጽ ላይ አለ።

**ኖኅም ለጌታ መሠውያውን** ሠራ፥ **ከንጹሕም እንስሳ ሁሉ... ወሰደ፡ ከንጹሐን ወፎች... ም ሁሉ፡ በመሠውያውም ላይ መሥዋዕትን-አቀረበ።**

**ጌታም መልካሙን መዓዛ አሸተተ፥ ጌታም በልቡ አለ፡ ምድርን ዳግመኛ ስለ ሰው አልረግምም** (ምድርን አልረግምም)፥ **የሰው ልብ አሳብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና፥ ደግሞም ከዚህ ቀድሞ እንዳደረግሁት፡** ሕያዋንን **ሁሉ እንደ ገና አልመታም።**

174 አሁንም የመጨረሻውን ቁጥር እናንብብ፦

እና... **በምድር ዘመን ሁሉ፡ 3መዝራትና ማጨድ፡... ብርድና ሙቀት፡... በጋና ክረምት፡... ቀንና ሌሊት አያቋርጡም**። (ቃል ኪዳን።)

175 ዮሐንስ ያየውም ተመሳሳይ ነገር፥ ኢየሱስ፡ በሰማያት ተቀባይነት ያለው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው። በዙሪያውም በዙፋኑ ዙሪያ ቀስተ ደመና ነበረ፡ በመልኩም መረግድ፡ ህምበራዊ-አረንጓዴ ብርሃን በዙፋኑ ዙርያ ነበረ። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን!

176 ተመልከቱ! በዋነኝነት የኖህን ያቀፈ ነው... የኖህን ቀስተ ደመና በዋናነት በሰባት ቀለማት ያቀፈ ነው። ቀስተ ደመናው ሰባት ቀለሞች እንዳሉት ማንም ያውቃል። አሁን፡ ቀለሞቹ ምንድን ናቸው? ቀይ፡ ብርቱካንማ፡ ቫዮሌት፡ አይደለም፡ ቀይ—ቀይ፡ ብርቱካናማ... አረንጓዴ፡ ሰማያዊ፡ ኢንዲጎ፡ እና ቫዮሌት። የቀስተ ደመናው ቀለሞች እነዚህ ናቸው። አሁን፡ እዚህ ጋር ጥልቅ የሆነ ነገር አግኝተናል፡ እና በጣም እየረፈደ ስለሆነ ዋና ዋናዎቹን እዳስሳለሁ። አሁን፡ አስታውሱ፡ ብርቱካናማ፡ ወይም፡ ቀይ፡ ብርቱካናማ፡ ቢጫ፡ አረንጓዴ፡ ሰማያዊ፡ ኢንዲጎ እና ቫዮሌት።

177 አሁን፡ ሰባትን፡ ልብ ካላችሁት። ተከታተሉ። ሰባት ቀስተ ደመናዎች... ማለቴ፡ ሰባት ቀለማት፡ ሰባት-የቀስተ ደመና ቀለማት። ሰባት ቀስቶች ማለት ነው! ሰባት ቀስቶች፡ ሰባት መብራቶችን የሚያንጸባርቁ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት፡ እያንዳንዱ ብርሃን ወደ ሌላኛው የሚጠቀለል ብርሃን ነው። በቀይ፡ በቀይ ይጀምራል። ከቀይ በኋላ ብርቱካናማ ይመጣል፡ ይህም የቀይ ነጸብራቅ ነው። ብርቱካናማ ከሆነ በኋላ... በኋላ—ከብርቱካናማ ቢጫ ሲሆን፡ ቀይ እና ብርቱካናማ አንድ ላይ ተደባልቆ፡ ቢጫ ያደርገዋል። ከዚያም አረንጓዴ። አረንጓዴ እና ሰማያዊ ጥቁር ያደርገዋል። ከዚያ ኢንዲጎ ይመጣል።

ከዚያ ከኢንዲጎ የሰማያዊ ክፍል የሆነው፡ ቫዮሌት ይመጣል። ሃሌ ሉያ! አይታያችሁም? እግዚአብሔር፡ ሰባት-ቀለማት ካለው ቀስተ ደመናው ጋር፡ የገባው ቃል ኪዳኑ ነው፡ በሰባት የቤተክርስቲያን ዘመን፡ ምድርን እንደሚያድን፡ የገባው ሰባት የቃል ኪዳን ቀለማት ናቸው።

178 ምን ያደርጋል? አስታውሱ፡ ይህን ቀለሙ፡ የሰራው ከምድር ጋር ነው። አሁን ግን ተመልከቱ። ይህ ቀስተ ደመና፡ (በቀስት መልክ) ወደ ጎን እንደተዘረጋ ሆኖ፡ የምድርን ግማሽ ይሸፍናል። የኖህ ቀስተ ደመና ቀለም... የሚሸፍነው፡ የምድር ግማሽ፡ ብቻ ነው። ሊታያችሁ የሚችለው፡ በቀስት መልኩ ብቻ ነው። ዮሐንስ በመረግድ ቀለሙ **ባየው** ጊዜ ግን፡ የእግዚአብሔርን ዙፋን ሁሉ ከብቦት ነበር። ከዚህ በፊት ስለ ግማሹ ተነግሮ አያውቅም ነበር። እሱ የሚሸፍነው... በቃ... ምድርን ቀስት መልክ ናት፡ ግማሿ ብቻ፥ ይህም የቤተ ክርስቲያን ዘመናት ተምሣሌት ነው።

179 ዮሐንስ በዚህ ህምበር ቀለም፡ በህምበር ቀለም ባየው ጊዜ ግን፡ እንደ ክብ ጸዳል ዙሪያውን የሸፈነ ነበረ። ጸዳል! ማንነቱን ሙሉ፡ ባለ ህምበር ቀለም ጸዳል ከብቦት ነበር! አያችሁ? አንድ ቀለም፡ ከሁሉ በላይ፡ በሁሉም ዘንድ፡ እና በሁሉ ውስጥ የሚሰራ አንዱ አምላክ ሲሆን፡ ነገር ግን ሰባት አብያተ ክርስቲያናት አሉ።

180 ለምሳሌ ታላቁን አልማዝ እዩት። ድሮ ይፈልጓቸው ነበር... በአፍሪካ ውስጥ በየመንገዱ ልታገኟቸው ትችላላችሁ። ያልተቆረጠ ከሆነ፡ መያዝ አትችሉም። ያልተቆረጠ ይዛችሁ ከተገኛችሁ፡ ወዲያውኑ ይከሷችኋል፡ በመያዛችሁ ምክንያት ዕድሜ ልክ ይፈረድባችኋል። ልክ ስታገኙት፡ ወዲያው መልሳችሁ ማስቀመጥ አለባችሁ።

181 አሁን፡ ይህን አልማዝ ሲያገኙት... ኦህ፡ በጣም ጠንካራ ነገር ነው። እርባ-ቶን የሚያህል መፍጫ **እንዲህ** ቆሞ አይቻለሁ፡ ያንን ብሉስቶን እዚያ ውስጥ ይጨምሩታል፡ እየዞረ ያደቀዋል፡ ድንጋዩን እመድ ያደርገዋል፡ አልማዙን ግን አያደቀውም። ያን እርባ-ቶን **እዚህ** ጋር፡ በማዘቢያ ተንጠንጥሎ፡ በእነዚያ ትላልቅ ጥርሶች እየተሽከረከረ፡ ያን ድንጋይን ያደቀዋል፥ አልማዝ ግን ምንም ሳይሆን ያልፋል፡ እርባ-ቶኑን ያናጋዋል እንጂ። ኦህ! ከደቀቀ በኋላ በወንፊት ሲያልፍ፡ የሚያልፉትን ሌሎችን ያናፋቸዋል፡ ያጥባቸውና በስተመጨረሻ በረጅሙ ሃዲድ ይወስዳቸዋል።

182 የዚያ ታላቅ ኪምበርሊ አልማዝ ማዕድን አስተዳዳሪ በጸሎት ሰልፍ ካሉ አስተናጋጆቼ አንዱ ነበር፡ መልካም፡ ትሑት ወንድም ነው።

183 ከዚያ በኋላ ሶስት ፊት ገደማ በሆነው በውሃው ላይ፡ በሚፈስበት ሰፍራ፡ ኮስሞሊን፡ ይጨመርበታል። (ታውቁታላችሁ፡ ይህ—ይህ ነገር ማን ነበር የምትሉት? እ... ሚዳ፡ ካቢኔቱ ላይ ጃር ውስጥ ያስቀመጥነው ነገር ምንድነው? ቫዝሊን!) እና ከፍ ካለው ሰላይድ ላይ፡ ያንን ቫዝሊን፡ አንድ ኢንች ጥልቀት ይጨመራል። እናም ይወርዳል፡ እና ያስተውሉ፡ ድንጋዩ በመጣ ቁጥር፡ ወዲያውኑ ከቫዝሊኑ ላይ ይንከባለል፥ አልማዝ በላዩ ላይ ሲመጣ ግን፡ ይጣበቃል። አልማዝ ደረቅ ስለሆነ ከዚያ ጋር ይጣበቃል። እነዚያን ነገሮች ሲለቅሟቸው አይቻለሁ፡ ደቃቆቹ ሳይቀር፡ በመነጽር ይለዩአቸዋል። እና

ምን እያደረጉ እንደሆነ ጠየኳቸው፡ ለአሜሪካ እንደሚሸጡዋቸው ነገሩኝ ለነ ቪክትሮላ ኒድልስ እና ለሌሎች ይሸጡታል፡ እነሱ እያገኙበትም፡ አያችሁ።

184 ግን እነዚያ ትልልቅ አልማዞች፡ አሁን፡ በዚያ ባሉበት፡ እንደ አንድ ትልቅ ኳስ ናቸው። ነገር ግን... ይወስዷቸውና ኤሌክትሪክ መሣሪያዎች በመጠቀም ይቆርጧቸዋል፡ የተቆረጠ አልማዝ ይሰራሉ። እነዚያን የሚቆርጡበት ምንያት፡ የካራቱ ደማቅ ቀለሞችን ለማንጸባረቅ ነው፡ ደግሞም፡ ሰባት ቀለማት ያንጸባርቃል።

ኦህ፡ ይህ ኢየሱስሰ...

185 ኦህ፡ ብዙ ገንዘብ ሊኖራችሁ ይችላል፡ መርከብ ሙሉ ካዲላክ ባለቤት ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ ምናልባት የትልቅ ትልቅ መጋዘን ወይም የአንድ ካቴድራል ፓስተር፡ ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ ነገር ግን፡ ወንድሜ ሆይ፡ ያንን ዕንቍ፡ ያንን አልማዝ፡ ስታገኘው፡ ሰው ስለዚያ ሃብቱን ሁሉ፡ ያለውን ሁሉ ይተዋል፡ ይሸጣል።

186 ሰነፏን ድንግል ተመልከቷት። ኦህ፡ ምን አደረገች? ዘይት ለመግዛት አንድ ነገር መሸጥ ነበረባት። ምን መሸጥ ይጠበቅባታል? የድሮ የሐይማኖት ሰርዓቷ እና ተቋማቶቿ እና ሌሎች ነገሮች። ያን ታላቅ ዕንቍ የሆነው ክርሰቶስን፡ ክርሰቶስ፡ ለማግኘት ያላትን ሁሉ ሸጠች። ኢየሱስ፡ ያ አካል... [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ? ... በእነዚህ ማለዳዎች አንድ ቀን፡ ባቡሩ ሲመጣ ወደ ሰማይ መሄጃ ትኬት ይዣለሁ። አቤት፡ እንዴት ያለ በረከት ነው!

ኦህ፡ ፍጹም ብሩክ ምንጭ
ኃጢአቴን ያጠበው፡
ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርሰቶስ ደም ብቻ ነው።

187 እንጋፋነት አይደለም፡ ሌላ ትልቅ ነገርም አይደለም፡ ምንም አይደለም፡ ባለጸግነትም አይደለም፡ በፍጹም—በፍጹም አይደለም፡ ብቻ ብሩክ ምንጭ ሰጠኝ። ይበቃኛል!

ባመጣሁት አይደለም በእጄ፡
መስቀልህ ላይ እንዲሁ ወጥቼ።

188 ያን ታላቅ ዕንቍ! ምን ነበር? ፍጹም ነበር። እግዚአብሔር በትልቁ ማሽን ውስጥ ያአስገባው በሠላሳ-ሦስት ዓመት ተኩል ዕድሜው ነበር፡ በወሰደው ጊዜም እነሆ ቅርጽ ያሰይዘው ጀመረ። ቈረጠው፡ ፈጨው፡ ቀጠቀጠው።

**... እርሱ ስለ መተላለፋችን ቈሰለ... ስለ** በደላችን **ደቀቀ፥ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር፥ በእርሱም ቁሰል እኛ ተፈወሰን።**

189 አምላክ በዚያ ፍጹም ሰው ላይ ምን አደረገ? በዓለም ደረጃ አንድ ብቻ ተገኘ፡ በመላው ዓለም ውስጥ አንድ ብቻ አለ፡ ያውም እሱ ነበር! እግዚአብሔርም ከዚህ ወቀረው፡ "እርሱ ስለ በደላችን ቆሰሏል።" ኃጢአተኛ ስለሆንኩ፡ የሰባት ቤተ ክርሰቲያን ዘመን የቀሰተ ደመና ብርሃን በላዬ ላይ እንዲበራ አደረገ፡ ይህም ስለ መተላለፌ መቁሰሉን አውቅ ዘንድ ነው።

190 ባለ ሰባት-ቀለም ቀስተ ደመናችሁ ይህ ነው። "እርሱ ስለ በደላችን ደቀቀ፡ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነው፡ በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።" እግዚአብሔር ቈረጠው፡ ቀጠቀጠውም፡ ሰባበረውም፡ ቈረጠውም፡ በሚሞተውንም ቍስል እራሱን፡ የኀጢአት ስርየት፡ ደስታ፡ ሰላም፡ ትዕግስት፡ በጎነት፡ የዋህነት፡ ጨዋነት ያንጸባርቅ ዘንድ ነው። ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት በህዝቡ ውስጥ የሚያንፀባርቁ ሰባት የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ብርሃን በዚያ ሰው አካል ውስጥ እንዲያበራ፡ እርሱ ደቀቀ፡ መላውን ዓለም ይቤዥ ዘንድ ተቀረጸ እንዲሁም ተስተካከለ፡ "ከምድር ከፍ ከፍ በተደረግኩ ጊዜ፡ ሁሉንም ሰው ወደ እኔ እስባለሁ።" እነዚያን የቀስተ ደመና ቀለሞች ሲያንጸባርቁ ተመልከቷቸው።

191 ዮሐንስ ሲያየው ግን፡ ምን ነበር? የቤዛው ቀን አልቆ ነበር። ሁሉም ነገር አልቆ፡ ወደ መጀመሪያ ሁኔታው፡ ሀምበር ቀለም ተመልሶ አየው። የአለምን ግማሽ ብቻ ሳይሆን፡ ብቻ... ፀሐይ፡ ስትዞር፡ እያችሁ፡ በዓለም ላይ በአንድ ጊዜ በግማሽ ብቻ ታበራለች። ዮሐንስም ባየው ጊዜ፡ የኢያስጲድንና የሰርዲዋስን ዕንቍ ያይ ዘንድ ተቀመጠ፡ ሀምበር ቀለሞች፥ ሁለቱም ሲቀላቀሉ፡ ሀምበር ታገኛላችሁ። "በዙፋኑ ዙርያ ሀምበር ቀለም ነው!" ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ እ— እላችኋለሁ፡ እንደው... ብዙ ብዙ ማለት እንችላለን።

192 ሰባት መንፈሶች፡ ሰባት ቀለሞች፡ ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ ሰባት አገልጋዮች፡ ሰባት መብራቶች፡ ሁሉም ነገር በሰባት ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር ፍጽምና "በሰባት" ነው። እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሠራ፡ በሰባተኛው ቀን፡ ዐረፈ። ዓለም ለስድስት ሺህ ዓመታት ይኖራል፡ በሰባተኛው ሺህ የሺህ አመት መንግስት ነው።

193 አስተውሉ፡ **በግማሽ ክበብ**፡ "ግማሹ ገና አልታወቀም።" አሁን፡ በእርግጥ እነዚህ ነገሮች አንድን ነገር ያመለክታሉ።

194 አሁን፡ በዘጸአት 23፡13 እና በዕብራውያን 6፡12 ላይ፡ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባ በራሱም ማለ። ዕብራውያን ፡13 ሲናገር፡ ወይም 9 ላይ፡ ፡13 ላይ፡ "በራሱ ማለ" ይላል። ለአብርሃምና ለይስሐቅ በነገራቸው ጊዜ ከእርሱ ጋር የዘለአለም ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ፡ ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን አደርጋለሁ ብሎ ለአብራሃም በነገረው ጊዜ፡ በእርሱ ይምል ዘንድ ከእርሱ የሚልቅ አንድም አልነበረም። እግዚአብሔር...

195 ቃል ኪዳን የሚፈጸመው ሁልጊዜ በመሐላ ነው፥ ስለዚህ ማናችሁም ቢሆን... መሐላ ከእናንተ በሚበልጥ አካል ታደርጋላችሁ፥ በእናት ትምላላችሁ፡ በአገር ትምላላችሁ፡ በሆነ ነገር ትምላላችሁ፡ በእግዚአብሔርም ትምላላችሁ። ከእናንተ በሚበልጥ አካል ካልሆነ በቀር መሐላን አትፈጽሙም።

196 ከእግዚአብሔርም የሚበልጥ ማንም ስላልነበረ፡ ስለዚህም ራሱ በራሱ፡ መሐላ ፈጸመ። አሜን! ይህን ቃል ኪዳን አጸናለሁ ብሎ በራሱ ማለ። ኣሜን። ኦህ! ይገርማል! "የአብርሃምን ዘር እጠብቃለሁ" በማለት፡ በራሱ ማለ። የአብርሃም ዘር ለአህዛብ ምንድን ነው? የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ የአብርሃም ዘር ነው። በራሱ ማለ፡ "እያንዳንዳቸው፡ ሁሉንም፡ አስነሣቸዋለሁ። የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ ወደዚህ ምድርም እመልሳቸዋለሁ።" ምን ማድረግ አለብን-... ስናስበው?

197 ስለዚህ እርሱን በአምበር ቀለም፡ በአረንጓዴ ክብ ቀስት አይተነዋል። ይህ አረንጓዴ፡ አረንጓዴ ምንን ይወክላል? ህይወትን። አረንጓዴ ዘወትር ለምለም ነው፡ ህይወት፡ ሁሌም አረንጓዴ ሆኖ ይኖራል። ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር በኦሪት ዘፍጥረት መሐላ እንደ ገባ፡ ቃል የገባው ነገር፡ "ይህ አልደግመውም... " በማለት (ቀስተደመናውን በሰማይ ላይ አደረገ።) ከእንግዲህ "ይህን ዓለም በውኃ እንደማያጠፋ ቃል ገብቷል።" የአብርሃምንም ዘር በሙሉ እንደሚያሰነሣ ይህች ዓለምም ከባባድ የሆኑ ፍርዶቿን ትቀበላለች በማለት፡ እነሆ በራሱ ቃል ገብቷል እንዲሁም ምሏል፡ ። ወደፊት በምንማራቸው ትምህርቶች ላይ የምናሳልፈው ፍርድ፡ ይህች ዓለም እንደምትፈነዳ እና ወደ እሳተ ጎመራ እንደምትለወጥ፡ ከላይ እስከ ታች ተገልብጣ፡ እንደምትደቅ ያሳያችኋል። ነገር ግን በራሱም ምሎ እንደገና እንደሚያስተካክላት፡ ከዚያም ልጆቹን ለሺህ ዓመት መንግስት በምድር ላይ እንደሚያስቀምጣቸው እንደማያጠፋት ማለ። ኦህ፡ ማይ!

> ግሩም የሺ ዓመት መንግስት መምጣት እንናፍቃለን፡
> ጌታችን ሲመጣ የምትጠብቀው ሙሽራ የሚወሰድበት
> ዘመን፥
> አቤቱ! ልቤ ይናፍቃል፡ የነጻነት ቀን፡
> ወደ ምድር ሲመጣ የሚያድነን።

198 አቤት፡ ያንን ቀን ለማየት እንዴት ጓጉተናል፡ ታላቁ የሺ አመት መንግስት እንደሚመጣ ቃል ገብቷል። ሌላው በዚያ ነገር፡ የተከበበበት ምክንያት፡ እርሱ ቃል ኪዳን-የሚጠብቅ አምላክ ስለሆነ ነው። ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል!

199 ለማንኛውም፡ አሁን የሚቀጥለውን ጥቅስ እንመልከተው። አቤት፡ አንድ ብቻ እንጨምራለን፡ ለመጨረስ አስር፡ ወይም አስራ አምስት ደቂቃዎች ቀርተውናል። ደከማችሁ እንዴ? እንድንቀጥል ትፈልጋላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] በጣም ጥሩ፡ 4ኛው ቁጥር እንውሰድ፡-

> **በዙፋኑ** ዙሪያም **ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ** ለብሰው **በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው፥ ሀያ አራት** ሽማግሌዎች **ተቀምጠው ነበር።**

200 ይህን ቁጥሩን በሙሉ ላናየው እንችላለን። ለማንኛውም፡ እንጀምር። 4ኛው ቁጥር፡ አሁን ተመልከቱ፡ ዮሐንስ ያ የመረግድ ቀለም፡ በዙሪያው ባየው ጊዜ፡ ቀስተደመናዎች፡ እና ሌሎች፡ ምን ማለት እንደነበሩ፡ ሌሎች ቀለሞች ሁሉ አይተናቸዋል። አሁን፡ በ 4ኛው ቁጥር፡ እዚህ ላይ ከሁሉ በፊት የሚናገረው፡ ቁጥር 4 ላይ-...

> **በዙፋኑ** ዙሪያም...

201 ተመልከቱት! ይህ በጣም የሚያምር ምስል ነው፡ እንዳያመልጣቹ፡ "ዙፋኑ።"

202 ታውቃላችሁ፡ እስኪ ወደ ሙሴ እንመለስ። ሙሴ... ዘልቀን ለማየት ጊዜ ስለሚያጥረን፡ የምለውን ብቻ ውሰዱ። ሙሴ፡ በሲና ተራራ ራእዩን በሰጠ ጊዜ...

203 ይህ ከእንግዲህ በኋላ የጸጋ ዙፋን እንዳልነበረ ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። በዚያ፡ ደሙ ተወስዶ ነበረ፡ መስዋዕቱ እንደገና ተመልሶ ተቀበሉት፡ ደሙም ከስርየት መክደኛው የራቀ ነበረ። ነጎድጓድና መብረቅ ስለ ወጣ አሁን የፍርድ ወንበር ሆነ። ልክ ነው?

204 አስታውሱ፡ ልክ እንደ ሲና ተራራ ነበር። ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ሲወጣ፡ ምን ሆነ? ነጎድጓድ፡ መብረቅ። ላም ወይም ጥጃ፡ ወይም በግ፡ ወይም ማንም፡ ተራራውን ቢነካ እንኳ ይሞታል። መጽሐፍ ቅዱስ "ሙሴ እንኳ እስኪፈራ ድረስ ነውጡ ታላቅ ሆነ፡" ይላል። ሙሴን-... እንዲህ አለው፡ "በተቀደሰ ስፍራ ነህና፡ ጫማህን አውልቅ።" ልጆቹን ወደ ርስታቸውንም ይወስድ ዘንድ፡ እና ያካፍል ዘንድ የነበረው ታላቁ አርበኛ ኢያሱ፡ ወደ ተራራው መውጣት የቻለው ግማሽ ያህል ብቻ ነበረ።

205 እነሆ ሙሴ ግን የእግዚአብሔርን ብልጭታና መብረቅ የመረግድም ቀለማት በዙሪያው ሆኖ በዚያ ቆመ፡ ትእዛዛት ሲጻፉ እየተመለከተ ነው። በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ፡ ያ ድምፅ መልሶ ሲናገር ይሰማ ነበር፡ "ሙሴ ሆይ፡ የት ነህ? በተቀደሰ ስፍራ ነህና፡ ጫማህን ከእግርህ አውልቅ።"

206 የፍርድ ወንበር፡ ነበረ አሁን፡ ከተዋጁት በቀር ማንም በዚያ ሊቆም አይችልም። ኃጢአተኛ በጭራሽ ሊቀርብ አይችልም (አልቋል)፡ የፍርድ ወንበር ሆኗል። በጣም ጥሩ።

207 ሙሴ፡ በሰማይ እንዳየው መሰረት፡ ነገሮችን በምድር ላይ ሰራ፡ ማደሪያውን አደረገ። ያንን እናውቃለን፡ አይደል? ጳውሎስም ተመሳሳይ ነገር ሲያደርግ እናገኘዋለን። ሊሆን የተገባው... ዕብራውያን 9፡23 ላይ፡ ሙሴ ነገሮችን ሠራ። ጳውሎስም በራእዩ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ (ይህን ታላቅ የዕብራውያን መጽሐፍ አስተማረ)፡ ሙሴ ያየውን በራእዩ አይቶ መሆን አለበት፡ ምክንያቱም እንደተናገረው (ያን ድንቅ የዕብራውያን መጽሐፍ አስተምሯል)፡ ክርስትና እንዴት የብሉይ ኪዳን ተምሳሌት እንደነበረ አስተማረ። ይህ-... ጳውሎስ፡ ታላቅ አስተማሪ ነበረ። እንግዲህ፡ **ያኔ** ዙፋኑ ያ ነበረ። ከዚያም በ...

208 እስቲ አሁን... ይህን ለማለፍ ፈልጌ ነበር... ቢሆንም ግን፡ ዝም ብዬ ማለፉ፡ አይጠቅምም። ጥቁር ሰሌዳው የት አለ? ወሰዳችሁት እንዴ? ተመልሷል፡ ዶክ? ይሁን፡ ምናልባት ከዚህ እንድታዩት ላደርግ እችላለሁ። አ—አ... አሁን፡ ደብተር እና እስክርቢቶ ያዙ፡ እዚህ ጋር አንድ ነገር እናገራለሁና። ዛሬ ጠዋት ቁጭ ብዬ ሳ—ሳለሁ የሆነ ነገር ወደ እኔ መጣ። አሁን ካስተዋላችሁ፡ ያደረግኩትን ልንገራችሁ፡ ከዚህ ከጀርባው ላይ ሳልኩት። አያችሁ? መንፈስ እንዳቀበለኝ ወዲያው ሳልኩት፡ አያችሁ፡ ምን እንደሚሆን እዚህ በስዕል አስቀመጥኩት። ነገር ግን እ—እዚህ ጋር አንድ ነገር ማለት እፈልጋለሁ።

209 አሁን፡ እግዚአብሔር፡ በዙፋኑ ላይ ሲቀመጥ፡ ያኔ ፈራጅ ነው። ልክ ነው? ዳኛ መቼ ነው የሚፈርደው? ወደ ፍርድ ወንበር፡ ወደ ዙፋን ሲወጣ። አሁን፡ ብሉይ ኪዳን እንዴት እንደተሠራ እንድትመለከቱ እፈልጋለሁ፡ ወደ ዙፋኑ የሚቀርቡት ሸንጎዎች እንዴት እንደተሰሩ፡ እና ዮሐንስ እንዴት እንዳየ። ዛሬ ጠዋት፡ ሙሉ በሙሉ ልናየው አይቻለንም። ይሁን እንጂ ዮሐንስ ወደሱ መቅረቢያ አንድ አይነት አጸድ አየ፡ ወደ እርሱ የሚቀረብበት አጸድ። አሁን፡ ኦህ፡ ይህንን በጣም ወደድኩት።

210 አሁን፡ በብሉይ ኪዳን፡ ሰዎች የሚሰበሰቡበት “ጉባኤ፡” የሚሉት ነገር ነበረ። ከሁሉ በፊት፡ ጉባኤው፡ ወደዚያ ለመግባት፡ ከመምጣታቸው በፊት፡ በውጪኛው አጸድ ዘንድ ከታረደው ደም ስር፡ ማለፍ ይኖርባቸዋል። በመጀምሪያ ቀይ ጊደር ወደሚታረድበት የመንጻት ውሃ ወዳለበት፡ ወደ መንጻት ውሃ ይመጣሉ። ይህ ማለት መጥቶ ቃሉን የሚያዳምጠው ኃጢአተኛ ነው።

211 ይህ ታላቅ የአይሁድ ራባይ በዚያ ላይ ሰሰብክ ሰምቶኝ ነበር፡ ወደ ጌታ የመጣው... በቱልሳ። በቱልሳ ላይ፡ ነበር። በቱልሳ ኦክላሆማ፡ ነበርን። እና የመጣው፡ እንደተመልካች ነበር። ከጉባኤው በኋላ ወጣና፡ እንዲህ አለ፡ “አውቃለሁ፡” አለ... በዓለም ካሉ ሰባቱ ምርጥ ራባዮች አንዱ ነው። ወደዚያም መጥቶ፡ እንዲህ አለ፡ “እነዚህ ‘ጴንጤቆስጤ፡’ የሚሏቸው... ክርስቲያን ቢዝነስ ሜን ማየት እፈልጋለሁ። ወደዚያ ሄጄ፡ ቁጭ ብዬ፡ መስማት እፈልጋለሁ።”

212 እግዚአብሔርም በዚያ ስለ ቀይ ጊደር መሥዋዕት እንድናገር ባዘዘኝ ጊዜ፡ ከአገልግሎት በኋላ አንዳንድ ወንድሞችን አግኝቶ፡ እንዲህ አላቸው፡ “ሰውየውን ማግኘት እፈልጋለሁ። ትምህርት እንኳን እንዳልተማረ አውቃለሁ ነገር ግን... ” አላቸው፡ “እኔ እነዚያን የተለያዩ አቀራረቦችን እና መሰል ነገሮችን የማውቅ የአይሁድ ራባይ ነኝ፡” “በህይወቴ ይህ አይቼ አላውቅም፡” አላቸው። “አይቼ አላውቅም፡” አለ።

213 አሁን በዚህ ሰዓት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ፡ ከቦታ ቦታ፡ ወንጌልን እየሰበከ፡ እና እየዞረ ያለ የጴንጤቆስጤ ራባይ ነው። እራሱን “የጴንጤቆስጤ ራባይ፡” ብሎ ይጠራል። በቀደም ለት በወንድም ጃክ ዘንድ በተገናኘን ጊዜ፡ ወደ ዋሺንግተን ዮሪ ሆቴል ሄደና፡ ሴቲቱ ሰለምታውቀው፡ እንዲህ አለችው፡ “ራባይ፡” አለችው፡ “ጥሩ ክፍል አዘጋጅተንልሃል፡ ይሁን እንጂ” “በውስጡ ቴሌቪዥን የለውም፡” አለችው።

214 እርሱም እንዲህ አለ፡ “እነዚያ ነገሮች ‘ገሃነመቪዥን፡’ ናቸው እርቁልኝ! ምንም ቢሆን፡ አልፈልጋቸውም፡ ቢገባም፡ ጣይው እልሻለሁ።”

“ራባይ!” አለችው፡

“የጴንጤቆስጤ ራባይ ነኝ፡” አላት። ሃሌ ሉያ!

215 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አንተ ወደ እስራኤል፡ በምትሄድ ጊዜ፡ አብሬህ መሄድ እፈልጋለሁ፡” አለኝ። “ወደ ህዝባችን ማድረስ እንችላለን፡” አለኝ።

216 እኔም አልኩት፡ “አሁን አይደለም፡ ራባይ፡ አሁን አይደለም። ጊዜው ገና ነው፡ አሁን አይደለም፡ ትንሽ ቆይ።”

217 አሁን፡ እነዚህ ቅዱስ ሰፍራዎችን ተመልከቷቸው። አሁን፡ ወደ አጸዶቹ ስትመጡ፡ አንደኛው አጸዱን ታገኛላችሁ፡ ውጪኛው አጸድ። ቀጥሎ ያለው ከናስ የተሰራ፡ መሰዋዕት የሚቀርብበት፡ መሥዊያው ነው። ከዚያም ከናሱ መሠዊያ ውጭ፡ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መግቢያ መጋረጃ ተሰቅሎበታል፡ በዚያም የሰርየት መክደኛው ነበረ፡ በዚያ ኪሩቤል ነበረ። በሚቀጥለው ትምህርታችን ላይ መግባት የምፈልገው ክፍል ያ ነው፡ እነዚያ ኪሩቤሎች የሰርየት መክደኛውን የሚጋርዱ ናቸው። ኦህ፡ ማይ! እ... አንድ ወር ሙሉ በዚህ ርዕስ መቆየት እንችላለን፡ እያችሁ፡ በእነዚህ ኩሩቤሎች።

218 አሁን፡ አሁን ወደ ውስጥ ሲገቡ አስተውሉ። ጉባኤው **ወደዚያ** ይመጣሉ፥ ካህናቱም **እዚህ** ይቆማሉ፥ ሊቀ ካህናቱ ግን ደሙን ይዞ፡ በዓመት አንድ ጊዜ፡ **ወደዚያ** መግባት ይችላል።

219 እርሱም ልዩ አለባበስ ይለብሳል፡ የተለየ አይነት ልብስ፥ አንዱ በአንዱ ላይ፡ የሮማን ቃጭሎች የተንጠለጠለበት ልብስ። በዚያም ሲንቀሳቀስ፡ የተለየ እንቅስቃሴ ያደርጋል። እየተራመደ፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር፡ እያለ ይንቀሰቀሳል። ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር፡" እነዚያ ሮማኖች እና ቃጭሎች በአንድነት "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ!" እያሉ ይዘምራሉ፡ ለምን? ደሙን ይዞ፡ በፊቱ በመቅረብ፡ የቃል ኪዳኑን ደም በእጁ ይዞ፡ በፊቱ በእግዚአብሔር ይቀርብ ነበር።

220 ለየት ያለ ሽቱ (ኦህ፡ ማይ!) ይቀባ ነበር። ልብሶቹም መንፈስ ቅዱስ-በተሞላ እጆች የተሰሩ ናቸው፡ የተጸፉ እጆች ይሰሩለት ነበር። የሳሮን ጽጌረዳ፡ የቅብዓት ዘይት፡ በራሱ ላይ ይፈሳል፡ ከነንጉሳዊ ሽቱ ጋር በጺሙ በኩል ወደ መላ ሰውነቱ ይወርዳል፥ ሮማን እና ቃጭል ጋር፥ ነውር የሌለበት የጠቦት ደም ይይዛል፥ በዚያ በውጭ ባለው መጋረጃ ለመቅረብ አይደፍርም፡ በዚያው በቆመበት፡ ሊሞት ይችላልና። ስለዚህ በልዩ መንገድ እንቅስቃሴ እያደረገ፡ ይራመዳል፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር። ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡" እያለ (ወደ እግዚአብሔር ይቀርባል) "ለእግዚአብሔር። ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ!"

221 ወደዚያም ሄዶ፡ ደሙን በዓመት አንድ ጊዜ በሰርየት መክደኛው ላይ ያቀርባል። በዚያ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ፡ የእስራኤል ልጆችን የመራቸው፡ የእሳቱን አምድ፡ የወረደውን የህምበር ቀለም፡ የአርያምን ክብር የማየት ዕድል ያገኛል። ማንም እንዳያየው መቅደሱን ይታጠናል። ሙሉ ሉሙሉ ደመና እስኪሆን ድረስ የእግዚአብሔር ክብር ይሞላው ነበር። ወደ ራሱም መጥቶ፡ ከመጋረጃው ጀርባ ወደ ሰርየት መክደኛውም በቅድስተ ቅዱሳን ይቀመጣል። "እጅግ የተቀደሰ ሰፍራ፡" ቅድስተ ቅዱሳን፡ ይባላል። እና በተለየ አለባበስ ይለብሳል፡ የተለየ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡ የተለየ ቅባት ይቀባል። ወደዚያ ለመግባት የተለየ ሰው ነበረ። አቤት ጉባኤው እንዴት ይቀናበት ይሆን!

222 ኢየሱስ ሲሞት ግን፡ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ተቀደደ። ሊቀ ካህናት ብቻ ሳይሆን፡ "የሚፈልግ ሁሉ" ተመሳሳይ የአርያም የክብር ቅባት ሊኖረው ቻለ በተቀደሰ ሕይወት መኖር ይችላል፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር፡" እያለ በፊቱ ባለው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል፡ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ይችላል። ከእርሱ ጋር ወሰዶ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ይህ ታሞ የተኛ ሰው፡ ወንድሜ ነው። አሁን ለመሞት፡ በሞት አፋፍ ላይ ደርሷል። አቤቱ 'ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለአንተ ጌታ፡' እያልኩ ወደ አንተ እቀርባለሁ።"

"ለምን? "

"እንደ ሊቀ ካህናት።"

"ስለ ምን? "

"ስለ ወንድሜ። 'ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር።'"

223 ይኸው! የእለት ጉዟችሁ፡ የእለት ንግግራችሁ፡ የእለት ባህርያችሁ፡ ልባችሁ፡ ነፍሳችሁ ሁሉ፡ ይህ ነው፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር።"

መራራ ስር፡ ወይም ሌላ ነገር ፈጽሞ የለም፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር። ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር፡" ስለ ወንድማችን ስንማልድ ማለት ነው። የወደደ ሁሉ ይምጣ፡ የተቀባው ሁሉ፡ ደሙን ከፊቱ ይዞ መቅረብ ይችላል፡ በፊቱ የሚሄደው ደም፡ "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና ለእግዚአብሔር፡" እያለ ይወዛወዛል።

224 እንግዲህ፡ ውጩኛው አጸድ፡ ቅድስት ይህ ነው። እና ቅድስተ ቅዱሳንም፡ በምድር ላይ የነበረ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይህ ነበረ። ተመልከቱ፡ በሰማያት በነበረው ምሳሌ የተሰራ ነበረ። አሁን፡ ወደዚያው ወደ ቅዱስ ቃሉ እንደገና እንመለሳለን። ኦህ፡ በራእይ መጽሐፍ ሁሉ ስንመላለስ፡ እንደገና በቀጥታ ወደዚህ መመለስ እንችላለን። እያችሁ?

225 አሁን እሱ… ዮሐንስ፡ ዮሐንስ የቆመው ምን ላይ ነበር? አጸዶቹ ላይ። ስዕሉን በደንብ እንድታገኙት እስኪ ትንሽ ዘልቀን እናነባለን፦

> **ከዙፋኑም መብረቅና… ድምፅ…** ነጐድጓድም ይወጣል፦ **ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር** (ወደዚያ እስክንገባበት ድረስ ጠብቁ!) **እነርሱም በዙፋኑ ፊት የሚበሩ፡ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።**

226 የእግዚአብሔርን ብርሃን ወደ ቤተክርስቲያን የሚያንጸባርቁ፡ ከትምህርት ቤት ሳይሆን፡ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ዙፋን ላይ፡ ከአንዳንድ ቢሾፖች ዘንድ ሳይሆን፡ የትንሣኤውን ኃይል በመግለጥ፡ ከእግዚአብሔር ዙፋን ነው፡ ትናንትናም ለዘላለምም ያው መሆኑ እየመሰከሩ፥ ብርሃን የሚያንጸባርቁ ሰባት ከዋክብት፡ የአርያም ብርሃን፡ ከአርያም ክብር ከቅድስተ ቅዱሳን ዘንድ በዚያ ያበሩ ነበር። በእነዚያ መቅረዞች ራስ ላይ፡ እሳት የተለኮሰባቸው ሰባት መብራቶች ነበሩ፡ እነዚያም ከትንሳኤው ኃይል የተነሣ፡ የገዛ ብርሃኑ፡ የገዛ ቀለማቱ፡ በቀጥታ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያበሩ ነበር። አሜን! እህም!

> **በዙፋኑም ፊት… ብርሌ** የሚመስል **የብርጭቆ ባሕር ነበረ፥ በዙፋኑም መካከል፡** በ**ዙፋኑም ዙሪያ፡ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንስሶች ነበሩ።**

227 በፊታቸው እየሄደም እነዚህን… እንሥሶች ማሳየት ጀመረ፡ ሕዝቅኤል ካየው ጋር ተመሳሳይ ነው፥ እነዚህም ጠባቂዎች… አንደኛው እንደ ሰው፡ አንደኛው አንበሳ፡ አንደኛው ደግሞ እንደ ንስር ናቸው። ምን ነበር? አሁን፡ ስናመጣቸው፡ እና ያንን የይሁዳ ነገድ አንበሳ እና በአራቱ ግድግዳዎች አቅጣጫ ሰፍረው ይህንም የሰርየት መክደኛ ሲጠብቁ የነበሩ፡ እነዚያ ልዩ ልዩ ነገሮች፡ በየነገዶቻቸው ስናወጣቸው አሁን ተከታተሉ። ኦህ፡ እንዴት ያለ ምስል ነው! ኦህ፡ አቤት… ወደፊት ጥሩ ቀናት አሉን።

228 አሁን፡ እንደምናየው ሁሉ፡ ይህ ሙሴ በምድር በጥላ ያስቀመጠው፡ በሰማያት ያለ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው፡ የፍርድ ዙፋኑ በምድር ላይ በቅዱስ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ስለተመሰለ፡ ይህ የእግዚአብሔር ዙፋን ነው። እግዚአብሔር… እስራኤላውያን ሁሉ ምሕረትን ለማግኘት ወደዚያ ቦታ ይመጣሉ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚገናኛቸው በፈሰሰው ደም ስር ብቻ ነውና።

229 አሁን፡ በደንብ ስሙኝ። ይህ የአርያም ክብር አንድ ቀን ከዚያ ከሰርየት መክደኛ ተነሳና፡ በሌላ ማደርያ ውስጥ ገባ (አሜን!)፡ ይሄኛውም፡ የእግዚአብሔር ፍርድ ወንበር ነው። "ፍርድ ሁሉ ለልጁ ሰጠው እንጂ አብ በማንም አይፈርድም።" ዋው! "በእኔ ላይ ብትናገር፡ ይቅር ይባልልሃል፡" ሌላው ላይ ብትናገር—የሚመጣው ላይ፡ ሌላ የምሕረት ወንበር ላይ። "ብትናገር... የሰው ልጅ ላይ ብትናገር፡ ይቅር እልሃለሁ፥ እነሆ አንድ ቀን ግን መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ልብ ውስጥ ለማደር ይወርዳል፡ ያኔ እሱን የሚጻረር አንዲት ቃል ብትናገር ፈጽሞ ይቅር አትባልም።"

230 ፍርዱ፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ እና እየጠነከረ ይሄዳል፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ኃጢአተኞች ወደ እርሱ እንዲመጡ ለማስታረቅ እየሞከረ፡ ያለማቋረጥ ትዕግሥቱን እየጨረሰ ይሄዳልና። በመጀመሪያ፡ በከዋክብት ውስጥ እያበራ በሰማያት ውስጥ ነበር። ሁለተኛው፡ በአርያም ክብር በኩል እያበራ በምድር ላይ ነበር። ቀጥሎም፡ መጥቶ ሥጋ ሆነና አሁንም ትዕግሥቱን ለብሶ፡ በእኛ አደረ። ከዚያም ሰውን በደሙ ዋጀና፡ በመንፈስ ቅዱስም አምሳል ወደ ቤተክርስቲያኑ መጣ፡ ስለዚህ እሱን የሚጻረር መናገር ማለት በቃ፡ ያለቀለት ነገር ነው።

231 አሁን ርዕደ መሬቱ ከየት እንደሚመጣ ማየት ይቻላል። ጊዜው ሳለ፡ አያስተውሉም። ሰዎች ምን ማለት እንደሆነ ሊረዱት አይችሉም።

232 አሁን፡ የመጀመሪያው ዙፋን በሰማይ ዘንድ፡ የፍርዱ ወንበር ነበር። ሁለተኛው ዙፋን በክርስቶስ ነበር። ሦስተኛው ዙፋን በሰው ውስጥ ነው።

233 አሁን፡ ይህ እዚህ ላይ የሳልኩትን ትንሽ ነገር ልውሰድና። እንዲህ እናደርጋለን... ጥቁር ሰሌዳ ቢኖረኝ፡ ምናልባት በበለጠ መልኩ እንድትረዱት ማድረግ እችል ነበር። አጸዶቹን እንስላቸዋለን፡ እንደ ቀለበት ክብ፡ ወይም በየአንዳንዳቸው፡ እንዲህ እናደርጋቸዋለን። አሁን እንዲህ እናደርጋለን... ይመስለኛል፡ ምናልባት **እንዲህ** ሳይሻል አይቀርም፡ እንዲህ አድርገን አጸዶቹን እንሰራቸዋለን።

234 አሁን፡ ሰው ምንድን ነው? ሦስታዊ ፍጥረት ነው፡ ሰጋ፡ ነፍስ፡ እና መንፈስ። ስንቶች ይህን ታውቃላችሁ? የእግዚአብሔርን አቀራረብ ተመልከቱ። ልቡስ ምንድን ናት? **እግዚአብሔር እንደ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የሰውን ልብ መረጠ**፡ የሚለውን መልእክቴን ታስታውሱታላችሁ? ዲያብሎስ እንደ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የሚመርጠው ጭንቅላትን ነው፡ አያችሁ፡ በአይኑ እንዲመለከት፡ ነገሮችን እንዲያይ ያደርገዋል። በዚያ ውስጥ ግን... እግዚአብሔር በዓይኑ የማያያቸው ነገሮች በልቡ እንዲያምን ያደርገዋል። እንደሱ ነው? አያችሁ፡ እግዚአብሔር በልብ ነው፡ በሰው ልብ ውስጥ የእግዚአብሔር ዙፋን አለ። ገባችሁ? ሰው! እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰው ልብ ውስጥ አደረገው።

235 አሁን፡ ተመልከቱ። የሰው የመጀመሪያ ክፍል ምንድን ነው? የሰው የመጀመሪያ ክፍል **ሰጋ** ነው። የሚቀጥለው ክፍል **ነፍስ** ነው፡ ይህ ማለት እሱን እሱ እንዲሆን የሚያደርገው የመንፈሱ ተፈጥሮ ነው። እዚህ ይገናኘዋል። እንግዲህ፡ የሰው ሶስተኛው ክፍል **መንፈሱ** ነው፡ መንፈሱም በልቡ መሃል ነው፡ በልብ መሀል ደግሞ እግዚአብሔር ለዙፋን የሚመጣበት ሰፍራ ነው።

236 በቅርብ ጊዜ፡ የዛሬ አራት አመት በቺጋጎ የወጣ—ጋዜጣ፡ ታስታውሳላችሁ፡ ይህ ምስኪን አማኝ… ማለቴ፡ ይህ እምነት አልባ ምስኪን ሰው፡ እግዚአብሔር በሰለሞን በኩል እንዲህ ሲል የተናገረው ነገር፡ “ሰው በልቡ እንዳሰበ እንደዚያው ነው” ማለቱ ስሕተት ነው አለ። እንዲህ አለ፡ “ማሰብ የሚቻልበት አቅም በልብ ውስጥ የለም። በልቡስ እንዴት ያስባል? ማለት የፈለገው… ጭንቅላት ለማለት ነው።”

237 እግዚአብሔር ጭንቅላት ማለት ቢፈልግ ኖሮ፡ “በጭንቅላቱ፡” ይል ነበር።

238 እንደ ሙሴ፡ ለምሳሌ ሙሴ… እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል፡ “ሙሴ ሆይ፡ ያለህበት ስፍራ ቅዱስ ነውና፡ ጫማህን አውልቅ”፥ እንዲህ ቢል ኖሮስ፡ “እንደው፡ ለምን ባርኔጣዬን አላወልቅም፡ ይህም’ኮ መልካም ነገር ነው”? የተባለው “ጫማ፡” ነው። “ጫማ፡” እንጂ፡ “ባርኔጣ፡” አላለውም።

239 “ንስሃ ግቡ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ተጠመቁ፡” ባላቸው ጊዜም፡ እንደተናገረው እንደዚያው ነው። “በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ” ማለቱ አልነበረም።

240 “ዳግም መወለድ **ያስፈልጋችኋል**፡” ባለ ጊዜ፡ “ሊያስፈልጋችሁ **ይችላል**፡” ማለቱ አይደለም።

241 “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች **ይከተሉአቸዋል**፡” አለ እንጂ፡ “**ምናልባት** ይችል ይሆናል፡” አላለም።

242 እንደተናገረው እንዲሁ ነው! አምላክ ነውና አይጸጸትም። ፍፁም የሆነውን ያውቃል ስለዚህ በዚያ መንገድ ያደርገዋል፡ እንዲሆን የሚያስበውም—በዚያ መንገድ ነው። ስለዚህ እናንተ ወደዚያ ማደግ ይጠበቅባችኋል። እሱ ወደ አሳባችሁ ሳይሆን፡ እናንተ ወደ አሳቡ መምጣት ይኖርባችኋል። ልዩነቱ ያ ነው።

243 አሁን፡ አሁን፡ በዚህ ሰጋ፡ ነፍስ ሰርዓት ውስጥ… አሁን፡ **ነፍስ** የሚለውን ቃል ወስዳችሁ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ—ወይም በዌብስተር፡ በሌሎችም ዘንድ፡ ብትመረምሩት “የመንፈስ ተፈጥሮ” ማለት እንደሆነ ይነግራችኋል።

244 ለምሳሌ፡ ይህ ሰው፡ **ይህ** ጆን ዶይ ነው፡ እንላለን። እሺ፡ ጆን ዶይ። **ይህም** ሳም ዶይ ነው። እሺ። አሁን፡ ጆን ዶይ ሰው ነው፡ ሰጋ ነው፡ የሳም ዶይ ወንድም ነው። አሁን፡ ጆን መንፈስ፡ ነፍስ፡ ሰጋ ነው፡ ሳም ዶይም እንዲሁ (ሰጋ፡ ነፍስ፡ መንፈስ) እንደሆነ፡ ሰጋ፡ ነፍስ፡ መንፈስ ነው። አሁን፡ **ይሄኛው** ሰው ክፉ፡ ጨካኝ፡ አጭበርባሪ፡ ሌባ፡ ውሸታም፡ አመንዝራ፡ ክፋት ሁሉ ነው፥ **ይሄኛው** ሰው ግን በፍቅር የተሞላ፡ ሰላም፡ ደስታ ነው። ሁለቱም ነፍስ፡ ሰጋ፡ መንፈስ አላቸው። ታዲያ፡ ልዩነታቸው ምንድነው? **ይሄኛው** ሰውዬ ወደ ኋላ ተጉዞ እንዲህ ሊል ይችላል፡ “እናቴን ትዝ አለችኝ፡ ገና ህጻናት ሳለን ያደርግናቸው ነገሮች ትዝ አሉኝ”፥ ሁለቱም ሊሉ ይችላሉ። ሁለቱም መንፈሶች አላቸው፡ ሁለቱም ነፍስ አላቸው፡ ሁለቱም ሰጋ አላቸው።

245 **የዚህ** ሰው መንፈስ ተፈጥሮ ግን ክፉ ነው፥ **የዚህ** ሰው መንፈስ ተፈጥሮ መልካም ነው። አያችሁ? ስለዚህ የመንፈስ ተፈጥሮ የሰው ነፍስ ነው። አያችሁ? ስለዚህ፡ አሁን፡ እግዚአብሔር ምን ውስጥ ለመግባት እየሞከረ ነው? የሰው መንፈስ እና ልብ ውስጥ። የመንፈስ ማደሪያ ስፍራ ልብ ነው።

246 ታውቃላችሁ፡ ሳይንስ ሲናገር (ቀደም ሲል አልጨረስኩትምና)፡ ሰው በልቡ አያስብም አለ። ከዚያም ሳይንስ በሰው ልብ ውስጥ የደም ህዋስ ወይም ሌላ ነገር የሌለበት ስፍራ፡ ማግኘት ጀምሯል፡ (በእንሥሳት ልብ ሳይሆን፡ በሰው ልብ ውስጥ)። እነርሱም "ይህ ስፍራ ነፍስ፡ ወይም መንፈስ የሚያድርበት ስፍራ ነው፡" ብለዋል። በቃ—ተውአቸው፡ በገዛ ስንፍናቸው ተጠቅመው እግዚአብሔርን ያረጋግጡታል። በትክክል። እግዚአብሔር ሰነፎችን እንዲመሰክሩለት ያደርጋቸዋል።

247 ይኸው፡ በየጋዜጣው ታላላቅ አርእስተ ዜናዎች፡ አለ። የወንድም ቦዜ ትንሿ ልጅ እንዲህ አለች፡ "ወንድም ብራንሃም፡ በቀደም የተናገርከውን ታውቃለህን? " "ተመልከት፡ ተመልከት፡ ሳይንስ አረጋግጦ ጨረሰ፡" አለች።

248 "መልካም፡ እግዚአብሔር ይባረክ! እፈልገዋለሁ፡ እህቴ፡ እፈልገዋለሁ—ይህን እፈልገዋለሁ፡" አልኳት።

249 የሰው ነፍስ የመንፈስ ተፈጥሮ ናት፡ የመንፈስ ማደሪያም የሰው ልብ ነው።

250 አሁን፡ አሁን፡ ውጨኛው አጸድ ምንድነው? ሥጋ ነው። አያችሁ? መጀመሪያ የምታገኙት፡ ስጋ ነው። መጀመሪያ ያንን ማስወገድ አለባችሁ። ከዚያም፡ ከስጋ ማዶ ታልፋላችሁ። "መንገዶቹ እጅግ ስለሚያንሸራትቱ፡ ተነስቼ ለመሄድ እ—አይሰማኝም ይላል ስጋ። እ—እ... በጣም ይሞቃል። ኦህ፡ ቸርች፡ እኔ እንጃ።" ስጋ ይሄ ነው። በጣም ጥሩ። እንግዲህ፡ ይህን ሁሉ ፈጅታችሁ ማለፍ አለባችሁ፡ እግዚአብሔር በዚያ በኩል ያልፋል።

251 ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣ፡ ወደ ነፍስ ይዘልቃል፡ ተፈጥሮ ማለት ያ ነው። "ወይኔ፡ እነ ጆንስ ምን ይሉኛል? ወይ፡ ጉድ! ታውቃለህ፡ እንዲህ አይነቱ ነገር ባደርግ—ቤተ ክርስቲያናችን ያባርሩኛል። አየህ? " እናንተ ግን በዚያ ውስጥ ማለፍ አለባችሁ።

252 በዚያ በኩል ስታልፉ፡ ያኔ እርሱም ዙፋኑ ወደሚያደርገው ልብ ይገባል። ያም መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥ ማለት ነው። ኢየሱስም አለ፡ "በእኔም ከሚያምኑ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንኳ ከምታሰናክል የወፍጮ ድንጋይ በአንገትህ ታስሮ፡ ወደ ጥልቅ ባሕር ብትወረወር ይሻልሃል።" እንደው በስሱ ማበሳጨትም ቢሆን፡ በሆነ ነገር እነሱን ማሳዘን እንኳ ቢሆን፡ ፈጽማችሁ አትጉዱአቸው። አንዳቸውም በሆነ ነገር ከማሳዘን ይልቅ፡ ራስህን ብታስጥም፡ ወይም ፈጽመህ በምድር ባትወለድ ይሻልህ ነበር። የምሩን ነው? ይዋሻል እንዴ? የተናገሩት ደቀ መዛሙርት ናቸውን? አይ፡ አይደለም። የተናገረው ኢየሱስ ነው! "በእኔ የሚያምኑትን ከእነዚህ ከታናናሾቹ፡ አንዱን እንኳ ብታሰናክል፡" አለ ኢየሱስ።

"ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል!"

253 አንድ ታላቅ፡ ግዙፍ ሰው ይመጣና "ኦህ፡ እኔ አምነዋለሁ! ሃሌሉያ!" ይላል፡

254 "በልሣን ተናግረህ ታውቃለህ፡ ልሣን ትተረጉማለህን፡ አጋንንትንስ ትገስጻለህን፡ እንደ ተሰፋ ቃሉንስ፡ ራዕዮችን፡ እና ሌሎች ነገሮች ታያለህን? "

"አይ፡ ያ ዘመን እኮ አልፏል።" እንዲህ አይነቱ አማኝ አይደለም፡ አስመሣይ-አማኝ ነው።

255 ኢየሱስ፡ የመጨረሻውን ቃል በተናገረ ጊዜ፡ “ወደ ዓለም ሁሉ እና ወደ ፍጥረት ሁሉ ሂዱ፡ ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።” በትክክል። “እኔ እስክመለስ ድረስ እነዚህ ነገሮች አማኞችን ይከተሏቸዋል።” እሱ የተናገረው የመጨረሻ ቃላት እነዚህ ናቸው። ሰንቶች ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ፡ ማርቆስ 16 ላይ።

አሁን፡ አያችሁት፡ ያኛው አስመሣይ-አማኝ ነው።

256 ነገር ግን በሚከተሉት ምልክቶች፡ እና የህይወታቸውን ትህትና፡ ምንም ሳያስመስሉ፡ የምር የሚያምን አማኝ ስታገኙ፡ እውነተኛ፡ እውነተኛ አንቀጾች ናቸው፡ ክርስትያን መሆናቸውን እወቁ፡ እረፉም። ያኔ ማድረግ ያለባችሁ፡ በንጉስ ጎዳና ላይ ናችሁና፡ አብራችሁ ሁኑ፡ አንድ ላይ ተጓዙ።

257 አሁን፡ ምን ይሆናል? ይህን ተመልከቱ። የአሕዛብ ቤተ ክርስቲያን አካል ስንመለከታት፡ ውጨኛው አጸድ፥ የሉተር ዘመን ነበረ።

258 እስከ 606 **ዓ.ም**. የቲያጥሮን ዘመን እስኪመጣ ድረስ—የአይሁድ ወገኖች እንደነበሩ፡ አስታውሱ፡ ከሞላ ጎደል ሁሉም የተለወጡ አይሁዳውያን ናቸው። ከአይሁዶች በኋላ ግን፡ አይሁዳውያን እና አህዛብ ሆኑ (በአብዛኛው ግን አይሁድ)። ወደዚህ፡ ወደ አሕዛብ ዘመን ዘንድ በመጣ ጊዜ ግን፡ አያችሁ፡ ማርቲን ሉተር፡ ጆን ዌስሊ፡ እና ሌሎች መጡ። አያችሁ?

259 አሁን፡ እነዚህ ከጨለማው ዘመን በኋላ የመጡትን ሶስቱ እዩአቸው፡ እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ ደርሰው አለፉ። ይህ በሆነ ጊዜ፡ እነዚህ ውጨኛው አጸዶች እዩአቸው። አያችሁ፥ ሰጋ፡ ነፍስ፡ መንፈስ። አያችሁ? እነዚያ የውጭ አጸዶች፡ ሰጋ። ቅድስት፥ ናዝሪን፡ ፒሊግሪም ሆሊነስ፡ ፍሪ ሜቶዲስት። አያችሁ? እና ቅድስተ ቅዱሳን፥ ወደ ድሮ ወደ ጴንጤቆስጤ፡ በመጀመሪያ ወደ ነበረው፡ አያችሁ፡ ወደ ጅማሬው ተመለሰ።

260 አሁን፡ እየሣላችሁት ከሆናችሁ፡ ይህን መጥቀስ እፈልጋለሁ። አሁን፡ ወደ ሰጋ መግቢያ የሆኑ፡ ሰጋን የሚቆጣጠሩ አምስት መንገዶች አሉ። ይህን ታውቃላችሁ። የሉም እንዴ? እነዚያም አምስቱ የሰሜት ሕዋሳት ናቸው። ሰጋን የሚቆጣጠሩ ሰሜቶች ሰንት ናቸው? አምስት፥ ማየት፡ መቅመስ፡ መዳሰስ፡ ማሽተት፡ መሰማት። ልክ ነው? ይህ ሰጋ ነው፡ ውጨኛው አጸድ፡ ሰጋ ነውና የምትታመኑበት ነገር አይደለም።

261 ከዚያም ውስጠኛው አጸድ አለ፡ ውስተኛ አጸድ እናገኛለን፡ ይህም ሁለተኛው መሰዊያ ነው። የሚቀጥለው መሠዊያ ይመጣል፡ የሚመጣውም በ—በህሊና፡ በምናቦች፡ በትዝታዎች፡ በፍላጎቶች፡ እና በፍቅር ሰሜት። ውስጠኛው አጸድ የሚቆጣጠሩ አምስት ሰሜቶች እነኚህ ናቸው። ያም ነፍስ ነው። ፍቅር፡ እና ሌሎች፡ የፍቅር ሰሜቶች ያሉት፡ ያ ነፍስ ነው። እና በመቀጠል በዚህ ዳሰሳ ውስጥ ያለው ቀጣይ ነገር፡ እንዲሁም ትዝታዎች፡ እና ህሊና፡ እና ምህረት፡ ወዘተረፈ፡ እ—እ—እና ምናብ ይኖራሉ። ቁጭ ብላችሁ ነገሮች ታመዛዝናላችሁ፡ ምን እያደረጋችሁ ነው? በሰጋችሁ ውስጥ ይህን ማድረግ አትችሉም፡ ሰሜታችሁ ነገሮችን አያገናዝብም። በውስጣችሁ ያለው ውስጠኛው አጸድ ነው።

262 ሶስት ደጆች አሉት። ምን እየሰራን ነው? አሁን እየከፋፈልናቸው ነው፡ እንዳያመልጣችሁ። ከአምስቱ ሕዋሳት፡ ከስጋ ተነስተን፡ ወደ ቀጣይ፡ ወደ ውስተኛው አጸድ፡ ነፍስ፥ አሁን ግን ወደ ልብ ትደርሳላችሁ። አያችሁ?

263 አሁን፡ እናንተ ፕሊግሪም ሆሊነስ እና ሜቶዲስቶች **በዚያ** በውጭ ባለው መሰዊያ ላይ ደርሳችሁ ትቆማላችሁ። አያችሁ፡ በአጸዶቹ ላይ ናችሁ። እናንተ ሉተራውያን እና ሌሎችም ገና በሥጋ ወደኋላ ተመልሳችኋል፡ ገና በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶች ላይ ናችሁ፡ አይን በሚያየው ታደርጋላችሁ። አያችሁ?

264 በመቀጠል ፍሪ የሜቶዲስት የሚባሉትን ፒልግሪም ሆሊነሶች ይመጣሉ፡ ወደሚቀጥሉት አጸድ መጥተው በቅድስና ያምናሉ፡ ይህም መሰዋዕቱ የሚቀርብበት ስፍራ ቅድስት ተብሎ ስለሚጠራ ነው።

265 ሊቀ ካህናቱ ግን በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ተከለከለው ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል። በመጀመሪያ የሉተራን ዘመን ነበረ፡ ከዚያም የሜቶዲስት ዘመን፡ ከዚያም **ይህ** ዘመን፡ የቤተክርስቲያን ብርሃናት እንደ ሰው ሰርዓት አመጣጥ፡ በመምጣት ላይ ነበሩ።

266 ከዚያም እንዴት—**ወደዚህ** እንዴት እንገባለን? አሁን፡ አስታውሱ፡ በቅድስት እና በቅድስተ ቅዱሳኑ መካከል መጋረጃ ነበረ፡ የተሰቀለ መጋረጃ ነበር። በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ክርስቶስ በልባችሁ ዙፋን ላይ ሊቀመጥ ሲመጣ፡ ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ ማለት ነው። በጽድቅ በኩል ገባ (ልክ ነው? )፥ ቅድስና፥ "ከዚያ በኋላ በአንድ ምን… " (በውኃ… በአንዲት ቤተ ክርስቲያን… በሐይማኖት ሰርዓት… አይደለም!) "በአንዱ መንፈስ፡" ከዚህም ሁላችንም አንድ አካል እርሱም የክርስቶስ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል። በምን? በመንፈስ ቅዱስ።

267 የሚገባበት ማን ነው? ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ጴንጤቆስጤዎች፡ የሚፈልግ ሁሉ። መጋረጃው፡ ልባችሁን ከሱ የሚጋርደው ያ መጋረጃ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ዝግጁ ናችሁ? መጋረጃው "የራስ-ፈቃድ" ይባላል። አሁንስ ምስሉን አገኛችሁት? **ከውጭ** ያሉ ሰሜቶች፡ የስጋ ስሜቶች እና የነፍስ ስሜቶች፡ በዚያ በቅድስት፡ እና በቅድስተ ቅዱሳኑም መካከል ያለው መጋረጃ። እና ወደዚያ መግባት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ የራስ-ፈቃድ ነው! "ለወደደ ሁሉ… " በምን? እጅ በመጨባበጥ? በመጥለቅ? የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን? ደብዳቤ በመላክ? የፈለገውን ላደረገ… ? አይደለም! "ከመጋረጃው ጀርባ መግባት **ለ**ወደደ ሁሉ።"

268 ክርስቶስ ወደ ስሜታችሁ ሲመጣ፡ እንዲህ ትላላችሁ "እንግዲህ፡ በርግጠኛነት። ወደ ሲኦል መግባት አልፈልግም፡ ዋናው ነገሩ ይህ ነው። ስለዚህ የቤተ ክርቲያን አባል እሆናለሁ።" እሺ፡ ሉተራን።

269 "በጣም ጥሩ፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ልንገርህ፡ በቻልኩት መጠን፡ የተለየ ህይወት መኖር አለብኝ፡" በመሠዊያው ላይ በመቀደስ። እሺ፡ ሜቶዲስት።

270 በጣም ጥሩ፡ **የወደደ** ሁሉ፡ የተዘረጋውን መጋረጃ ይለፍ። ኦህ፡ ክብር ለእግዚአብሄር ይሁን! እኔ'ማ ወዲያ ማዶ ተሻግሬአለሁ። ሃሌሉያ ለሰሙ! ኦህ፡ ማይ! የወደደ ሁሉ፡ የገዛ ፈቃዱ የሆነውን፡ ይህን መጋረጃ ይቅደድና፡

እግዚአብሔር ወደ ልቡ እንዲገባ ይፍቀድ። ያኔ በሰው ልብ ውስጥ ክርስቶስ በፍርድ ወንበር ላይ አለ ማለት ነው! ምን ሊፈጠር ነው?

271 "ተገቢ ነገር... ኦህ፡ እኔ ቆሻሻ ቀልዶችን—እቀልዳለሁ፡ ምንም አይኮንነኝም፡" ትላላችሁ። ለምን? የሚከሳቸው ምንም ነገር ስለሌላቸው ነው። ያንን ነገር የሚያስወጣ—አንዳች የተቀመጠ ነገር የላቸውማ። የሚከሳችሁ ነገር—ስለሌላችሁ ነው። "ይኸውልህ፡ ልንገርህ፡" ሴትዮዋ "ጸጉርሽን ማሳጠር ትችያለሽ፡ ማንም አይከሰሽም፡" ብላኛለች። ምንም አያስገርምም! አያችሁ? "ኦህ፡ ቁምጣ መልበስ እችላለሁ... **ይህ** ማድረግ እችላለሁ። እ... " ሰዎቹ እንዲህ ብለውኛል፡ "ሲጋራ ብታጨስ አይጎዳህም፡ አንዳንድ—አንዳንድ የካርታ ጨዋታዎች እና አንዳንድ ዳይሶችን ብጫወት አይጎዳህም፡" ምንም ባደርግ አትጎዳም አሉኝ። "አይጎዳኝም።" ከዚያ የቤተ ክርስቲያን አባላት ሆነው ይቀጥላሉ፡ አያችሁ፡ "**ይህን** ማድረጌ አይጎዳኝም።" ለምን? ለምን? ሊከሳችሁ የሚችል በውስጣችሁ ምንም ነገር ስለሌላችሁ ነው።

272 ክርስቶስ በእናንተ በገባ ጊዜ ግን፡ በልባችሁ ላይ መሠዊያ ሰርታችኋል ኃጢአታችሁም በየቀኑ ይወሰዳል። ታላቁ ቅዱስ ጳውሎስም፡ እንዲህ አለ፡ "ዘወትር እሞታለሁ። ሕያው ብሆንም፡ **እኔ** ሕያው ባልሆንም፡ ክርስቶስ በእኔ ይኖራል።" ውስጠኛው መጋረጃ ይህ ነው። ኦህ፡ ወንድም፡ እህቶች ሆይ!

273 እንፍጠን፡ አውቀዋለሁ... ኦህ፡ አይ፡ ጊ... ጊዜዬ አልቋል፡ መጨረስ አልችልም። እንየው፡ ዝም ብዬ... በቃ፡ ባልቀጥል ይሻላል። አያችሁ፡ ስለ ሃያ-አራቱ ሽማግሌዎች መናገር ፈልጌ ነበር፡ ግን ሁላችሁም የእራት ሰዓታችሁ እየከለከልኳችሁ ነው። እንዲህ እናድርግ... እስኪ፡ እንደው... ሃያ-አራቱ ሽማግሌዎች ቀጥልበት የምትሉ ስንቶች ናችሁ? እ... [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] በጣም ጥሩ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። በጣም ጥሩ፡ አንድ ደቂቃ። "ሃያ-አራት ሽማግሌዎች፡" እንግዲያውስ፡ አሁኑኑ ቶሎ እንያቸው፡ "በዙፋኑ ዙሪያም፡ ሀያ ስንት-... በዙፋኑ ዙሪያ ነበሩ።"

274 አሁን ምን እንደሆነ እዩ... የዙፋኑ መገኛ የት ነው? በልብ ውስጥ። በማን ልብ ውስጥ? በሰባቱ የቤተክርስቲያን ዘመን አባላት፡ ክርስቶስ! "በሚሰሩት ስራዎቻቸው ላይ፡ አንዳች ክፉ ነገር ብትናገር ትኰነናለህ፡" በፍርድ ቀን ስለሱ መልስ ትሰጥበታለህ። ምድርን የሚፈርዳት ማን ነው? ቅዱሳን ምድርን ይፈርዳሉ።

275 ዳንኤል ከእልፍ ጊዜ አእላፍ ሲመጣ ያየው ማንን ነው? ቅዱሳኑን። መጻሕፍቱ ተከፈቱ፡ ኃጢአተኞች። ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ፡ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ፡ ሰነፏ ድንግል ናት። ኦህ፡ ማይ፡ ይህ ማየት ይሳናቸዋልን? ሰነፏ ቤተክርስቲያን፡ ዘይቱን ከመብራታቸው ዘንድ ጨርሰው፡ ሙሽራውን ለመገናኘት የወጡት፥ ወደዚህ ፈጽመው ያልደረሱ፡ ክርስቶስ በእነርሱ ተአምራት ይሰራ ዘነድ በልሳንም ይናገር ዘንድ ድንቆች ያደርግ ዘንድ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ መኖሩን ለማረጋገጥ ፈጽሞ ያልተቆጣጠራቸው።

276 ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ እንዲህ ቢል ኖሮስ "እኔ ኢየሱስ ነኝ፡ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡" ምንም ሳያደርግ፡ "ወደዚያ ሄጄ የዚች ቤተ ክርስቲያን አባል እ—እሆናለሁ" ቢልስ? የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናልን?

277 ታዲያ ምን አለ? “የአባቴን ሥራ ባላደርግ፡ እንግዲያውስ አትመኑኝ።”

278 ኦህ፡ ማይ! አይታችኋል? እግዚአብሔር እንዲህ ማድረግ ይወዳልና፡ እራሱን ተረከ። እርሱ ጀሆቫ ነው። እራሱን ማስተዋወቅ ይወዳል። ኦህ፡ በዚህ በጣም ደስ ይለኛል። አዎን፡ ወዳጄ። ራሱን ለእኔ አስተዋውቋል፡ ለእናንተም እንዳስተዋወቃችሁ አውቃለሁ። እናንተ አሁን የተቀበላችሁ ወጣቶች፡ እንደ ሌሎቹ... ምናልባት ሌሎች ክርስቲያኖች በሚያውቁት በኃይሉ ችሎት እና ታላቅነት የማታውቁት ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ ይሁን እንጂ በቀጥታ ወደዚያ እያደጋችሁ ናችሁ። ወደ ንጉሱ አውራ ጎዳና እየመጣችሁ ነው። ዝም ብላችሁ... በተቻላችሁ መጠን እየተመለከታችሁ እና እየዘረጋችሁ ቀጥሉ። ሩጫውን በተቻላችሁ መጠን፡ ሩጡ፡ ሩጡ። ለተራ ነገር አትቁሙ፡ ጉዞአችሁን ቀጥሉ።

279 ምስኪኗ እህት ስኔሊንግ ትለው እንደነበረ፦

> ሩጫዬን፡ ሮጬአለሁ፡ ሮጬአለሁ፡ ተሻግሬዋለሁ፥
> ሩጫዬን፡ ሮጬአለሁ፡ ሮጬአለሁ፡ ተሻግሬዋለሁ፥
> ሩጫዬን፡ ሮጬአለሁ፡ ሮጬአለሁ፡ አንተም ቁጭ አትበል።

ምስኪኗ ነፍስ፡ ዛሬ ከአድማስ ማዶ ነች።

280 በጣም ጥሩ፡ አሁን፡ በዚያም—በዚያ ላይ ዙፋኖች ነበሩ፡ ሃያ-... አራት እና ሃያ መቀመጫዎች ነበሩ። እስኪ፡ ስንት ነበሩ፡ አራት እና ሃያ? ሃያ-አራት። በጣም ጥሩ፡-

> **... ሀያ አራት ዙፋኖች፡** በዙፋኖቹም **ላይ... በዙፋኖቹም ላይ ሃያ አራት ሽማግሌዎች**... (አንድ ዙፋን ለአንድ) **ነጭ ልብስ** ለብሰው፥ **በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ተቀምጠው ነበር።**

281 አሁን፡ “ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች።” ልታስተውሉልኝ የምፈልገው መላእክታዊ ፍጡራን እንዳልነበሩ ነው። መላእክት ወይም ሰማያዊ ፍጥረታት፡ ከዘውዶች እና ከዙፋኖች ጋር የሚያያዝ ነገር የላቸውም። እያችሁ፡ መላእክት ብቻ ናቸው፡ ምንም መያያዝ የላቸውም፡ በጭራሽ ድል ነስተው አያውቁም። ትንሽ ዝቅ ብላችሁ ካያችሁ፡ የሚዘምሩት ዝማሬ፡ እና ሌላ ነገር በማየት፡ እንዲሁ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ትችላላችሁ። እያችሁ? የቤዛነት መዝሙር ዘመሩ፡ ስለዚህ፡ መላእክት መዋጀት አያስፈልጋቸውም። እያችሁ? በጣም ጥሩ። እነዚያ ግን የተዋጁ ሰዎች ነበሩ።

282 እንደውም... እናንተ ሰዎች፡ ይሄን ለመጨረስ ጊዜ አይኖረኝም። እናንተ የምትጽፉ ግን፡ የተዋጁ ሰዎች እንደ ሆኑ ልታውቁ ከፈለጋችሁ፡ የማቴዎስ ወንጌል 19:28 አንብቡ፡ እሺ፡ ማቴዎስ፡ 19፡28፣ ራዕይ 3፡21፣ ከዚያም ሌሎችንም ያዙ፡ ራዕይ 20፡4፣ ራዕይ 2፡10፣ አንደኛ ጴጥሮስ 5፡2 እና 4፣ ሁለተኛ ጢሞቴዎስ 4፡8 ላይ። ያ እንደተዋጁ ግንዛቤ ይሰጣችኋል። ዛሬ ጠዋት ይህንን መዳሰስ እፈልጋለሁ፡ እያችሁ። እናንተም ለሳምንታት ያህል ይህን ማበጠር ትችላላችሁ፡ እያችሁ። እነሱ የተዋጁ ሰዎች ነበሩ እንጂ፡ መላእክት አልነበሩም—አልነበሩም፡ ሰማያዊ ፍጡራን አልነበሩም። እያችሁ? ልብሳቸውን፡ አለባበሳቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት ትችላላችሁ፥ የነበራቸውን ነገር፡ ስልጣናቸውን መገመት ትችላላችሁ፥ የዘመሩትን መዝሙር መገመት ትችላላችሁ፥ ከዚያ መላእክታዊ ፍጡራን አለመሆናቸውን እወቁ። እህም።

283 ወደ ማለቂያው መድረሴ እያስደሰተኛም፡ ቢሆንም እስቲ አንድ ተጨማሪ ቃል እናንብብ። ፈቃደኞች ናችሁ? በጣም ጥሩ። ለአፍታ ያህል፡ ወደ ዳንኤል 7 እንመለስ፡ ወደ፡ ዳንኤል 7 እንመለስ፡ እና አንድ ቃል እናንብብ። ይህን እፈልጋለሁ... ይህ ዛሬ ጠዋት በሌላው መልእክት ላይ ሙሉ በሙሉ ያግዛችኋል። እንደሚያግዛችሁ እርግጠኛ ነኝ—ይህን ካነበባችሁ እና ይህን ካያችሁ በኋላ በጣም ጥሩ ስሜት እንዲሰማችሁ ያደርጋል፡ የዳንኤል ምዕራፍ 7 የሆነውን፡ ዳንኤል ተመልከቱ፡ እና ከ 1 እንጀምር... ዳንኤል 7 ላይ፡ 9ኛውን ምዕራፍ-... 9ኛው ቁጥር እንውሰድ። አሁን፡ እነዚህን ነገሮች በደንብ ሰሟቸው፦

> ዙፋኖችም... **እስኪዘረጉ** ድረስ **አየሁ፡ በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ፡** ልብሱም **እንደ በረዶ ነጭ፡** የራሱ**ም ጠጉር እንደ... ጥሩ ጥጥ** ነበረ፥ **ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፡** (አሁንም እንደገና ተመልከቱት፡ ወደ መረግድ እሳት ተመለስ።) **መንኰራኵሮቹም የሚነድድ እሳት ነበሩ።**
>
> የእሳትም... **ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር፥** ሺህ ጊዜ **ሺህ ያገለግሉት ነበር፡ እልፍ ጊዜ** አእላፋት**ም** (የተቤዡት ማለት ይኸውላችሁ።) **በፊቱ ቆመው ነበር፥ ፍርድ**ም **ሆነ፡ መጻሕፍትም ተገለጡ።**

284 አሁን፡ ይህ ፍርድ እንደሆነ፡ አስተውሉ። አያችሁ? አሁን፡ እዩ። ዳንኤል፡ በፍርድ ጊዜ ዙፋኖችን ባያቸው ጊዜ፡ ባዶ ነበሩ፡ "ዙፋኖች ተዘርግተዋል፡ በዘመናት የሸመገለውም መጣ፡ ከሰማያት መጣ።" ዮሐንስ ባየው ጊዜ ግን፡ ዙፋኑ ላይ ኢየሱስ ተቀምጦበት ነበር፡ እና ለደቀ መዛሙርቱ፡ እና ለአባቶች ለተቤዣቸው የሆኑ ዙፋኖችም፡ በተቀማጭ ሞልተው ነበር። አያችሁ? ዳንኤል ያየው ከክርስቶስ ዘመን ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ነው። ከክርስቶስም በኋላ፡ ከሁለት-ሺ አምስት መቶ አመታት በኋላ፡ ዮሐንስም በሚመጣው ዓለም ኖረ፡ እና ይህ ሁሉ ሲሆን አየ። ዳንኤል፡ ይህ አላየም፡ (አያችሁ? ) በዘመናት የሸመገለ ሲመጣ አየ፡ ሲመጣ ብቻ አየው። ዮሐንስም ባየው ጊዜ ግን፡ ዙፋኑ ሙሉ ነበረ፡ አያችሁ፡ ዙፋኖቹም በዘመናት ከሸመገለው ጋር ተዘረጉ፡ ፍርድም ሆነ። ዮሐንስ ባየው ጊዜ ግን፡ ሽማግሌዎች በዮሐንስ ዘመን ገና አልተመረጡም ነበር... ማለቴ በዳንኤል ዘመን አልተመረጡም፡ በዘመን ፍጻሜ የተዋጁ ናቸው... ? ... ኡህ ማይ! ኡህ፡ እንዴት ያለ... እንዴት ያለ ድንቅ ነው?

285 ስለዚህ፡ በዳንኤል 7፣ እሱ... ዳንኤል ምን አደረገ? ፍርዱን አስቀድሞ አየ፡ የተቀመጡት ዙፋኖች ባዶ መሆናቸውን አየ። አያችሁ፡ ባዶ መሆን ነበረባቸው። እንደ ዮሐንስ በሱ ጊዜ፡ ከተነጠቀችው ቤተክርስቲያን በኋላ፡ በተዋጁት ሽማግሌዎች ተሞላ። እምም።

286 **ሽማግሌ** ማለት ምን ማለት ነው? **ሽማግሌ** የሚለውን ቃል፡ ከወሰዳችሁ... እነዚህ እዚህ የተጻፉት ሁሉ፡ እንዲሁ እያለፍኳቸው ነው። **ሽማግሌ** ማለት "የአንድ ከተማ ራስ" ወይም "የአንድ ጎሳ ራስ።" **ሽማግሌ** "የአንድ ነገር ራስ፡" ማለት ነው። ለምሳሌ ልክ እ—እንደ... ወንድም ነቪል አሁን የዚህ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነው። ምንድነው? የዚህች አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ራስ ነው። አያችሁ? እና የከተማው ከንቲባ የዚህች ከተማ ሽማግሌ ይሆናል፡ አያችሁ፡ የከተማዎቹ ሽማግሌ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ

ዘመን የነበሩትን፡ የከተማው ሽማግሌዎች ታስታውሳላችሁ? **ሽማግሌ** ማለት "የአንድ ከተማ ራስ" ወይም "የአንድ ጎሳ ራስ ነው።"

287 አሁን፡ ስንት ነበሩ? ሃያ እና አራት፡ ሃያ-አራት ሽማግሌዎች። ልክ ነው? አሁን... ኦህ፡ ማይ! እነማን ነበሩ? አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል፡ ዐሥራ ሁለቱ ነገዶች። ይህ... አሁን፡ ወደ ሌሎች ትምህርቶች እስክናልፍ ድረስ እናየዋለን፡ ትክክል መሆኑን እናረጋግጣለን፡ እናንተም፡ እየጻፋችሁ ስለሆናችሁ ደስ ብሎኛል። አያችሁ? አሥራ ሁለቱ ነገዶች እና አሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል! አሁን፡ ተመልከቱ። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል...

288 ጴጥሮስ አንድ ቀን ጠየቀ፡ እንዲህ ሲል "እኛስ ምን እናገኛለን? አባትን፡ እናትን፡ ባልን፡ ሚስትን፡ ልጆችን፡ ሁሉንም ነገር ትተናል፡ ሁሉንም ነገር ትተናል።" ጴጥሮስም፡ "ሚስቶቻችንን ትተናል፡ ልጆቻችንን ትተናል፡ አንተን ለመከተል፡ አባታችንንና እናታችንን፡ ቤቶቻችንን እና መሬቶቻችንን ትተናል።"

289 እርሱም እንዲህ መለሰ፡ "እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ፡ በአሥራ ሁለቱ ነገዶች ላይ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለት ዙፋኖች ላይ ትቀመጣላችሁ።" ይኸው ነው፡ የተቤዡት፡ የተቤዡ ሽማግሌዎች ማለት እነዚህ ናቸው።

290 ዳዊት ክርስቶስን በጥላ ሲተርክ ተ—ተመልከቱት። አያችሁ? ዳዊት ወደ ስልጣን በመጣ ጊዜ፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት እስከፊ ጊዜ አሳልፏል። ይሁን እንጂ ቅብአቱ ግን በላዩ ላይ ነበር፡ አዎን፡ ቅብአት በላዩ ላይ ነበር። እና ብዙ ሰዎች ግን እንዲህ አሰበዉት ነበር "ተራ ከዳተኛ፡ የሆነ ነገር ማፈራረስ፡ ማለያየት የሚያስብ ተራ ሰው።" አንዳንድ ሰዎች ግን ቀጣይ ንጉሥ እንደሚሆን አውቀው፡ አብረውት ቆዩ። ወንድሜ ሆይ፡ በዚህ በጉዞ ሳሉ፡ ከእርሱ ዘንድ በምንም ልትለዩአቸው አይቻላልችሁም እላለሁ።

291 አንድ ቀን እዚያ ተራራ ላይ ቆመ፡ ቁልቁል አይቶ የራሱን ትንሿ ተወዳጅ ከተማ፡ በጠላት ተከባ አያት። በዚያም ቆሞ ትንሽ ልጅ እያለ አስታወሰ፡ በጎችን በዚያ በኩል ያሰማራ ውኃ ይጠጣ ነበር፡ ግሩም ውኃ ነበር። (ስለዚህ ነገር በቅርብ ጊዜ እዚህ ተናግረን ነበር፡ **የህይወት ውኃዎች**።) እነሆ አሁንም እሱ፡ "ከዚያ ጠጥቼ ነበር፡ ብሎ አሰበ።"

292 ማድረግ የቻላት ነገር አጠገቡ ያሉትን ማዘዝ ብቻ ነበር። ወንድሜ፡ ከሰዎቹ መካከል ሁለቱ ሰይፋቸውን ይዘው በአስራ አምስት ማይል ፍልስጥኤማውያን ውስጥ ተዋጉ፡ ከምንጭ ውኃ እንዲያመጡለት፡ ግራ እና ቀኝ ያሉትን መቆራረጥ ጀመሩ። ባለ ስልጣን እንደሚሆን ያውቃሉና። አዎን፡ ወዳጄ። አንድ ቀን፡ አንዳቸው፡ እሱን ለማዳን፡ ጉድጓድ ውስጥ ገብተው፡ በአንድ-እጅ አንበሳን ገደሉ። ተዋጊዎች ነበሩ። እና ወደ—ስልጣን ከመጣ በኋላ፡ ምን እንዳደረገ ታውቃላችሁ? እያንዳንዳቸውን በየከተማው ላይ ገዥ አድርጎ ሾማቸው።

293 እዚህ ውስጥ ክርስቶስ አይታያችሁም? "ድል የሚነሣ በከተማይቱ ላይ ይነግሣል።" ድል ነሺዎች! ዛሬ ወደ ስልጣን እንደሚመጣ ከተረዳን፡ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ ገዢ ይሆናል። ጀርመን፡ እና አሜሪካ፡ እና ሁሉም ይወድቃሉ፡ እያንዳንዱ ሀገር ይወድቃል። የዚህ ዓለም መንግሥታት የአምላካችንና የክርስቶስ መንግሥት ይሆናሉ፡ በእነርሱ ላይ ይገዛል ይነግሥማል። እውነት ነው።

294 ስልጣን እንደሚይዝ እውቀናል፡ ስለዚህ ብቸኛዋ ፍላጎቱ እኛን ማዘዝ ናት! "ሃምሳ ሳንቲም በማይገኝባት በትንሿ ቲምቡክቱ እሱን እንድወክለው ይፈልገኛል፡ ከድሃ ወገኖች በቀር፡ ምንም ነገር በማይገኝባት፡" ፍላጎቱ ያ ነው። አሜን!

295 "ብዙዎች መሆን አያስፈልጋችሁም፡ **ይህን** ማድረግ አያስፈልግህም፡ መሄድ የሚፈልግ ይንገረኝ።" አሜን። በቃ።

296 "የተለየ ነገር እንድሠራ ከፈለገኝ፡ የተለየ እሠራለሁ፡" እንደ እነዚህ እህቶች እና እንደ ሌሎች፡ "አንድን ነገር እንዳደርግ ከፈለገኝ፡ እግዚአብሔር ይባረክ፡ ይህን ማድረግ ለእኔ ትልቅ ዕድል ነው።" ይኸው! ዓለም የወደደችውን ትበል፡ ወደፊት ስልጣን እንደሚይዝ እኛ እውቀናል። "በፊቴ ያለውን ሩጫ በትዕግሥት መሮጥ ካለብኝ፡ ተሎ የሚከበኝን ኃጢአቶቼን ማስወገድ ካለብኝ። የእምነታችንን ደራሲ እና ፈጻሚውን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ልመልከት።" ወደ ስልጣን ይመጣልና!

297 እነዚያ ሃያ አራት ሽማግሌዎች፡ "ሽማግሌዎች።" በጣም ጥሩ። አስራ ሁለት... ራእይ ላይ፡ እናገኘዋለን። በራእይ መጽሐፍ፡ ምዕራፍ 21 አካባቢ፡ የኢየሩሳሌም ከተማ አሥራ ሁለት መሠረቶችን እንዳላት እናያለን። ልክ ነው? አሥራ ሁለት ደጆች ነበሩት፡ በእያንዳንዱም ወገን ሦስት፡ ሦስት ጊዜ አራት ማለት አሥራ ሁለት ደጆች ነበሩ። ልክ በምድረ በዳ እንደተሰራች የማደሪያው ድንኳን ዓይነት ነው፡ ሙሴ በዚያ ሳለ ያየው ነገር ጳውሎስም ያየውን ዓይነት፡ ዮሐንስም በትክክል አይቶአልና።

298 አሁን ደግሞ አሥራ ሁለቱ መሠረቶች የሐዋርያት ስም እንደነበሩ እናስተውላለን። ለአሥራ ሁለቱም ደጆች በበሩ ላይ የእያንዳንዱ ነገድ ስም ነበራቸው። ስለ እነዚያን አሥራ ሁለቱን ሽማግሌዎች፡ አሥራ ሁለቱን ነገዶች፡ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት፡ አሥራ ሁለቱ መሠረቶችን፡ አሥራ ሁለቱን ደጆች እይታችን ምንድነው! ኦህ፡ ማይ! የእግዚአብሔርን የቁጥር ስሌት ከያዛችሁ ምንም አትስቱም፡ በማንኛውም ጊዜ በሁሉም ቦታ በትክክል ትገጥማለች።

299 እያችሁ፡ ዓለም የተሰራችባቸው ስድስት ቀናት ያሉን፡ ለዚህ ነው፡ አሁንም ወደዚህ ሰባተኛው ቀን እየተቃረብን ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለት-ሺህ ዓመታት፡ እግዚአብሔር በውሃ... ዓለምን በውሃ አጠፋው። ሁለተኛው ሁለት-ሺህ ዓመታት፡ ክርስቶስ መጣ። ዛሬ 1961 ነው፡ ትንሽ ጊዜ ብቻ ይቀራል፡ በደጅ ነው። ኢየሱስ ያለው፡ ተመልከቱ፡ "አሁን፡ እስከ ፍጻሜ አይቀጥልም፡" እንዲህ አለ፡ "ምክንያቱ ስራውን አሳጥረዋለሁ። ካልሆነ ግን፡ ስጋ ሁሉ በአቶሚክ ቦምብ ይጠፋል። ኧሃ-ሃህ። ስለ ተመረጡት ሲል፡ ስራውን በጽድቅ አሳጠረዋለሁ። የተወሰነውን ጊዜ፡ አሳጥረዋለሁ።" እያችሁ፡ ከዚያ በኋላ ሚለንየም አንድ ሺ-አመታት፡ ታላቁ ቀን ይሆናል።

300 ቤተክርስቲያን ለስድስት ሺህ ዓመታት በኃጢአት ደከመች፡ ሰባተኛው ሺህ ደግሞ ሚሊኒየም ነው። እግዚአብሔር ዓለምን በስድስት ሺህ ዓመታት ሰርቶ፡ ሰባተኛውም ሺህ ከሥራው ሁሉ እንዳረፈበት ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያንም በኃጢአት ምክንያት ለስድስት ሺህ ዓመታት ትደክማለች፡ ሰባተኛውም ሺህ ቤተ ክርስቲያን ታርፋለች።

301 በሽማግሌዎች ላይ የነበረው ነጭ ልብስ የቅዱሳን ጽድቅ ነው። **ነጭ** ማለት “ጽድቅ።” **ተጎናጽፈው** ስለነበሩ “ካህናት ወይም ዳኞች” መሆናቸው ያሳያል፡ ነጭ-የተጎናጸፋ፡ ካህናት፡ ዳኞች፡ ነቢያት፡ ወዘተ፡ ምን እንደነበሩ ተመልከቱ። ነጭ-የተጎናጸፉ፡ ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ነበሩ። ሃያ አራት ሽማግሌዎች ይኖራሉ። ከእነርሱም ለአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ አሥራ ሁለት ይሆናሉ። ለቤተክርስቲያንም አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ይሆናሉ።

302 በታላቁ የንጉሥ አደባባይ ይሆናሉ። ያስታውሱ፡ **እነዚህ** ሁሉ፡ በዚያ ተቀምጠው ይገኛሉ። **እዚህ** ጋር ደግሞ ክርስቶስ እና ሙሽራይቱ በዙፋኑ ላይ ተቀምጠዋል፡ ሚስቱ ማለት ቤተክርስቲያን፡ ከጎኑ ተቀምጣለች። ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች... መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ የቤተ መቅደሱ ጃንደረቦች ያገለግሉታል። በሄደበት ሁሉ፡ ሚስቱም ከእርሱ ጋር ትሄዳለች። ኦህ፡ ኦህ ማይ! በሚመጣው ታላቅ ዘመን፡ ኃጢያት ሁሉ እና የኃጢያቶች ውጤቶች ሁሉ...

303 ዛሬ ሰዎች በጣም የሚወዷቸው ትልልቅ፡ ድንቃ ድንቅ ሕንፃዎች፡ ገንዘቡንና ፍትወትን ሁሉ ኃጢአት እና ቆንጆ ሴቶች እና ወንዶች፡ በሥጋቸው ላይ የወደዱትን መሥራት የሚሞክሩትን ሁሉ፡ በአንዱም በሌላም፡ ዲያብሎስ ነፍሳቸውን ወደ ገሃነም እንዲልኩለት እንደ ወጥመድ የሚጠቀምባቸው ሁሉ፡ ይጠፋሉ እንዲሁም ይበሰብሳሉ፡ የቆዳ ትሎች ይበሏቸዋል። እና በመጀመሪያ፡ የቆዳ ትሎች... ከዚያም ወደ አለመኖር ለመለወጥ እና ለመጥፋት የእሳተ ጎመራ አመድ ለመሆን—ሁሉ ወደ እሳተ ገሞራ እሳት ውስጥ ይገባሉ።

304 ነገር ግን ወዳጄ ሆይ፡ ከእነዚህ ማለዳዎች አንድ ቀን፡ ነገር ሁሉ ካለፈ በኋላ፡ በአንዱ ማለዳ ላይ፡ እንደገና ታብባለች። መስኮቹ ነጭ ቀለም ባለው አበባ እና—ከአበባው ጋርም ከሕይወት ዛፋ ከሚወጣው የጽጌረዳው መዓዛ ይደባለቃል፡ ክርስቶስም በየማለዳው ይመላለሳል። ያኔ ግሩም አእዋፋት፡ እርግቦች፡ በዛፎቹ ላይ ተቀምጠው ይዘምራሉ፡ ከዚያ ወዲያ ሞት እና ሐዘን አይሆንም። ክርስቶስ እና የተዋጁት ወደ ምድር ይመለሳሉ፡ ለዘላለም ወጣት ይሆናሉ እንጂ፡ ማርጀት አይኖርም። የማይሞቱ ሆነን፡ በምስሉ እንኖራለን፡ ከጸሐይ እና ከከዋክብት ይልቅ እንደምቃለን።

ለውቧ ከተማ ተመድቤአለሁ
ጌታዬ የራሱ ለሆኑት ያዘጋጃት፡
በሁሉም ዘመናት የተዋጁ ሰዎች
በነጭው ዙፋን ዙሪያ “ክብር!” የሚዘምሩባት።
አንዳንድ ጊዜ የሰማይ ቤቴ ትናፍቀኛለች፡
ክብር ሁሉ የሚታይባት፡
አዳኜን ሳየው እንዴት ያለ ደስታ ይሆናል፡
በዚያ ውብ የወርቅ ከተማ!

እሱን ለማየት እንዴት ጓጓሁ! ኦህ፡ እሱን ማየት እፈልጋለሁ!

ለውቧ ከተማ ተመድቤአለሁ።

305 ዮሐንስ፡ በፍጥዋ ደሴት፡ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ሆና ስትወርድ አያት። ክብሯን፡ አንድ ቀን ማየት እፈልጋለሁ።

እርሱን እና ፊቱን፡ ላየው እናፍቃለሁ፡
ስለ ማዳን ጸጋውን ለዘላለም እዘምርለታለሁ፥

በክብር ጎዳናዎች ላይ ድምፄን ከፍ አድርጌ፥
ጭንቀት አልፎ፡ ለዘላለም ደስታ፡ ቤቴ ገብቻለሁ።

306 የበረዶው ማዳለጥ እና ማንሸራተት ሁሉ፡ የቀኑ ሙቀት እና ድካም ሁሉ፥ ሚስቴ እና ማቤል መጥተው ይህን መዝሙር ቢዘምሩልን፡ ብችለው—ኖሮ፡ “ወደ ጉዞው መጨረሻ ስድረስ፡ የመንገዱ ድካም ምንም አይመስልም።” እውነት ነው።

307 ለወንጌል ሥራ ከቤተክርስቲያን የወጣሁበት ሌሊት፡ ሁላችሁም ስታለቅሱ ትዝ ይለኛል፡ ምናልባት ከጥቂቶች በቀር፡ ማናቸውም፡ የሄደ የለም። እህት እና ወንድም ስፔንሰር፡ ምናልባትም—እዚህ ሲያለቅሱ ከነበሩ፡ ጥቂት ከአንጋፋዎቹ-መሰራቾች። መንፈስ ቅዱስ ግን “መሄድ አለብህ፡” አለኝ!

308 እና ለመጀመሪያ ጊዜ ለወራት ከሄድኩ በኋላ፡ ሚዳ ወደ ጆንስቦሮ ወረደች፡ ቤኪ ትንሽ ገና ህጻን ልጅ ነበረች፡ በአሮጌው ኮተንቤልት ባቡር ላይ ወረዱ፡ እዚያ ለመድረስ ቀናት ውስደባቸው። እና በሌሊት ስትደርስ እዚያ ቆሜ ነበርሁ። ሶስት ጎዳናዎችን አልፎ ወደ ነበረው፡ ወደ አዳራሹ ለመግባት ሞከርን፡ ፖሊሶች መንገዱን ሞልተውት ነበር። ጎዳናው ሳይቀር በህዝብ ተጨናንቆ ነበር። ወደ ቦታው ለመግባት፡ በጎዳናው ደጋግመን መዞር ነበረብን። ሚዳም እንዲህ አለችኝ፡ “ቢል፡ አንተን ሊሰሙህ ነው የመጡት? ”

309 “አይደሉም፡” አልኳት። ከዚያ እንዲህ ብለን ዘመርን።

ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፡
ከሩቅ ምድርም ይመጣሉ፡
ከንጉሣችን ጋር ለመብላት፡ እንደ እንግዳው ለመመገብ፥
እነዚህ ተጓዦች ምንኛ ብጹአን ናቸው!
የተቀደሰ ፊቱን የሚያዩ
በመለኮታዊ ፍቅር የበሩ፥
የጸጋው ተካፋዮች ብፁዓን ናቸው፡
በዘውዱ ውስጥ እንደ እንቁዎች ያበራሉ።

ኦህ፡ ኢየሱስ በቅርቡ ይመጣል፡
ፈተናዎቻችን ያኔ ያበቃል።
ኦህ፡ ጌታችን ይህ ጊዜ ቢመጣስ
ከኃጢአት ነፃ ለሆኑት ሲመለስ?
ኦህ፡ ደስታ ይሆንላችኋልን፡
ወይስ ሀዘን እና ጥልቅ ተስፋ መቁረጥ?
ጌታችን በክብር ሲመጣ፡
በአየር ላይ እንቀበለዋለን።

310 አሜን! ኧረ፡ እኔስ እወደዋለሁ! ሀዘን እና ጥልቅ ጭንቀት ይሆንባችኋል፡ ወይንስ ደስታ? ጌታችን በክብር ሲመጣ፡ በአየር ላይ እንቀበለዋለን። እነዚያን ሃሳቦች በአእምሯችን ይዘን፡ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ጌታ ቢፈቅድ፡ ይህን አገልግሎት ሌላ ጊዜ እጨርሳለሁ።

311 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ እነሆ፡ ከምሥራቅ እና ከምዕራብ ይመጣሉ፡ ከሩቅ አገሮች ይመጣሉ። ስለ ታላቁ መነጠቅ አስባለሁ። በአፍሪካ፡ በህንድ፡ እና በአለም ዙሪያ የሰበክኳቸው ሰዎች፡ ፊታቸውን እንደገና ላይ እናፍቃለሁ።

ወደ አውሮፕላኑ እየወጡ፡ ብዙዎቻቸው፡ በአጥሩ ላይ ተደግፈው እየጮሁ እና እያለቀሱ ነበር። አንድ ጊዜ ከጳውሎስ ጋር የወጡ ሰዎች፡ ተንበርክከው የጸለዩት ጸሎት ትዝ ይለኛል። “ከእንግዲህ ወዲህ… ብዙዎቻችሁ ፊቴን እንደማታዩ እርግጠኛ ነኝ፡” ይላቸው ነበርና።

ግን ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፡
ከሩቅ አገር ይመጣሉ፡
ከንጉሣችን ጋር ለመብላት፡ እንደ እንግዳው ለመመገብ፥
እነዚህ ተጓዦች ምንኛ ብጹአን ናቸው!
የተቀደሰ ፊቱን የሚያዩ (በመረግድ ክብር የከበረ፡)
በመለኮታዊ ብርሃን የበራ ፊት፡

በኩራዝ ወይም በሻማ ሳይሆን፡ በመለኮታዊ ብርሃን—የበራ።

በመለኮታዊ ብርሃን የበራ ፊት፥
የጸጋው ተካፋዮች ብፁዓን ናቸው፡
በዘውዱ ውስጥ እንደ እንቁዎች ያበራሉ።

አምላክ ሆይ!

የእሳት ፍም ነቢዩን በነካ ጊዜ፡
እጅግ በኃይል ንጹህ አደረገው፡
የእግዚአብሔር ድምፅ “ማን ይሄድልናል፡” ባለ ጊዜ?
እነሆ መለሰ “እነሆኝ፡ ላከኝ፡” አለ።

312 አቤቱ፡ ዛሬ ጠዋትም መልአኩን፡ ኢሳይያስ ያያቸው፡ ስድስት ክንፍ ያላቸውን ኪሩቤሎችን ላክልን፡ “ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅድስና፡ ለእግዚአብሔር፡” እያሉ፡ በህንጻው ላይ ይብረሩ። ወጣቱ ነቢይ ኢሳያስም እንዲህ አለ፡ “እኔ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ፡ በረከሰ ህዝብ መካከል የምኖር ነኝ፡ ዓይኖቼም የእግዚአብሔርን ክብር አይተዋል።” የመቅደሱ ምሰሶዎችም ተናወጡ። መልአክም ከመሠዊያው ላይ ጉጠት አነሣ፡ የእሳት ፍምም አውጥቶ በከንፈሩ ላይ አኖረው፡ አለውም፡ “ከንፈሮችህን ቀድሻለሁ። የሰው ልጅ ሆይ፡ አሁን ትንቢት ተናገር።” ጌታ ሆይ፡ ዛሬም ያን መልአክ ላክልን፡ ከንፈሮቻችንን ከክፋት ቀድሰልን። ጌታ ሆይ፡ ግባና፡ ልቦቻችንን ቀድሰ። የራስ-ፈቃድን ሰባብርልን። ይህም… ፈቃዱ (ለአንተ ይሁን) ጌታ ሆይ፡ ፈቃድህ ይሁን። አቤቱ፡ አምላኬ ሆይ፡ ፈቃድህ በእኔ ውስጥ ይሁን። ጌታ ሆይ፡ እኔ እና ቤተክርስቲያኔ እና ህዝቤ የአንተ እንሁን። እራሳችንን ላንተ አሳልፈን ሰጠን።

313 አባት ሆይ፡ ገጣሚው እንዳለ፥

አሁን በኃጢያት በኀፍረት ሚሊዮኖች እየሞቱ ነው፡

በአፍሪካ ውስጥ፡ በህንድ ውስጥ፡ በዓለም ዙሪያ ሁሉ፡ በሰዓት ሺዎች ይሞታሉና፡ አንተን ሳያውቁህ ወደ አንተ እየመጡ ነው።

አሁን በኃጢያት በኀፍረት ሚሊዮኖች እየሞቱ ነው፡

እግዚአብሔር ሆይ፡ እኔ ግን፡ ይህን ሳስብ ነፍሴን ይሰባብራል።

አሳዛኝና መራራ ጩኸታቸውን አድምጥ፥
ፍጠን፡ ወንድሜ፡ ስለደህንነታቸው ፍጠን፥
“ጌታ ሆይ፡ አለሁ በል፡” በፍጥነት።

314 ፍቀድ፡ ጌታ ሆይ፡ አሁንም ፍቀድ። አባት ሆይ፡ በዚህ ባለፈው ዓመት፡ ሁሉንም ዓይነት ስህተቶች ሠርቻለሁ፡ ስለ ሁሉም ይቅር እንድትለኝ እጸልያለሁ። እናም ጌታ ሆይ፡ በዚህ አዲስ አመት፡ እንደገና ቅባኝ። በኃጢያትና በኀፍረት ወደተቀመጡት፡ እየሞቱ ወዳሉት ሚልዮኖች ልሂድ። ይህን የእውነትህን መገለጥ፡ ለእነርሱም የመንፈስ ቅዱስን ቅባት አምጣላቸው፥ በዚያ ቀን ከምሥራቅና ከምዕራብ እየመጡ፡ በዘውድህ ውስጥ እንደ ዕንቁ ያበራሉ። አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ የተቀበሩበትን የምድር አፈር ላይ ወርጄ፡ የሚኖርበትም የምድር እርኩሰት አይቼ፡ ቆፍሬ ላውጣቸው እርዳኝ። በአንተም ፊት የተቀደሰ እና ንጹሕ እንደ ክርስቲያን እንዲኖሩ የሚያደርጋቸውን፡ ቅዱሱን አምላክ ማየት ይሁንላቸው፡ ከክፋት ሁሉ፡ ከዓለማዊነት መደነቅ ሁሉ፡ ወደ ህያው አምላክ መመለስ ይሁንላቸው፡ ለዚያም ለታላቋ ቀን የመንግሥትህ ተወካዮች ይሁኑ።

315 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ይህችን ምስኪን ቤተክርስቲያን ቀድሳት። እዚህ ያለን ሰው ሁሉ በመንፈስህ ቀድሰው፡ መንፈስ ቅዱስም፡ ወደ እያንዳንዳችን ልብ ይግባ። ቀድሞውንም የነበረውን መንፈስ በእነርሱ ውስጥ አድስ-... በራስ-ፈቃድ ልባቸውን ክፈተው፡ የራሳቸውን ፈቃድ ክደው ፈቃድህን ወደ ማወቅ መጥተዋልና።

316 እነዚያ ወጣቶች፡ ጌታ ሆይ፡ ብዙዎቹ ገና ሕፃናት ናቸው። በክንዶችህ እንዴት እንደምታጠባቸው አንተ ታውቃለህ! አንዲት እናት የልጇን እንባ ከዓይኖቻቸው እያበሰች፡ እንክብካቤውን ታውቅበታለች ስለምትወዳቸውም—ልዩ ልዩ ነገሮችን ትሰጣቸዋለች። ጌታ ሆይ፡ አንተም ገና ለተወለዱልህ ለልጆችህ እንዲሁ ነህ። ገና መራመድ፡ ማውራት እንኳን አይችሉም። ማድረግ የሚችሉት ማልቀስ እና እማማን መጠበቅ ብቻ ነው። አምላክ ሆይ፡ እንደ ታናናሽ ጠቦቶች፡ በእቅፍህ፡ በጥንቃቄ ይዘህ፡ በራሳቸው መራመድ እስኪችሉ ድረስ ምራቸው። ከዚያ በኋላም፡ ጌታ ሆይ፡ የአገልግሎት ጎዳና ላይ ምራቸው። አቤቱ ይሁን።

317 የበደሉንን ይቅር እንደምንል፡ ኃጢአታችንን ይቅር በለን። ከክፉ አድነን እንጂ፡ ወደ ፈተና አታግባን። መንግሥትም፡ ኃይልም፡ ክብርም፡ ለዘለአለሙ ያንተ ነውና፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ኣሜን።

318 እግዚአብሔር ይባርካችሁ! ዛሬ ጠዋት ኢየሱስ ክርስቶስን እንድትወዱ አዲሱን ዓመት በዚህ ሲያስጀምራችሁ፡ ጌታ አንድ ነገር እንዳደረገላችሁ አምናለሁ፡ ስለዚህ አንድ ቀን እሱን ማየት እና እሱን መውደድ እና ከእሱ ጋር ለዘላለም መኖርም ያስፈልጋችኋል። ከእናንተ ማንም እንዳይጠፋ፡ ሁላችሁም እንድትድኑ እና በመንፈስ ቅዱስም እንድትሞሉ፡ መምጣቱም በደጅ ነውና፡ እስከ ምጽአቱ ቀን ድረስ እንድትጠበቁ መሻቴ ነው።

አሁን መድረኩን ለወንድም ኔቪል እመለሳለሁ።

61-0101 ራእይ፡ ምዕራፍ አራት ክፍል 2
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ:

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org